# የዲያብሎስ ውጊያዎች

የግብጽ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ
ቅዱስነታቸው አቡነ ሺኖዳ ፫ኛ እንደጻፉት

አያሌው ዘኢየሱስ እንደተረጎመው

የሽፋን ስዕል፡ ዲ. ሲራክ ወጋየሁ

ኅዳር ፲፱፻፺፩ ዓ.ም
አዲስ አበባ

## ምሥጋና

የትርጉሙን ረቂቅ በማንበብ ገንቢ አስተያየታቸውን ለሰጡኝ ለቀሲስ ጌታቸው ደጀኔና ለእህቴ ለሊሻን ተፈራ፣ የትርጉሙን ረቂቅ በኮምፒዩ ተር በመጻፍና በማስተካከል ለረዳችኝ ለእህቴ ለእሌኒ ወጋየሁ፣ ጊዜውን መሰዋዕት በማድረግ የኅትመቱን ሥራ ተከታትሎ ላስፈጸመልኝ ውድ ወንድሜ ያዕቆብ ሰንደቁ መንፈሳዊ ምሥጋናዬ እጅግ የላቀ ነው።

የመጀመሪያ ዕትም ኅዳር 1994

ሁለተኛ ዕትም መስከረም 1995

የእንግሊዘኛው ርዕስ - Diabolic Wars


የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን ደንብና ሥርዓትን ጠብቆ የተዘጋጀ።


መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።
All Rights Reserved



አድራሻ፡ ደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን
/ወይም/
☎ 20 04 38 ✉ 9673
አዲስ አበባ


## ማውጫ


ምዕራፍ አንድ
የዲያብሎስ ውጊያዎች ..... 1

ምዕራፍ ሁለት
ዲያብሎስ በውጊያዎቹ ውስጥ የሚታወቅባቸው ባሕርያት ..... 8
1. የማያቋርጥ ተዋጊ ነው። ..... 8
2. ኃይለኛ ነው። ..... 9
3. በውጊያ የሰለጠነና ማንነታችንን የሚያውቅ ነው ..... 12
4. ብልህና ተንኮለኛ ነው። ..... 12
5. ውሸታም ነው። ..... 12
6. መንቻካ ነው። ..... 15
7. ከሳሽ ነው። ..... 16
8. ብዙ ችሎታዎች አሉት። ..... 17
9. ጨካኝ ነው። ..... 17
10. በማስመሰል ርህራሄው ተንኮለኛ ነው። ..... 18
11. ቀናተኛ ነው። ..... 20
12. ምቹ ጊዜን ይጠብቃል። ..... 21
13. የማያምንና የማይታመን ነው። ..... 21

ምዕራፍ ሦስት
የዲያብሎስ ደባዎች ..... 23
1. በመልካም ምግባር ውስጥ ኃጢአትን መሰወር ..... 23
2. ሌላ መልካም ምግባር ትይዛለህ በሚል ሰበብ የያዙትን ማስጠፋት ..... 25
3. መልካም ምግባራትን ያለቦታቸው እንዲጠቀሙ ማድረግ ..... 30
4. ጥርጣሬን መትከል ..... 31
5. ተስፋ ማስቆረጥ ..... 34
6. ዕቅዱን ይለውጣል ..... 38
7. ኃዘን ..... 43
8. ፍጥነት ..... 45
9. የተራዘመና ዝግ ያለ አቀራረብ ..... 47
10. ጥቃቅን ጉዳዮች ..... 50
11. ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ ..... 51
12. ማባከን ..... 53
13. የእግዚአብሔርን ፍቅር በትክክል እንዳይረዱት ማድረግ ..... 55
14. እምነትና ዋጋን ማዛባት ..... 56
15. የብዙኃኑን ዝንባሌ ማስከተል ..... 60
16. መፈታተን ..... 62
17. ማደንዘዝ ..... 64

18. ሃይማኖትን ወደ ፍልስፍና ማስለወጥ ..... 65
19. ያለ ኃጢአት ማሳረፍ ..... 67
20. ውጪያዊ መልካም ምግባራትን ማጉላት ..... 68
21. ቁጡ ማድረግ ..... 70
22. መሰናክሎችን ማኖር ..... 70
23. ዓይናፋር ማድረግ ፤ በይሉኝታ መያዝ ..... 70
24. ጊዜን ማስባከን ..... 71
25. ረዳቶችን ማስማራት ..... 72

ምዕራፍ አራት
1. የዲያብሎስን ውጊያዎች እንዴት ማሸነፍ ይቻላል? ..... 74
ሀ. ማሸነፍ ይቻላል ..... 74
ለ. አትፍራ ..... 75
ሐ. ዲያብሎስን ተቃወም ..... 78

2. ዲያብሎስን በምንና እንዴት መቃወም ይቻላል? ..... 80
ሀ. በእምነት ..... 80
ለ. በትህትና ..... 82
ሐ. በጥበብና በማስተዋል ..... 84
መ. በምክርና በንስሐ ..... 84
ሠ. በንቁነትና በጥንቃቄ ..... 85
ረ. በጸሎትና በጾም ..... 87
ሰ. ሂድ አንተ ሰይጣን ..... 89
ሸ. ኃጢአትን በእግዚአብሔር ቃል መርምሮ በማየት ..... 91

ምዕራፍ አምስት
የዲያብሎስ ውጊያዎች ጥቅም ..... 93
1. ትሑት መሆንን ..... 93
2. የእግዚአብሔርን እርዳታ ለማግኘት ጸሎትና ጾም መያዝን ..... 93
3. ለኃጥአን ርህራሄ ማድረግን ..... 93
4. የውጊያ ልምድን ያዳብራል ..... 94
5. የድል አክሊልን ያቀዳጃል ..... 94
6. መንፈሳዊ ንቃትና ዝግጁነትን ያጎለምሳሉ ..... 94
7. ጠንካራና የማንፈራ ያደርጋሉ ..... 94
8. የእምነት ት/ቤቶች ናቸው ..... 95
9. የዲያብሎስን እኩል ተሳትፎ ያሳያሉ ..... 95
10. የመንግሥተ ሰማይ በሮችን ይከፍታሉ ፤ ደረጃችንንም ይወስናሉ ..... 95

*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።*

## *ከተርጓሚው*

ከቅዱስነታቸው አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ ብዛት ያላቸው መንፈሳዊ መጻሕፍት መካከል "የተራራው ስብከት" ከሚለው በማስከተል "Diabolic Wars'' በሚል ርዕስ የተጻፈውን "የዲያብሎስ ውጊያዎች" በማለት ወደ አማርኛ ተርጉሜ ለምዕመናን ለማቅረብ እንድችል መድኃኔዓለም ብርታትና እውቀት ስለሆነኝ ክብርና ምሥጋና ይድረሰው።

"Diabolic Wars'' የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል በቀጥታ ወደ አማርኛ ሲመለስ "ዲያብሎሳዊ ውጊያዎች" የሚለውን ትርጉም ይይዛል። እኔ ግን "Diabolic" የሚለውን ቃል "of Diabolos'' በሚለው አንድምታ "የዲያብሎስ" የሚለውን ትርጓሜ እንዲይዝ አድርጌ "የዲያብሎስ ውጊያዎች" በማለት ተርጉሜዋለሁ። "ዲያብሎስ" የሚለውም ቃል የግሪክ ሲሆን "ሰይጣን" የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል ይተካል። ቃሉ በአዲስ ኪዳን እንጂ በብሉይ ኪዳን ውስጥ አይገኝም። ለእኛ አገርና ቤተ ክርስቲያን ይኸው ቃል እንግዳ ስላልሆነና በአዲስ ኪዳን ውስጥም በተለያዩ መጻሕፍት ውስጥ ተጠቅሶ ስለሚገኝ ከእንግሊዘኛው መጽሐፍ እንዳገኘሁት በቁሙ በዚሁ ቃል ተርጉሜዋለሁ። ስለሆነም ዲያብሎስ የሚለውም ቃል በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሰይጣን የሚለውን ቃል ተክቶ ይገኛል።

"የዲያብሎስ ውጊያዎች" የሚለው ይህ መጽሐፍ በአምስት ዋና ዋና ምዕራፎችና በአምሳ ዘጠኝ ንዑሳን ርዕሶች የተከፋፈለ ሲሆን በምዕራፎቹ ሥር ስለ ዲያብሎስ ውጊያ አመጣጥ ፤ ዲያብሎስ በውጊያዎቹ ውስጥ ስለሚታወቅባቸው ባሕርያቱ ፤ የዲያብሎስ ደባዎች ምን እንደሚመስሉ ፤ የዲያብሎስን ውጊያዎች እንዴት ማሸነፍ እንደሚቻልና ስለዲያብሎስ ውጊያዎች ጥቅም በሚገባ ከመገንዘባችን በተጨማሪ ዲያብሎስ በሰው ልጆች ላይ ስለሚያውጀው ጦርነት ፤ ስለ ርኩሳን ባሕርያቱ ፤ እንዴት እንደሚዋጋ ፤ እንደሚያሸንፍ ፤ እንደሚጥልና እንዴት ልንቃወመውና ልናሸንፈው እንደምንችል ውጊያውን በማሸነፋችንም በተጋድሎአችን ምን ዓይነት መንፈሳዊ በረከት እንደምናገኝ ይጠቁመናል።

መጽሐፉ በዓይነቱ የመጀመሪያ ከመሆኑም ባሻገር የባላጋራችን ወጥመድ የት ጋር እንደሚጠመድ ፤ ከወጥመዱ እንዴት እንደምናመልጥ ፤ በምንና እንዴት እንደምናሸንፈው ጠቃሚ ትምህርት ስለሚሰጠን ምዕመናን የትምህርቱ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ በትህትና ላሳስብ እወዳለሁ።

እግዚአብሔር አምላካችን በዲያብሎስ ወጥመዶች ከመያዝ ይጠብቀን!

አያሌው ዘኢየሱስ

# ምዕራፍ አንድ

## የዲያብሎስ ውጊያዎች

መንፈሳዊ ተጋድሎዎች ለእኛው ጥቅም ሲባል ከእግዚአብሔር የሚታዘዙ ናቸው። ስለ እነዚህ ተጋድሎዎችና ስለ ውጤታቸውም አንድ ቅዱስ አባት እንዲህ በማለት ተናግሯል። "ያልተጋደለ አያሸንፍም ያላሸነፈም የድል አክሊል አያገኝም።"

እግዚአብሔር እነዚህን ውጊያዎች የሚያዘጋጀው ነፃ ፈቃዳችንን ለመፈተሽና ድል ካደረግን የመንግሥተ ሰማያት ባለቤቶች ሊያደርገን ወዶ ነው። ባላጋራችን ዲያብሎስ ግን በባሕርይው የእግዚአብሔርን መንግሥት መቃወምና ወደዚያ ለመግባት የሚወዱትን ሁሉ መከልከል ስለሆነ ይዋጋቸዋል። እርሱ የእግዚአብሔርን ልጆች በመዋጋትና ልክ እንደ ኢዮብ በመክሰስ እግዚአብሔርን ይዋጋል። ኢዮብ 1 እና 2። በጽድቅ ሕይወት የሚመላለሱት ሁሉ መለኮታዊውን ቡራኬ እርሱ እንዳላገኘው እነርሱም እንዳያገኙ በቅንዓት ይታገላቸዋል። የዲያብሎስ ውጊያዎች ለሁሉም ስለሆኑ ከእነዚህ ውጊያዎች የሚያመልጥ የለም። ስለ እነዚህ ውጊያዎች ስንናገርም በዲያብሎስ በሠራዊቱና በደጋፊዎቹ ስለሚካሄዱት ውጊያዎች መናገራችን ነው። ከአዳም ከሔዋንና ከልጃቸው ከቃየን ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ ዲያብሎስ የሰው ልጆችን በሞት ጥላ ስር ለመክተት እየተዋጋ ነው። ዲያብሎስ ነቢያትን ሐዋርያትን የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረባቸው ዳዊትና ሶምሶንን (ሁለቱም ኋላ ቢጸጸቱም) እግዚአብሔር የተወውና ቅዱስ መንፈሱ የራቀውን ንጉሥ ሳዖልን በውጊያው ጥሏል። ". . . ከፉም መንፈስ ከእግዚአብሔር ዘንድ አሰቃየው" 1ኛ ሳሙ 16፡14። እናስ አንተ! የዲያብሎስ ውጊያዎች በወጣንያንና በኃጢአተኞች ላይ ብቻ የተነጣጠሩ ይመስልሃልን? አይደለም።

ዲያብሎስ የሚዋጋው ሁሉን ነው። በእግዚአብሔር ጸጋ በማደግ ላይ ያሉትን እንኳ ይዋጋል። እንዲያውም ውጊያው በእነርሱ ላይ ይበረታል። ስለሆነም ማንም ሰው ራሱን ከውጊያዎቹ ነፃ ወይም የበላይ አድርጎ የማሰብና ቸልተኛ መሆን የለበትም። ንጉሥ ዳዊትን እናስታውስ ምንም እንኳ የእግዚአብሔር መንፈስ ቢያድርበትና በእግዚአብሔር የተቀባ ቢሆንም በዝሙት ወድቆ የከፋ ኃጢአትን ፈጽሟል። በዚህም ዲያብሎስ ሁሉን እንደሚዋጋ እናስተውላለን። "ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና" 1ኛ ጴጥ 5፡8 ታዳኙን ለማጥመድ ያለማቋረጥ ይዞራል ማለት ነው። በኢዮብ ታሪክ ላይ እንደምናነበው እግዚአብሔር ሰይጣንን "ከወዴት መጣህ" ብሎ ሲጠይቀው እንዲህ በማለት ነበር በግልጽ የመለሰው። "ምድርን ሁሉ ዞርኋት በእርስዋም ተመላለስሁ" ኢዮ 1፡7 ኢዮ 2፡2። በእርግጥም ይህ ዙረት የሚታደን ለመፈለግ ብሎም ለመጣል የሚደረግ ዙረት ነው።

ዲያብሎስ የሚዋጋው ሰው በመንፈሱ ብርቱ ቢሆንም እንኳ ቶሎ አይተወውም። በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኃጢአት እንዲህ የሚል ቃል አለ። "ወግታ የጣለቻቸው ብዙ ናቸውና እርሷም የገደለቻቸው እጅግ ብዙ ናቸው" ምሳ 7:26። ዲያብሎስ አሥራ ሁለቱን የጌታ ሐዋርያት ለመዋጋት እንኳ አላመነታም። ስለዚህ ውጊያም ጌታችን ለሐዋርያው ለቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ በማለት ተናግሮታል። "ስምዖን ስምዖን ሆይ እነሆ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ" ሉቃ 22:31-32። ዲያቢሎስ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንኳ ሊፈታተነው ደፍሯል። ሦስት ፈተናዎችን በየም ላይ ሳለ አቅርቦለታል። ማቴ 4:1-11። ምንም እንኳ ከዚህ አስቀድሞ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሕርይ በጥምቀቱ ሲገለጥ ቢመለከትና ስለ ማንነቱ ቢያውቅም አርባ ቀንና ሌሊት ከመፈተን ወደ ኋላ አላለም። "ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው" ዕብ 4:15 "እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለ ተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና" ዕብ 2:18 በእርግጥም የክርስቶስ በሰይጣን መፈተን እኛን ለሚገጥመን ፈተና ሁሉ መጽናኛችን ነው። ፈተና ቢገጥማችሁ አትጨነቁ ክርስቶስ ተፈትኖ እንዳሸነፈ እናንተም ታሸንፋላችሁና።

የዲያብሎስ ውጊያዎች በእግዚአብሔር በመንግሥቱና ቤተ መቅደሶቹ በተባልን በእኛ ሁሉ ላይ ያነጣጠሩ ናቸው። ዲያብሎስ የእግዚአብሔርን መንግሥት በማንኛውም መንገድ በመቃወሙና ሰዎችን በመጣሉ ይደሰታል። "ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ" ማቴ 24:24። በመጽሐፍ ቅዱስ "እንዲሁ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል" ሉቃ 15:10 የሚል ቃል እንዳለ ሁሉ ሰይጣንና መልዕክተኞቹ አንድ ጻድቅ ሰው ሲወድቅና ለእነርሱ ፈቃድ ሲገዛ ያለጥርጥር ይፈነድቃሉ።

እንዲህ ስላለው መንፈሳዊ ተጋድሎ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲጽፍ ይህን ብሏል። "የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ። መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ሥፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።" ኤፌ 6:11-12። ሐዋርያው በዚሁ ምዕራፍ ዝቅ ብሎ የዘረዘራቸውን መንፈሳዊ መሣሪያዎች ያልታጠቀ ሁሉ እንደዚህ ያለውን ውጊያ መመከትና መከላከል አይችልም። ይህም ያለ እግዚአብሔር አጋዥነት እንደማይሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ነግሮናል። "ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም" ዮሐ 15:5። እንዲህ ባለው መንፈሳዊ ውጊያ ጊዜ የነቢዩ ዳዊትን ቃላት ማስታወስ ምንኛ መልካም ነው! "ሰልፉ የእግዚአብሔር ነው።" 1ኛ ሳሙ 17:47።

መንፈሳዊ ውጊያ አያቋርጥም። በዓይነቱም ይለያያል እንጂ አያልቅም። ከዚህች ምድር በሞት እስከምንለይበት ቀን ድረስ ሥጋ ለባሾች ስለሆንን ለእነዚህ ውጊያዎች የተጋለጥን ነን። ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ ይለናል።





"በእንግድነታችሁ ዘመን በፍርሃት ኑሩ" 1ኛ ጴጥ 1:17። እዚህ ላይ ፍርሃት የሚለው ቃል ዲያብሎስን እንድንፈራው የተጠቀሰ ሳይሆን ወደ ጥንቃቄና ራስን ወደ መጠበቅ የሚያመራ ፍርሃት መሆኑን ለማመልከት ነው። ለእያንዳንዱ ሰው ከሆነ ውጊያው እስከ ዕለተ ሞት ድረስ አያበቃም። ለዓለሙ ከሆነ ደግሞ እስከ ዕደሜዎች ፍጻሜ ድረስ ይቀጥላል። ሰይጣን ከታሰረበት ከተለቀቀ በኋላም ይህን ዓለም ያታልል ዘንድ ይወጣል። ራዕ 20:7-8። "በኋለኞች ዘመናት . . . ሃይማኖትን ይክዳሉ" 1ኛ ጢሞ 4:1። "በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን እወቅ" 2ኛ ጢሞ 3:1። ከኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት አስቀድሞ ውድቀት ይደርሳል። 2ኛ ተሰ 2:3። ዲያብሎስም በሚችለው ሁሉ ማሳቱን ይቀጥላል ወደ ምድርም ይመጣል። "ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው አውቆ በታላቅ ቁጣ ወደ እናንተ ወርዷል" ራዕ 12:12።

ይህ ቀጣይነት ያለው የዲያብሎስ ውጊያ በቅድስና ወቅት እጅግ እየበረታ ይመጣል። እኛ መንፈሳዊ ሥራ ስንጀምር ዲያብሎስ በጣም ስለሚበሳጭ የሚያጠምደው ሰው ከወጥመዱ ቢያመልጠውም እንኳ ስልቱን እየቀያየረ ይዋጋዋል። ስለሆነም እኛ የቅድስና ሥራ ስንጀምር ውጊያውን ይከፍታል ስልቱን ይቀያይራል ብዙ መሰናክሎችንም ያኖራል። እኛ መንፈሳዊ ሥራ ስንጀምር እርሱ ውጊያውን ይጀምራል። ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ባጠናከርን ቁጥር ዲያብሎስ መንግሥቱ ስለሚናጋ ምቾት አይሰማውም። "The Paradise of the Fathers'' በሚለው መጽሐፍ ውስጥ ያለውን ድንቅ አባባል እስቲ እንመልከት። "በእኩለ ሌሊት የገዳማት ደወል ለጸሎት ሲደወል የሚነቃቁት በጸሎት የሚተጉት መነኮሳት ብቻ ሳይሆኑ ጸሎት እንዳይጸለይ የሚዋጉት የክፋት ሠራዊትም ጭምር ናቸው"። አንድ ቅዱስ አባትም እንዲህ ብሏል "ለጸሎት በቆምክ ጊዜ ሁሉ ተዋግቶ ሊጥልህ የሚችል ኃይል እንዳለ አስብ።"

እኛ መንፈሳዊ ሥራዎችን ማለትም ጸሎትን ተመስጦን ዝማሬን ንባብንና ስግደትን በምንጀምርበት ጊዜ ዲያብሎስ እጆቹን አጣምሮ አይመለከተንም። እርሱም እኛን ሊዋጋበት የሚያስችሉትን የውጊያ ስልቶች ያቀናብራል። በመጽሐፈ ሲራክ እንዲህ የሚል ቃል አለ "ልጄ! ለእግዚአብሔር ትገዛ ዘንድ ወደ ገዳም ብትሄድ ሰውነትህን ለመከራ አዘጋጅ።" ሲራ 2:1 ይህ ምንባብ ምንኩስና በሚሰጥበት ወቅት ባለው ጸሎት ውስጥ ይደገማል። በእርግጥም ዲያብሎስ ሊቃወሙት ዝግጁ የሆኑትን ሁሉ ለመዋጋት ምንጊዜም ዝግጁ ነው። ስለሆነም መንፈሳዊ ሥራህን ተከትሎ ውጊያዎች ቢያጋጥሙህ እንዳይደንቅህ። እነዚህ ውጊያዎችም ፊትህን ከክርስትና እንድትመልስ አያድርጉህ። ምንም ዓይነት ፈተናና መከራ ቢገጥምህ እንኳ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስን ቃል ምንጊዜም አስታውስ። ". . . ድካማችሁ በጌታ ከንቱ እንዳይሆን አውቃችኋልና የምትደላደሉ የማትነቃነቁም የጌታም ሥራ ሁልጊዜ የሚበዛላችሁ ሁኑ።" 1ኛ ቆሮ 15:58። እኛ ትግሉን ስንጀምር እርሱ ውጊያውን ይጀምራል። እኛ መንፈሳዊ ሥራ እንጀምራለን እርሱ ተቃውሞውን ይቀጥላል።

ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን "ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ" (1ኛ ቆሮ 9፡27) በሚለው መርህ ቃል ውስጥ ሥጋን በጾም ማስገዛት ስለሚቻል ሰይጣን ጾምን መቃወሙን እንረዳለን። በጾም ወራት ነፍሳችን ከእግዚአብሔር ጋር ስለምትገናኝ ጾማችን ሰይጣንን ያበሳጨዋል። በተለይም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዲያብሎስን በረታበት በዐቢይ ጾም ወቅት ብዙዎች በፍቅር ስለሚጾሙና ይህም አስቀድሞ መሸነፉን ስለሚያስታውሰው በጾም ክፉኛ ይበሳጫል። ማቴ 4። ስለሆነም ዲያቢሎስ ይህን ጾም ለማደናቀፍ በዚህ ወራት የተለያዩ ችግሮችን በመፍጠር ሰዎች እነዚህን ለመፍታት በሚያደርጉት መጣደፍ መንፈሳዊውን ሥራ እንዲዘነጉ ያደርጋቸዋል። ስለዚህ ማናችንም በዚህ ወቅት ጾምን ከችግሮቻችን ችግሮቻችንንም ከተዘጋጀ ወጥመድ ለይተን ማወቅ አለብን።

መንፈሳዊ ሥራዎች ያለ አንዳች ጥርጥር ርኩሳን መናፍስትን በቅንዓት እንደሚያነሳሳቸው ልናውቅ ይገባል። ዲያብሎስ እርሱ ያጣውን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ መሆንን መንፈሳዊው ሰው እያጠናከረ በሄደ ቁጥር ቅንዓቱ ይጨምራል። ምንም እንኳ ሰው ምድራዊና ሥጋ ለባሽ ቢሆንም በነፍሱ ወደ አርያም መምጠቅ ስለሚችልና ሰይጣን ደግሞ መንፈስ ሆኖ (ማቴ 12፡45) ከእግዚአብሔር የራቀና ርኩስ መንፈስ በመሆኑ (ማር 1፡27) ሁልጊዜ በሰው ልጆች ይቀናል። ገና ከመጀመሪያው ሰይጣን በአዳምና በሔዋን ስለቀናባቸው በኃጢአት ወድቀው ለሞት እርግማን እንዲበቁ አድርጓቸዋል። ስለሆነም "ሞት በሰይጣን ቅንዓት ወደ ዓለም ገባ" እንላለን። ዲያብሎስ በመንፈሳዊ ሥራዎቻቸው አመርቂ ውጤት ባላቸው ላይ ይቀናል። በእግዚአብሔር በተወደሱትና ለእርሱ ቅርብ በሆኑት ይቀናል። ወደ ንስሐ ለመድረስ በሚጥሩትና እግዚአብሔርን ከልብ በሚያመልኩት ይቀናል። በትሑቱ ፣ በየዋሁና በልበ ንጹሑ ይቀናል። ስለሆነም ሁሉንም ይዋጋቸዋል። በእርሱ ቁጥጥር ሥር ያሉትንስ? በኃጢአት ጥላ ሥር ያሉትንስ? በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የደከሙትንስ? እነዚህን ለምን ይዋጋቸዋል? እነዚህን ያሉበትን ሁኔታ እየተመለከተ ከመደሰት ባሻገር ዘወትር እየተከታተለ ወደ በለጠ ጥፋት ይመራቸዋል።

ከዚህ በመቀጠል ሦስት ዐበይት መንፈሳዊ ውጊያዎችን እንጠቅሳለን። የመጀመሪያው ዲያብሎስ ቀላል አሊያም ከባድ ውጊያ የሚከፍትበት ሰው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በራሱ ምኞት የሚወጋ ሰው ነው። ይህን ምስኪን ሰው ሰይጣን መነሻውን ያመለከተውና በውስጣዊ ፍላጎቱ አሊያም ልማድ ብሎ በያዘው ክፉ ዐመሉ እንዲወጋ የሚተወው ሰው ነው። አንዱ በሥጋው ሲፈተን ሌላው በቁም ቅዠቱ ይፈተናል። አንዳንዱ በራሱ ሲፈተን ሌላው ደግሞ በሕሊናው ይፈተናል። ሦስተኛውና የመጨረሻው ደግሞ በሐሰተኛ ወንድሞች፣በክፉ ሰዎች ወይም "የዲያብሎስ ደቀ መዛሙርት" በምንላቸው አሊያም በዲያብሎስ ኃይል የሚፈተን ሰው ነው። ለዚህ ነው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለምስጋና በምናቀርበው ጸሎት ውስጥ "ቅናትን ሁሉ፣መከራውንም ሁሉ፣የሰይጣንንም ሥራ ሁሉ ፣ የክፉዎች ሰዎችንም ምክር ፣ የጠላትንም





መነሳት ፣ የተሰወረውንና የተገለጸውን ከእኛና ከሕዝባችን አርቅልን" በማለት እንድንጸልይ የምታስተምረን።

ሌላው ዓይነት ውጊያ ደግሞ ለመፈተን ወይም ነጥሮ ለመውጣት የሚከፈት ውጊያ ነው። ለዚህ ዓይነቱ ውጊያ ምሳሌ የሚሆነን ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ተዘግቦ እናገኛለን። "ከእነዚህም ነገሮች በኋላ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው እንዲህም አለው አብርሃም ሆይ . . . የምትወደው አንድ ልጅህን ይስሐቅን . . . መስዋዕት አድርገህ ሰዋው።" ዘፍ 22፡2። እዚህ ላይ እግዚአብሔር አምላክ ምስጋና ይግባውና አባታችን አብርሃምን አልተዋጋውም። የፍቅሩን ጥልቀትና ለእርሱ ያለውን ታዛዥነት ይመለከት ዘንድ ፈተነው እንጂ። ይህንንም ፈተና አብርሃም አለፈ።

ኃጥኡም ሆነ ጻድቁ ውጊያ ይከፈትበት ዘንድ ግድ ነው። በኃጥኡና በጻድቁ ላይ በሚከፈተው ውጊያ መካካል ግን ልዩነቱ ምንድር ነው? ዋናው ልዩነት ጻድቁ ውስጡ ንጹሕ ሆኖ ለውጪያዊው ውጊያ የተጋለጠ መሆኑ ነው። ይሁን እንጂ ይህን ውጪያዊ ውጊያ ዝም ብሎ አይመለከተውም። ይልቁንም ባለው አቅም ሁሉ ያሸንፈው ዘንድ ይቃወመዋል ይፋለመዋልም። በሌላ መልኩ ግን ኃጢአተኛውና ክፉው ሰው ለውጪያዊውም ሆነ ለውሳጣዊው ውጊያ የተጋለጠ ሊሆን ይችላል። በውጪ በሰይጣን ፈተናዎች ሲወጋ በውስጥ ደግሞ ከሕሊናውና ከልቡናው በሚመነጩት ፍላጎቶቹ ይወጋል። ስለሆነም የልቡናውን በሮች በመክፈት የዲያብሎስን አሳብና ምክር ያለማመንታት ተቀብሎ ያስተናግዳል። ይህን በመቋቋም ጥቂት ማሰብ ቢችልም እንኳ ተጋድሎው ደካማና ዘለቄታ የሌለው ስለሚሆን የውጪያዊውን ጠላት አሳብ በቆራጥነት እስከ ማስወጣት አይደርስም።

ጻድቃን በውጊያ ወቅት ኃይላቸው ስለሚገለጥ ያሸንፋሉ። ኃጥአን ግን ይሸነፋሉ። ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ጻድቃኑ ለጊዜውም ቢሆን ለራሳቸው ጥቅም ሲባል እንዲሸነፉ ያደርጋል። አንድ ሰው የሚገጥመውን ውጊያ ሁሉ የሚያሸንፍ ከሆነ በትዕቢትና ራሱን ከሁሉ የበላይ በሚያደርግ ውጊያ ሊወድቅ ይችላል። ስለሆነም እግዚአብሔር አልፎ አልፎ እንዲሸነፉ በማድረግ ትሑታንና ልባቸው የተሰበረ ያደርጋቸዋል። በዚህም ጠላት በውጊያው ምን ያህል ከባድና ጭካኔ የተሞላበት መሆኑን በማሳየት ለእንደዚህ ዓይነቱ ውጊያ ለተጋለጡት ወገኖቻቻው እንዲራሩ ያደርጋቸዋል። ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል "ከእነርሱ ጋር እንደ ታሰረ ሆናችሁ እስሮችን አስቡ የተጨነቁትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ ሆናችሁ አስቡ።" ዕብ 13፡3።

የዲያብሎስን ውጊያዎች የማያውቅ ሰው በእነዚህ ውጊያዎች ድል የሆኑትን እየተመለከተ ይፈርድባቸዋል አሊያም ይጠላቸዋል። ውጊያውን የሚያውቀውና የተፋለመው ግን በውጊያው ለሚወድቁት ይራራላቸዋል። ሐዋርያው እንደተናገረም ስለ ድካማቸው ይጸልይላቸዋል። "በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት

ጸንታችሁ ተቃወሙት" 1ኛ ጴጥ 5፡9። ስለ አውሬው በራዕይ ዮሐንስ ላይ የተነገረው ቃል ምንኛ አስፈሪ ነው! "ቅዱሳንንም ይዋጋ ዘንድ ድልም ያደርጋቸው ዘንድ ተሰጠው" ራዕ 13፡7። ከዚህ የሚከተለውስ ምንኛ አስደንጋጭ ነው! "በነገድና በወገንም በቋንቋም በሕዝብ ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጠው። ከዓለምም ፍጥረት ጀምሮ በታረደው በግ ሕይወት መጽሐፍ ስሞቻቸው ያልተጻፉ በምድር የሚኖሩ ሁሉ ይሰግዱለታል" ራዕ 13፡7-8 ምንም እንኳ ይህ ለአንዳንዶች በፍርሃት ተስፋ የሚያስቆርጥ ቢሆንም ለአውሬው ይሰግዱለታል የተባሉት ከዓለም ፍጥረት አንስቶ ስማቸው በሕይወት መጽሐፍ ላይ ያልተፃፈው ናቸው። እነዚህ የጥፋት ልጆች ሲሆኑ ቁጥራቸውም ያለ ጥርጥር ብዙ ነው። ይህም የዲያብሎስን ኃይልና የውጊያዎቹን አስከፊነት ያመለክተናል። ይሁን እንጂ ዲያብሎስና አውሬው ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር መጣላቸው አይቀሬ በመሆኑ በዚህ እንጽናናለን።

ይህን ሁሉ የምንጠቅሰው ጠንቃቆች እንድንሆን ነው። ባላጋራችን በጣም ጨካኝ መሆኑን ካወቅን የሐዋርያውን ቃል በማስተዋል እናጢነው። "እንግዲህ እንደ ጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ።" ኤፌ 5፡15። የዲያብሎስን ድል ማድረግ አያስፈራንም ይበልጥ ጠንቃቆችና ንቁዎች እንድንሆን ያደርገናል እንጂ። በራሳችንም ኃይል እንድንመካም አያደርገንም በውጊያችን ሁሉ ፈጥነን ወደ እግዚአብሔር በመጠጋት እንዲረዳንና እንድናሸንፈው ያደርገናል እንጂ። እርሱ በእኛ አድሮ ዲያብሎስን ይዋጋልናል ዓለሙንም እንድናሸንፈው ያስችለናል። እንዲህም ብሎናል "በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ ፤ ነገር ግን አይዟችሁ ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ።" ዮሐ 16፡33። በእርግጥም እርሱ በዲያብሎስ በተፈተነ ጊዜ አሸንፎታል። አሁንም እያሸነፈው ነው ፤ እስከ ዓለም ፍጻሜም በእኛ አድሮ ያሸንፈዋል። "ነገር ግን በክርስቶስ ሁልጊዜ ድል በመንሳቱ ለሚያዞረን በእኛም በየስፍራው ሁሉ የእውቀቱን ሽታ ለሚገልጥ አምላክ ምስጋና ይሁን።" 2ኛ ቆሮ 2፡14። ጌታችን የእኛን ሥጋ ለብሶ ነው ዲያብሎስን ድል ያደረገው። አሁንም ከኃጢአት ነፃ አድርጎና ቀድሶ የድል አድራጊነትን ኃይልና መንፈስ ሰጥቶታል። ቅዱስ ጎርጎርዮስ በቅዳሴው "እኔነቴን በአንተ ቀድሰህዋል" ብሏል። አስቀድሞ ዲያብሎስ ይህን ሰውነታችንን ተቆጣጥሮት ነበር። ይሁንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንኑ ሥጋችንን ለብሶ ዲያብሎስን ድል በመንሳት የቀደመው ክብራችንንና እርሱን መምሰላችንን መልሶልናል።

ስለሆነም ከአሁን በኋላ ይህ ሰውነታችን ዲያብሎስ ባስፈለገው ጊዜ ሁሉ በማሸነፍ የሚያላግጥበት መጫወቻው አይደለም። በእርሱ ተሸንፏልና ይፈራው ጀምሯል። መድኃኒታችን የፍርሃትን መንፈስ ከእኛ በማራቅ የዲያብሎስን ኃይል ድል የምናደርግበትን መንፈስ ሰጥቶናል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ተናገረውም ክርስቶስ በእኛ አድሮ ዲያብሎስን ድል እንደሚያደርገው ተስፋ አለን። "በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል





እንድትጠነክሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር . . ." ኤፌ 3፡16። ስለዚህ ዲያብሎስ ውጊያ በሚከፍትብን ወቅት ሁሉ የመድኃኒታችን ክንድ ከእኛ ጋር ስላለና በእኛ ቦታ ሆኖ በመዋጋት ድል ስለሚያደርግልን ውጊያዎቹን እንፈራቸው ዘንድ አይገባም። እግዚአብሔር የዲያብሎስን ውጊያዎች አያጠፋልንም እናሸንፋቸው ዘንድ ግን ያስችለናል። አምላካችን ስለ እኛ ተዋግቶ ዲያብሎስን ድል ሲያደርገው እኛ ደግሞ ፈቃዱን በመፈጸም እየኖርን ያዘጋጀልንን የድል አክሊል ከእርሱ እንቀበላለን።

ከዚህ በላይ ያነሳነው ሁሉ ወደሚቀጥለው ምዕራፍ ማለትም "ዲያብሎስ በውጊያዎቹ ውስጥ የሚታወቅባቸው ባሕርያት" ወደሚለው የሚያሸጋግረን አጠር ያለ መግቢያ ነው።

# ምዕራፍ ሁለት

## ዲያብሎስ በውጊያዎቹ ውስጥ የሚታወቅባቸው ባሕርያት

የጠላታችንን የውጊያ ጥበብ ፤ በውጊያዎቹ ውስጥ መገለጫ ባሕርያቱና በምን ዓይነት ዘዴ እንደሚዋጋን ማወቃችን እንዴት መልሰን እንደምንዋጋው ስለሚያስችለን ይጠቅመናል።

ዲያብሎስ በውጊያዎቹ ውስጥ የሚገለጥባቸው ባሕርያት እንደምን ያሉ ናቸው? እንዴት ይዋጋል? የውጊያ ዘዴው ተመሳሳይ ነው ወይስ እንደ ሁኔታው ይቀያየራል? የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስን ቃል አብነት አድርገን በእነዚህ ጥያቄዎች ዙሪያ በመነጋገር እንዴት ዲያብሎስን መቋቋም እንደምንችል እንመለከታለን። “በሰይጣን እንዳንታለል የእርሱን አሳብ አንስተውምና።” 2ኛ ቆሮ 2፡11። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል ስለ ዲያብሎስ ከዚህ የሚከተሉትን ባሕርያቱን እናውቃለን።

1. የማያቋርጥ ተዋጊ ነው።

ሰይጣን ከወደቀበት ጊዜ አንስቶ ዋና ዓላማው ጠብ መጫርና መዋጋት ሆኖአል። እርሱ ምንጊዜም ተዋጊ ነው። የቀደሙት ወላጆቻችን አዳምና ሔዋንን ከመዋጋቱ አስቀድሞም ተዋጊ ስለነበር ብዙ ቅዱሳን መላዕክትን በማሳሳት የኃይሉ መጠቀሚያ ሠራዊት አድርጓቸዋል። ከዚህ ጊዜ በኋላ ተዋግቶ መጣልን ልማዱ አድርጎታል። በዚህም መሠረት ኪሩብን ሊቃናትን ሥልጣናትን ኃይላትን ነቢያትንና ሐዋርያትን የተመረጡትንም ሳይቀር መዋጋቱን ቀጥሏል። ባሕታውያንን መናንያንን መነኮሳትንና እግዚአብሔርን የሚወዱትንም ይወጋል። በመልካም አኗኗርና በጽድቅ ያሉትንም ሁሉ ይዋጋቸዋል። ተቃዋሚና ተቀናቃኝ የሚሉት ስያሜዎች የተቀጸሉለትም ምንጊዜም የእግዚአብሔርን መንግስትና ፈቃድ ስለሚቀናቀንና ስለሚቃወም ነው። ዘንዶው፤የቀደመው እባብ፤ሰይጣን፤ ዲያብሎስ የሚባሉትም የእርሱ መጠሪያዎች ናቸው። ራዕ 12፡9 ከክርስቶስ ስቅለት አስቀድሞም “የዚህ ዓለም ገዥ” ተብሏል። ዮሐ 14፡30 ውጊያን አቋርጦ፤ደክሞና እረፍት ወስዶ አያውቅም። ምንጊዜም ቢሆን “እንደሚያገሳ አንበሳ” ይዞራል። 1ኛ ጴጥ 5፡8። በኢዮብ ታሪክ እንደምናነበውም ከአንዴም ሁለት ጊዜ ለእግዚአብሔር ሥራ ፊት አለመሆኑን ተናግሯል። “ምድርን ሁሉ ዞርኋት ፤ በእርሷም ተመላለስሁ” ፤ “በምድር ላይ ዞርሁ በእርሷም ተመላለስሁ” ኢዮ 1፡7፤2፡2። የነደፋቸውን ሁሉ ያለማቋረጥ ይከታተላቸዋል። ክፉ ዘሩንም ባገኘበት ይዘራል። እግዚአብሔር ስንዴ በዘራበት እርሻ ሁሉ እርሱ እንክርዳድ ይዘራል። “ሰዎች ሲተኙ ግን ጠላቱ መጣና በስንዴው መካከል እንክርዳድ ዘርቶ ሄደ” ማቴ 13፡25።

ዲያብሎስ ሰዎችን ብቻ ሳይሆን ቅዱሳን መላእክትንም ይዋጋቸዋል። ከመላእክት አለቃ ከቅዱስ ሚካኤል ጋር ስለ ሙሴ ሥጋ ተከራክሯል። ይሁዳ





ቁ.9 በእግዚአብሔር መልአክ ፊት ታላቁን ካህን ኢያሱን ይከሰው ዘንድም ቆሟል። ዘካ 3፡1-2። እግዚአብሔር ለሃያ አንድ ቀናት ወደ ዳንኤል የላከውን መልአክ ሊቀ መላእክት ሚካኤል ሊረዳው እስከመጣበት ቀን ድረስ ዲያብሎስ እየተቃወመው ነበር። ዳን 10፡12-13። ከዚህ የበለጠ የሚያስገርመውን ደግሞ በራዕይ ዮሐንስ ላይ እናነባለን። “በሰማይም ሰልፍ ሆነ ፤ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውንና መላእክቱን ተዋጉ” ራዕ 12፡7። ምንም እንኳ ውጊያዎቹ ሁሉ በአብዛኛው በጥፋትና በሽንፈት ቢጠቃለሉም መዋጋቱን አላቆመም። እነሆ ውጊያ ከተፈጥሮ ባሕርያቱ አንዱ እየሆነ መጥቷል።

2. ኃይለኛ ነው።

በመዝሙር 102፡20 ላይ “ብርቱዎችና ኃያላን” የሚለው ቃል ዲያብሎስ ከመላእክት አንዱ እንደመሆኑ ለእርሱም የተነገረ ነው። እንደ መልአክነቱ ንጽህናና ቅድስናውን አጣ እንጂ ኃይሉን አላጣም። ለዚህም ነው ሐዋርያው “የሚያገሳ አንበሳ” ያለው። 1ኛ ጴጥ 5፡8። በመጽሐፈ ኢዮብ ውስጥም ዲያብሎስ ኢዮብን “ከእግሩ ጫማ ጀምሮ እስከ አናቱ ድረስ በክፉ ቁስል መታው” የሚል ታሪክ እናነባለን። ኢዮ 2፡7። ከዚህም በተጨማሪ እነሆ ኃይለኛ ዐውሎ ነፋስ ከምድረ በዳ ተነስቶ የኢዮብን ቤት አራቱን ማዕዘን በመምታት በባለቤቶቹ ላይ ወድቆ ሁሉንም እንዲገድላቸው አድርጓል። ኢዮ 1፡19። ከእነዚህ በተጨማሪ ብዙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች ኃይሉን ገልጠው አሳይተዋል። ከእነዚህም የሚከተሉት ይገኙበታል።

*በጥፋት ውኃ ዘመን ዲያብሎስ ዓለሙን ሁሉ ወደ ጥፋት መምራት ችሏል። የአባታችን የኖህ ቤተሰቦች ብቻ ሲድኑ ሁሉም ጠፍተዋል። በዚያን ወቅት ምድርን ከኃጢአት ለማንፃት ብቸኛው መንገድ የሕይወት እስትንፋስ ያለውን ተንቀሳቃሽ ፍጥረት ሁሉ ከገጸ ምድር ማጥፋት መሆኑን እግዚአብሔር ወስኗል።

* በሰዶምና ገሞራም እንዲሁ ነው። እግዚአብሔር በዚያች ሀገር ያሉትን በደለኞች ስለ አሥር ጻድቃን ሊምር ቃል ከገባ በኋላ ስለታጡ ጠፍታለች። ዘፍ 18፡32 የተገኙት አራቱ የሎጥ ቤተሰቦች ሲሆኑ ከእነርሱም አንዲቱ ይህችውም የሎጥ ሚስት ከተማዋ መውጪያ ላይ የጨው ዓምድ ሆና ቀርታለች። ሁለቱ የሎጥ ሴት ልጆችም ቢሆኑ ከሰዶም ከወጡ በኋላ በድለዋል። ስለ ሎጥ እንዲህ ተብሎ ተጽፏል። “ጻድቅ ሎጥም በመካከላቸው ሲኖር እያየና እየሰማ ዕለት ዕለት በአመፀኛ ሥራቸው ጻድቅ ነፍሱን አስጨንቆ ነበርና።” 2ኛ ጴጥ 2፡8

* የዲያብሎስ ኃይል ዓለሙ ሁሉ ወደ ጣዖት አምልኮ እንዲዞር ማድረግ ችሏል። ከአንድ አገር ሕዝብ በስተቀር በዚያን ጊዜ እንዴት አድርጎ ዓለሙን ሁሉ ወደ ጣዖት አምልኮ ሊመራ ቻለ? ይህ አደገኛ ነገር

ነው። በመጨረሻ ያ የአንድ አገር ሕዝብም ለአምልኮ ጣዖት ተንበረከከ። ሙሴ በተራራው ላይ ሳለ ወገኖቹ በወርቅ ቀልጦ ለተሠራ የጥጃ ምስል የሚቃጠል መስዋዕት አቅርበው እንዲህ አሉ "እስራኤል ሆይ! እነዚህ ከግብጽ ምድር ያወጡህ አማልክትህ ናቸው።" ዘጸ 32፡1-6።

* በነቢዩ በኤልያስ ዘመን በንጉሡ በአክአብ ዘመነ ንግሥና በእግዚአብሔር ሕዝቦች መካከል አራት መቶ አምሳ የበአል ነቢያትና አራት መቶ የማምለኪያ ዐጸድ ነቢያት ነበሩ። በአጠቃላይ ከንግሥቲቱ ከኤልዛቤል ማዕድ የሚበሉ ስምንት መቶ አምሳ የሐሰት ነቢያት ነበሩ ማለት ነው። 1ኛ ነገ 18፡19። መጽሐፈ ነገሥትና መጽሐፈ ዜና መዋዕልም በይሁዳና በኢየሩሳሌም የነገሡ አብዛኞቹ ነገሥታት ለጣዖት አምልኮ እንደተንበረከኩ ይተርኩልናል።

* ጠቢቡ ሰሎሞንም በዲያብሎስ ኃይል ከወደቀ በኋላ አምልኮ ጣዖትን ፈጽሟል። ሰሎሞን ማለት በምድር ላይ እንደ እርሱ ጠቢብ የሌለ ፤ጥበብና ማስተዋል ከእግዚአብሔር የተሰጠው (1ኛ ነገ 3፡12)፤ እግዚአብሔር ከአንዴም ሁለት ጊዜ የተገለጠለት (1ኛ ነገ 3፡5 ፤ 9፡12)፤ ለአምልኮ ጣዖት እንደተንበረከከ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ እናነባለን። "ሰሎሞንም ሲሸመግል ሚስቶቹ ሌሎችን አማልክትን ይከተል ዘንድ ልቡን አዘነበሉት። የአባቱን የዳዊት ልብ ከአምላኩ ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም እንደ ነበር የሰሎሞን ልብ እንዲሁ አልነበረም። ሰሎሞንም የሲዶናውያንን አምላክ አስታሮትን የአሞናውያንንም ርኩሰት ሚልኮምን ተከተለ። 1ኛ ነገ 11፡4-8። በእርግጥም ይህ የዲያብሎስ ኃይል እንዴት ወዳለ አስደንጋጭና አደገኛ ደረጃ ሊደርስ እንደሚችል ያሳየናል።

* ሌላው የዲያብሎስ ኃይል ማረጋገጫ የሚሆነንን የምናገኘው በመጨረሻዎቹ ቀናት ምን እንደሚደረግ ስናጤን ነው። በዚህ የመጨረሻ ዘመን "ሺሁም ዓመት ሲፈጸም ሰይጣን ከእስራቱ ይፈታል ፤ በአራቱም በምድር ማዕዘን ያሉትን አሕዛብ ያስታቸዋል።" ራዕ 20፡7-8። ሐሰተኛ ክርስቶሶችና ሐሰተኛ ነቢያት አድርጎ ወደ ዓለም የሚልካቸውም ቢቻላቸው የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ድንቅና ምልክት ያሳያሉ። ማቴ 24፡24። በዚያች የጭንቅ ጊዜ የሚታየውን የዲያብሎስ አደገኛ ሥራ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደዚህ ገልጾታል። "እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር ፤ ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለተመረጡት ሰዎች ያጥራሉ" ማቴ 24፡22። በእነዚህ ቀናት ዲያብሎስ ፀረ ክርስቶስ የተባለውን የዓመፃ ሰው ይልከዋል። ይህም ራሱን ከእግዚአብሔር በላይ በማድረግ የሚመጻደቀው ነው። "በዚያም ጊዜ ጌታ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ የሚያጠፋው ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው ዓመፀኛ ይገለጣል፤ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ የእርሱ መምጣት በተዓምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው።" 2ኛ ተሰ 2፡9-10።





የሰይጣን የኃይሉ ውጤት በመጀመሪያ ጥፋትን ያመጣል። ይህም የሚሆነው ከክርስቶስ መምጣት አስቀድሞ ነው። ነገር ግን ይህን ፀረ ክርስቶስ የተባለ የጥፋት ሰው ጌታችን ከአፉ በሚወጣው መንፈሱና በመገለጡ ድንቅ ብርሃን አጥፍቶት ቀኖቹን ስለሚያሳጥርልን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። 2ኛ ተሰ 2፡8። ሌሎቹ የሰይጣን ኃይል የተገለጠባቸው ክስተቶች የሚከተሉት ናቸው።

* እርሱ በታላቁ ሐዋርያ በቅዱስ ጴጥሮስ አንደበት ተናግሯል። ስለሆነም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ወደ ኋላዬ ሂድ አንተ ሰይጣን . . . እንቅፋት ሆነህብኛል" ብሎታል። ማቴ 16፡22-23። ጴጥሮስን ብቻ ሳይሆን ሌሎቹንም አሥራ አንዱን ሐዋርያት እንደ ስንዴ ሊያበጥራቸው ወዷል። ነገር ግን መድኃኒታችን ይህን እንዲያደርግ አልፈቀደለትም። ሉቃ 22፡31-32። እርሱ ጠረኛና ጀግኖች የነበሩትን ዳዊትንና ሶምሶንን ጥሏል። በለዓምን አጥፍቷል፤ከቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያት አንዱ የነበረውን ዴማስንም ነጥቋል። ብዙ የጣላቸው ጠንካሮች አሉ። ምሳ 7፡26 የነቢዩ የዳዊት ቃላት ምንኛ እውነት ናቸው! "ኃያላን እንዴት ወደቁ! የሰልፍም ዕቃ እንዴት ጠፉ!" 2ኛ ሳሙ 1፡27።

* ሌላው ኃይሉ በብዙዎች ላይ በአንድ ጊዜ ተገልጦ መታየቱ ነው። አንዳንድ ሰዎች ዲያብሎስ ከእነርሱ ይወጣላቸው ዘንድ ይወዳሉ። እነዚህም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያቱ "አጋንንትን አውጡ" (ማቴ 10፡8) በማለት እንዲያወጡአቸው የተናገራቸው ርኩሳን መናፍስት ናቸው። ከእነዚህም አንድ "ሌጌዎን" ያደረበት ሰው ነበር። ማር 5፡9 ስለዚህ ርኩስ መንፈስ "ሊያሸንፈው የሚችል አልነበረም" (ማር 5፡4) የሚል ቃል ተጽፎ እናነባለን። በዚያን ወቅት የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት እንደነዚህ ያሉትን ርኩሳን መናፍስት ከሰዎች ማስወጣት ተስኗቸው ነበር። ስለሆነም ጌታችን እንዲህ አለ። "ይህ ወገን በጸሎትና በጾም ካልሆነ በምንም ሊወጣ አይችልም።" ማር 9፡9።

ይህ ኃይል ስላለውም ይሆናል እግዚአብሔር ለአንድ ሺ ዓመታት ያሰረው። "የቀደመውንም እባብ ዘንዶውን እርሱም ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለውን ያዘው ፤ ሺ ዓመትም አሰረው። ወደ ጥልቁም ጣለው . . . ከዚያም በኋላ ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ ይገባዋል።" ራዕ 20፡2-3። ይሁን እንጂ ስለ ዲያብሎስ ኃይል ከዚህ በላይ የተነገሩት ሁሉ አንተን ሊያስፈሩህ አይገባም። ምክንያቱም ምንም እንኳ ዲያብሎስ ኃይለኛ ቢሆንም ኃይሉ ከእግዚአብሔር ኃይል ስለማይበልጥ ነው። ይህም በመሆኑ እግዚአብሔርን ብቻ አይደለም ብዙ ቅዱሳን አባቶች ድል ስለሚያደርጉት ይፈራቸዋል።

### 3. በውጊያ የሰለጠነና ማንነታችንን የሚያውቅ ነው።

ዲያብሎስ የሰው ልጆችን በመዋጋት ከሰባት ሺ ዓመታት በላይ ልምድ አለው። ይህም ከአዳም አንስቶ ሲሆን ምን ያህል የካበተ የሰው ልጆችን የመዋጋት ልምድ እንደሆነ አስተውል! በዚህም ያለጥርጥር ምንኛ የሰው ልጆችን ነፍስ እንደሚያውቃትና እንዴትስ ሊዋጋት እንደሚችል መረዳቱን እንገነዘባለን። የሰው ልጆችን ነፍስ በሚገባ ስላጤናት ደካማና ጠንካራ ጎኗን ማወቅ ብቻ ሳይሆን በምን ዓይነት ዘዴ እንደሚዋጋትም ያውቃል። ዲያብሎስ ታላቁ የሥነ ልቦና ጠቢብም ነው። ለእርሱ የሥነ ልቦና ትምህርት ተራ "ቲዎሪ" ሳይሆን የሰው ልጆችን ሁሉ በሚያቅፍ መልኩ በተግባራዊ ሳይንስ የተደገፈ የልምድ ችሎታ ነው። ስለሆነም መቼ እንደሚዋጋ እንዴት እንደሚዋጋና መቼስ ማፈግፈግ እንዳለበት ያውቃል። የአእምሮና የልቦና በሮች በየት በኩል እንደሆኑም ያውቃል።

### 4. ብልህና ተንኮለኛ ነው።

ዲያብሎስ "የቀደመው እባብ" ተብሎ ተጠርቷል። ራዕ 20፡2 ፤ 12፡9። ስለ እርሱ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል። "እባብም እግዚአብሔር ከፈጠረው ከምድር አውሬ ይልቅ ተንኮለኛ ነበር።" ዘፍ 3፡1። በዚህ ተንኮሉም ብልህና አዋቂ ነው። እኛም "እንደ እባብ ብልህ" እንድንሆን ተነግሮናል። ማቴ 10፡16። የዲያብሎስ ጥበብ ግን ማጭበርበር ጮሌነትና ሰውን መጉዳት የተሞላበት ነው። የሰይጣን ጥበብ እንደ ሁኔታው የውጊያ ስልቱንና ታክቲኩን መለዋወጥ በመቻሉ ይገለጣል። አደገኛ ከሚባሉ ዘዴዎቹም መዋሸት ፣ ማታለልና ማጭበርበር ስለሚገኙበት የሚዋጋው ሰው አመጣጡን ለማወቅ ግራ ይጋባል። ከዚህ በተጨማሪ ኃጢአትን እንደ መልካም ምግባር አድርገን እንድንቆጥር ያሳስበናል። ሌላም ሌላም . . . የዲያብሎስ ተንኮሎች ምንኛ ብዙ ናቸው!

### 5. ውሸታም ነው።

የቀደሙ ወላጆቻችን አዳምና ሔዋን "ሞትን አትሞቱም" እና "እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ" (ዘፍ 3፡4-5) በማለት ዋሽቷቸዋል። ውሸት የዲያብሎስ ልዩ ባሕርይ በመሆኑም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ሐሰተኛ የሐሰትም አባት" (ዮሐ 8፡44) ብሎታል። እንዲህ የተባለው ዲያብሎስ የሚነግረንን ማንኛውንም ነገር በማመን ከመታለል እንድንጠነቀቅ ነው። የዲያብሎስ ውሸት በሚናገራቸው ቃላት ብቻ ሳይሆን በሌላም አደገኛ በሆነ መልኩ ያስተላልፋቸዋልና ነው። ይህም በሚልካቸው ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ክርስቶሶች መናገር መቻሉ ነው። ከእንደነዚህ ካሉትም የዲያብሎስ መልእክተኞች እንዴት መጠበቅ እንዳለብን ጌታችን እንዲህ በማለት ነግሮናል። "በዚያን ጊዜ ማንም እነሆ ክርስቶስ ከዚህ አለ ወይም ከዚያ አለ ቢሏችሁ አትመኑ። ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሳሉና፤ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ





ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ።" ማቴ 24፡23-24። በእርግጥ የሚያሳዩአቸውን ድንቅና ምልክት ከዓመፃ ሰው ይኸውም ከዲያብሎስ የሚያገኟቸው ናቸው። "የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው።" 2ኛ ተሰ 2፡9።

ለዚህ ምሳሌ የሚሆነንና ዲያብሎስ እንዴት በሐሰተኞች ነቢያት አፍ እንደተናገረ የሚያስገነዝበንን ቃል እንመለከታለን። ዲያብሎስ ንጉሥ አክአብን እንዴት ለጥፋት እንዳመቻቸው በመጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ተጽፏል። "እኔ አሳስተዋለሁ . . . ወጥቼ በነቢያቶቹ ሁሉ አፍ ሐሰተኛ መንፈስ እሆናለሁ አለ።" 1ኛ ነገ 22፡21-22። መንፈስ ቅዱስ በቅዱሳን ነቢያት አንደበት እንደሚናገር ሁሉ ዲያብሎስም በሐሰተኞች ነቢያት አንደበት ይናገራል።

በሌላም በኩል ዲያብሎስ ሐሰቱን በውሸት ሕልምና ራዕይ ያስተላልፋል። በእንደነዚህ ባሉት ብዛት ያላቸው ሐሰተኛ ሕልሞችና ራዕዮች መነኮሳት አባቶቻችን ምንኛ ይፈተኑ?! እንዲህ ዓይነቱ ተጋድሏቸው "The Paradise of Monks'' በሚለው መጽሐፍ ውስጥ ተጽፎ እናነባለን። እስቲ ለምሳሌ የሚሆነንን አንድ ታሪክ እንመልከት። በአንድ ወቅት ዲያብሎስ ለአንድ መነኮስ አባት ተገልጦ "እኔ መልአኩ ገብርኤል ነኝ ፤ እግዚአብሔር ወደ አንተ ልኮኝ መጥቻለሁ" ይለዋል። መነኮሱም በትህትና "እኔ ኃጢአተኛ ነኝ ፤ የእግዚአብሔርን መልአክ እመለከት ዘንድ አይገባኝም። ምናልባት የተላከኸው ወደ ሌላ አባት ሆኖ ሳለ እኔ ዘንድ በስህተት መጥተህ ይሆናል" በማለት ሲመልስለት ዲያብሎስ ውሸቱ ስለተገለጠበት ያን መነኩሴ አባት ትቶት ይጠፋል።

ከእግዚአብሔር በሚመስሏቸው ብዛት ባላቸው ሐሰተኛ ሕልሞች ዲያብሎስ ስንት ሰዎችን አሳስቶ ይሆን? "ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና።" 2ኛ ቆሮ 11፡14። በአንድ ወቅት ጋሌዎን ለተባለ ባህታዊ እንደ ተሰወሩ አባቶች ተመስሎ ይገለጥለትና ወደ እነርሱ ህብረት እንዲገባ ይጠይቀዋል። ጋሌዎንም ባለማወቅ ተከትሏቸው ይጓዛል። በመጨረሻም ምንም በማይገኝበት ዱር ውስጥ አሹፎና አላግጦበት ይሄዳል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር አምላክ ስለ ቀደመ ተጋድሎው ስለ ልብ ንጽህናውና ስለነበረው መንፈሳዊ ቅንዓት ሲል ያድነዋል።

በሌላም በኩል የዲያብሎስ ውሸት በጠንቋዮችና በአስማተኞች በኩል ይተላለፋል። ይህን በተመለከተ እግዚአብሔር እንዲህ በማለት አዟል። "አምላክህ እግዚአብሔር ወደ ሚሰጥህ ምድር በገባህ ጊዜ እነዚያ አሕዛብ የሚያደርጉትን ርኩሰት ታደርግ ዘንድ አትማር። ወንድ ልጁን ሴት ልጁን በእሳት የሚያሳልፍ፤ምዋርተኛም ፤ ሞራ ገላጭም ፤ አስማተኛም ፤ መተተኛም ፤ በድግምት የሚጠነቁልም ፤ መናፍስትንም የሚጠራ ፤ ጠንቋይም ፤ ሙታን ሳቢም በአንተ ዘንድ አይገኝ። ይህን የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር የተጠላ ነው። ስለዚህም ርኩሰት አምላክህ እግዚአብሔር

ከፊትህ ያሳድዳቸዋል” ዘዳ 18፡9-12። ምናልባት በዚህ ጥቅስ ውስጥ አንድ የምናስተውለው ነገር ይኖራል። የዲያብሎስ ውሸት በመናፍስት ጠሪዎችና በሙታን ሳቢዎች ውስጥ እንኳ መገለጥ እንደሚችል በእንደዚህ ዓይነቱ ግንኙነት መካከል ዲያብሎስ ስለዚያ ስለተጠራው ሰውና ስለ ቤተሰቦቹ ማንነት የሚያውቃቸውን አንዳንድ ነገሮች የውሸቱ ማላበሻ አድርጎ እነዚያን ሰዎች ሊያታልላቸው ይችላል። ከተቀበሉት ሰዎችን የሚያታልልበትን ሙሉ የውሸት ታሪኩን ቀስ በቀስ በመተረክ ፍጹም ወደ ተሳሳተ መንገድ ይመራቸዋል።

በኮከብ ቆጣሪዎችና የተሰወረውን እንገልጣለን በሚሉ ሰዎች አንደበትም ዲያብሎስ ውሸቱን ይነዛል። ኮከብ ቆጣሪዎች፣የውስጥ እጅ ገጽ አንባቢዎች፣ጠጠር በታኞች፣የስኒ አተላ አንባቢዎችና በተለያየ መንገድ ስለ ሀብት ማግኘት የሚናገሩ ሰዎች ቢኖሩም በሃይማኖት ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር የማይታወቀውን የሚያውቅ የለም። ስለሆነም ማንም የተሰወረውን (የማይታወቀውን) አውቃለሁ ብሎ ቢናገር እርሱ ውሸታም ነው።

የዲያብሎስ ፈተናዎች በሙሉ የተለያዩ የውሸት ዓይነቶች ናቸው። ሰዎች ደስታን ከኃጢአት እንደሚያገኙ አድርገው እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል። ይህም ደስታ ምናልባት ከመዝናናት፣ከሥልጣን፣ከጥቅም፣ ከክብር ወይም ከፈንጠዝያ የሚመጣ እንዲመስላቸው ያደርጋል። ሰውየው ከወደቀ በኋላ ግን የዲያብሎስ ፈተናዎች በሙሉ ፈጥነው የሚያልፉና የሚጠፉ የውሸት በራሪዎች መሆናቸውን ይገነዘባል። በዚህ መልኩ ነው ሰሎሞን ዙሪያውን በከበበው ምቾትና ተድላ ፍጹም ደስታን እንደሚያገኝ አድርጎ ያሳየው። ይሁን እንጂ ሰሎሞን ሁሉም ከንቱ የከንቱም ከንቱ መሆኑን ተናገረ። ኃጢአትን አስውቦና አስጊጦ በማሳየት ሰዎች ተፈትነው ወጥመዱ ውስጥ እንዲወድቁ ማድረግ የዲያብሎስ ጥበብ ነው። በእነዚህ የሐሰት ጌጣጌጦቹም የኃጢአት ውጤቱ ክፉና አስቀያሚ መሆኑን ከሰዎች ይደብቃል።

የቁም ቅዠትም ሰዎችን የሚያጠምድበት ሌላው የዲያብሎስ የውሸት መሣሪያ ነው። በዚህ የቁም ቅዠት የሚያናውዛቸውም ከዚህ በሚያገኙት የሐሰት ደስታ ተዘናግተው መልካም የሆነውን ሁሉ ከመፈጸም እንዲቆጠቡ ለማድረግ ነው። ከዚህ በኋላ እነዚህ የጥቃቱ ሰለባዎች በሐሰት ቅዠት ተውጠው የአሸዋ ቪላዎችን እየገነቡ የሐሰት ተድላና ደስታን ያልማሉ። ድንገት ሲባንኑም ያለሙት ሁሉ ባዶ መሆኑን፣ዲያብሎስ መልካም ነገር ሊያከናውኑበት የሚችሉትን ጊዜ በከንቱ እንዳባከነባቸውና የውሸት ምቾት እንደሰጣቸው ያውቃሉ።

ዲያብሎስ በሐሰት መረቡ ከሚያጠምዳቸው መካከል አንዱን ለምሳሌ ያህል እንመለከታለን። አንድ ራሱን ለመግደል የሚያስብ ሰውን ራሱን ቢገድል ለጭንቀቱ ሁሉ መፍትሄ ሊያገኝ እንደሚችል በማስመሰል ያታልለዋል። የዚህ ሰው ትኩረትም በሕይወት መኖሩ ሙሉ ለሙሉ ጥቅም





እንደሌለው ለችግሩ ሁሉ ብቸኛው መፍትሄ ሞት መሆኑንና ከጭንቀቶቹ ሁሉ ነጻ የሚያወጣው ይኸው መንገድ ብቻ እንደሆነ በማሰብ ላይ ይሆናል። ሰውየው የዚህን የዲያብሎስ የሐሰት መፍትሄ አምኖ በመቀበል ራሱን ከገደለ በኋላ ግን እረፍት ያጣል። በሲዖል ውስጥ በዚህ ዓለም ከነበሩበት ችግሮችና መከራዎች ሁሉ የበለጠ የማያቋርጥ ድካም፣ሕማምና ስቃይን ይቀበላል። ይሄኔም ሞት ለችግሮቹ ሁሉ መፍትሄ ሳይሆን ለበለጡ ችግሮች የሚጋለጥበት የመጀመሪያው ደረጃ መሆኑን ይረዳል። እንዲህ በማድረግ ዲያብሎስ በውሸት ያታልለዋል፣በተሳሳተ መንገድ ይመራዋል በመጨረሻም ያጠፋዋል። አብዛኞዎቹ ኃጢአቶች ከዲያብሎስ የሐሰት ሰሌዳዎች በስተ ጀርባ የተደበቁ ናቸው። ዲያብሎስ ሌባውን ቢሰርቅ ማንም እንደማያየውና እርሱ መስረቁን ማንም እንደማይደርስበት ያማክረዋል። ይህንኑ ጉዳይ ለጉቦኛው፣ለህገ ወጥ ነጋዴውና ለአጭበርባሪው ሹክ ይላል። በእነዚህ ሁሉ ዲያብሎስ ይዋሻል፤እግዚአብሔር ግን ያያል። በሰው ዓይን ሊታይ የማይቻለው ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ግልጽ ነው።

ለገዳዩም የተገዳዩ ሕይወት ወይም መኖር አላስፈላጊ አሊያም በስህተት የሆነ በማስመሰልና በሞት መስተካከል እንደሚገባው ይህ ካልሆነ ግን የሟቹ መኖር የእርሱን ክብር እንደሚያጎድፍበትና ለተገዳዩ ነፍስ ሰላም የሚያስገኝላት አድርጎ ያሳየዋል። ከሂዶተ እግዚአብሔር ግን በዲያብሎስ ለሰዎች የሚቀርብ ዋናው ሐሰት ነው። ሰው የራሱ አስገኚ እንጂ ፈጣሪ የለውም ለሚሉ ሰዎችም ሀልዎተ እግዚአብሔር የእነርሱን ሀልውና እንደሚያደናቅፈው አድርጎ ያሳያቸዋል። ለማርክሲስቶቹም እግዚአብሔር ከፍ ባለ ማማ ላይ ተቀምጦ ጨቋኙ ሲጨቁን ባለጸጋውም ደሀውን ባሪያ ሲያደርግ የሚመለከትና ለሕዝቡ ግድ የሌለው አምላክ እንደሆነ አድርጎ ያሳያቸዋል።

6. መንቻካ ነው።

ዲያብሎስ የማይደክምና የማይሰለቸው መንቻካ ነው። አንድ ክፉ አሳብን ለሰዎች ሀሊና እጅግ በጣም ብዙ ጊዜ ደጋግሞ ያቀርባል። ሰዎች ይህን ክፉ አሳቡን ውድቅ ቢያደርጉበትም እንኳ ያለ መታከት ደጋግሞ ያቀርብላቸዋል። ምናልባትም አንድ ሰው በዚህ ተደጋጋሚ ግፊትና መንቻካነት ሊረታ ይችላል። ‘‘The paradise of the Father’’ በሚለው መጽሐፍ ውስጥ ዲያብሎስ አንድ መነኩሴን በአንድ ዓይነት ኃጢአት ብቻ ያለ እንዳች ድካምና ተስፋ መቁረጥ ለአምሳ ተከታታይ ዓመታት እንደተዋጋው እናነባለን። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስንም በተፈታተነው ጊዜ መፈታተኑን ከአንደኛው ወይም ከሁለተኛው ወይም ደግሞ ከሦስተኛው ፈተና በኋላ አላቆመም። ጌታ ቢገስጸውና ከአጠገቡ ቢርቅም ቅዱስ ሉቃስ እንደ ጻፈልን እስከ መጨረሻው አልነበረም። “ዲያብሎስም ፈተናውን ከጨረሰ በኋላ እስከ ጊዜው ከእርሱ ተለየ” ሉቃ 4፡13። “እስከ ጊዜው” የሚለው ቃል በሌሎችም ጊዜያት በተደጋጋሚ ሊፈታተነው ተመላልሶ እንደ መጣ የሚያመለክት ነው።

ብዙዎችን ወደ ስህተትና ጥፋት መርቷል። ለአብነትም ብዙዎችን በጥፋት ውኃ ፣ በሰዶም እሳትና ምድር ተከፍታ እንድትውጣቸው ጋብዟል። ዘኍ 16። ከዚህ ሌላ በእርሱ አማካይነት አእምሮአቸውን ባጡና በአበዱ ሰዎች ላይ ይህ ወደር የማይገኝለት ጭካኔው ይገለፃል። እስቲ የጌርጌሴኖኑን ሰው እንመልከት። ". . . አጋንንት ያደሩበት . . . ከብዙ ዘመንም ጀምሮ ልብስ ሳይለብስ በመቃብር እንጂ በቤት አይኖርም ነበር . . . በሰንሰለትና በእግር ብረትም ታስሮ ይጠበቅ ነበር። እስራቱንም ሰብሮ በጋኔኑ ወደ ምድረ በዳ ይነዳ ነበር" ሉቃ 8፡26-29። በሌላ ቦታም ". . . ሁልጊዜም ሌሊትና ቀን በመቃብርና በተራራ ሆኖ ይጮኽ ነበር። ሰውነቱንም በድንጋይ ይቧጭር ነበር።" (ማር 5፡5) የሚል ቃል አለ። እርሱን የሚመስሉ ሌሎችም ብዙዎች እንዳሉ እናስብ።

ጭካኔው ቅዱሳኑን በሚዋጋበት ጊዜ ደግሞ በአስፈሪ ሁኔታ ይገለጣል። አንድ ታላቅና ቅዱስ አባትን እጅግ በጣም አስፈሪ በሆኑ የተለያዩ ገጽታዎች እየተከሰተ ይታየው ነበር። አንዳንዴ በጣም አስቃቂ ድምጽ እያወጣ በዙሪያው በሚዞር አስቀያሚና አስደንጋጭ አውሬ ተመስሎ ይመጣበታል። በአንድ ወቅት ደግሞ አንዱን ጻድቅ አባት ክፉኛ በመጎሰም በሞትና በሕይወት መካከል ትቶት ሄዷል። የቅዱስ ኪራኮስንም ታሪክ የሚያነብ ሌሎች ብዛት ያላቸው ተመሳሳይ አሊያም የከፉ ጭካኔዎቹን ሊገነዘብ ይችላል።

ዲያብሎስ ውጊያዎቹ ጥፋቱና በዓለም መካከል የሚያነሳሳቸው የወንጀል ቀግባራቱ ጭካኔ የተሞላባቸው ናቸው። የእነዚህ ሁሉ ውጤታቸው የታወቀ ነው። ዲያብሎስ ዓለም በእነዚህ ሁሉ ጥፋቶች ሲጠፋ በመመልከት ከመደሰቱ ባሻገር ይህን እንደ ትልቅ ድል ይቆጥረዋል። ኀሊናና ነፍስን በማጥፋት፤ሙግትና ክርክርን በማስፋፋት፣ጠብና መለያየትን በመዝራት ተወዳዳሪ የማይገኝለት አጥፊና በሚያስፋፋው ጥፋትም የሚደሰት ነው። እመኑኝና ዲያብሎስ ቅዱሳኑን ስለተዋጋባቸው እጅግ አስከፊና አስቃቂ ውጊያዎች ብናነብ እኛን የተዋጋበት ውጊያ ምንም እንዳልሆነ በመቁጠር እኛንስ አልተዋጋንም እስከ ማለት እንደርሳለን። የዲያብሎስ ጭካኔ የሚያስደንቀን ደግሞ ርኅሩኅ መስሎ መቅረብ መቻሉ ነው።

## 10. በማስመሰል ርኅራኄው ተንኮለኛ ነው።

የዲያብሎስ የርኅራኄ ቃላት ሰዎችን ለመጣል የሚጠቀምባቸው የክፋት መግቢያዎች ናቸው። በምትጾምበት ወቅት ለአንተ ያዘነ በመምሰል ለጤንነትህ ስትል ብላ ይልሃል። እንዳትደክምና በቀላሉ በበሽታ እንዳትያዝ ያስፈራራሃል። "እግዚአብሔርን ታከብርበት ዘንድ የተሰጠህ ሥጋህን ትጎዳውና ትገድለው ዘንድ አይገባም።" ይልሃል። የሐዋርያውን ቃል ሊጠቅስልህም ይችላል። "ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና . . . ይመግበዋል ይከባከበውማል።" ኤፌ 5፡29። በመንፈስ ስትጠነክር በማስመሰል





ያዝንልሃል። ሌሊት ነቅተህ በጸሎት ስትተጋ፤ስትሰግድና ስታነብ "በትጎትና" ትተኛና ታርፍ ዘንድ ይጠራሃል።

እርሱን መዋጋትህ ከመጠን ያለፈ መሆኑንና በትዕቢት እንዳትወድቅ የፈራልህ በመምሰል ስለ አንተ በጣም "ቸር" እና የሚጨነቅ ሆኖ ውጊያህን ያደክማል። መንፈሳዊ አገልግሎትህንም እያጠነከርክ ስትመጣ "ይህን ሁሉ ታደርግ ዘንድ አይገባም ፤ አባቶቻችን ብዙም ሳይጠልቁ ብዙም ሳይርቁ ማገልገላቸው ብዙዎችን አድኗል በማለት አስተምረውናል።" ይልሃል። የሐሰት ንግግሩን በመቀጠልም "እንዲህ ያለው ውጊያህ እንዲያውም ከዲያብሎስ ነው። እርሱ ደግሞ ለአንተ መልካም እንደማያቅድልህ እወቅ" ይላል። "እጅግ ጻድቅ አትሁን ፤እጅግም ጠቢብ አትሁን እንዳትጠፋ" (መክ 7፡16) ሊልህም ይችላል።

"አዛኝ ልቦና" ያለው በመምሰል የሚቀርብህ ዲያብሎስ ስለ ኃጢአትህ ስታለቅስ ወደ አንተ በመቅረብ "ለምን እያለቀስህ በሐዘን ትኖራለህ? ይህን እግዚአብሔር አይወደውም። እግዚአብሔር ኃጢአትህን ሁሉ በደሙ በማንጻት ይቅር ብሎህ የለምን? ታዲያ ስለምን ስለነዚህ ኃጢአቶችህ ታለቅሳለህ? በሰዎች ፊት አእምሮህንና ነፍስህን አጥተህ እስክትታይ ድረስ በማልቀስህ ልትቀጥል ትወዳለህ?" ካለህ በኋላ አንድ ጥቅስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይጨምርልሃል። "ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ" ፊል 4፡4። የልቦናህን መዋረድና የንስሐ እንባህን አጥተህ እስክትቀዘቅዝ ድረስ ውጊያውን ያፋፍምብሃል። ከዚህ በኋላ ኃጢአት መሥራት ለአንተ ቀላል ስለሆነ ወደ ቀደመው በደልህ ትመለሳለህ። በዚህ ጊዜ "ከሳቅ ኃዘን ይሻላል፤ከፊት ኃዘን ልብ ደስ ይሰኛልና።" (መክ 7፡3) የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንድትዘነጋው ያደርግሃል።

ይኸው "አዛኝ ልቦና" ያለው መስሎ የሚቀርብህ ዲያብሎስ ህሊናህ እንዳይወቅስህ አድርጎ ስህተትህን ትክክል ነው ብለህ እንድትቀበል ያደርግሃል። ለስሜቶችህ የተቆረቆረ በመምሰል ራስህን ከመውቀስ እንድትታቀብ ይመክርሃል። በኃዘንና ተስፋ በመቁረጥ ማዕበል ስትመታም እንኳ "አዛኝ" መስሎ ይቀርብሃል። ከዚያም ለፈጸምካቸው ስህተቶች ሁሉ የተለያዩ ይቅርታዎችንና ቅን የሚመስሉ ፍርዶችን እንድትፈርድ እንዲህ በማለት ያማክርሃል። "ሁሉም ነገር ስህተት ነው አትበል። እንዲህ እያልህ ራስህን በመገሰጽም ጥርጣሬ ውስጥ አትውደቅ። ይህ በእርግጥ ትክክል አይደለም። ይህን ስትል ግን ከልብህ አይደለም። አሳብህ መልካም ስለሆነም ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅሃል ፤ እግዚአብሔር አሳብን ይመለከታልና። ይህም ትክክል አይደለም። ግን ምን አደረግህ? ነገር ግን ያሉት ሁኔታዎች ናቸውና ስለሚፈጥሩብህ እመነኝና እኔም በአንተ ቦታ ብሆን የማደርገው ይህንኑ ነው። እግዚአብሔር ከችሎታህና ከአቅምህ በላይ የሆነውን ከአንተ አይጠይቅምና አትጨነቅ።" ይልሃል። ስህተትህን ትክክል አድርጎ ካሳየህና ካሳመነህ በኋላ ግመልን ትውጥ ዘንድ ኅሊናህን ያሳርፍልሃል። በዚህም ከንስሐ ራስህን ከመጠበቅና በጥቂቱ ከመታመን ያርቅሃል።

የዲያብሎስ “ቸርነት” በነፃ የሚታደል ሳይሆን ሰዎችን ለመጣል ማጥመጃ ሆኖ የሚቀርብ መሣሪያ ነው። ስለዚህ እወቅበት አትስማው። ራስህን አጥብቀህ በመጠበቅ ባህርይህን አጽና። ዲያብሎስ በአንተ ላይ በሚከፍታቸው ውጊያዎች ሁሉ ታማኝ አለመሆኑን አስተውል። መልካም አቀራረብ ይኑራቸው እንጂ ምክሮቹ ሁሉ የሚታመኑ አይደሉም። የአንተ ጥፋት እንጂ ሌላ ምንም አያስደስተውም።

## 11. ቀናተኛ ነው።

መንፈሳዊ ሕይወቱ የተቃናና ጻድቅ የሆነ ሰው በተመለከተ ቁጥር የዲያብሎስ ልቦና እረፍት ያጣል። በሚቻለው ሁሉ ይህን ሰው ለመጣል ይነሳሳል። በዚህ ቅናቱም ምሕረት የሌለበት በትሩን ይቃጣል። ጻድቁ ዮሴፍ በተመለከታቸው ህልሞች በመቅናቱ በወንድሞቹ ልቦና ውስጥ የቅናትን መንፈስ በማስገባት እንደ ባሪያ እንዲሸጡት አድርጓል። ከዚህም በኋላ ዮሴፍ በመልካም ባሕርይው በጲጥፋራ ፊት ሞገስ በማግኘቱ ድጋሚ ስለቀናበት እንደ ጥፋተኛ ተቆጥሮ ወደ ወኅኒ እንዲጣል አድርጓል። በዓለሙ በመቅናቱም ዓለሙ ያለ አምልኮተ እግዚአብሔር እንዲቀር በብዙ አማልክት እንዲያመልክና እግዚአብሔር የለም ብሎ እንዲያምን አድርጎት ይታያል። ለዚህ ዓላማው መሳካትም የተለያዩ አመለካከቶችንና ፍልስፍናዎችን ጥንታዊ አምልኮዎችንም ጨምሮ ይጠቀማል። የመዝሙረኛው ዳዊት ቃላት ምንኛ እውነት ናቸው “የአሕዛብ አማልክት ሁሉ አጋንንት ናቸው።” መዝ 95፥5።

ዲያብሎስ በእውቀት በጥበብ በድንግልናና በትህትና ይቀናል። ስለሆነም አላዋቂነትን፣ዝሙትንና ትዕቢትን በያዘው ክፉ አስተሳሰብ በዓለሙ ውስጥ ያስፋፋል። ሰሎሞንን ከጠቢብነቱ መልሶ በኃጢአት ጥሎታል። ወደ ፊትም የተሳሳተ እውቀት መዝራቱን ይቀጥላል። “ሰነፍ በልቡ እግዚአብሔር የለም ይላል።” መዝ 13፥1። ዝሙትም ዓለሙን ሁሉ የሚዋጋበት አደገኛ መሣሪያው ነው። ትዕቢትም ሌሎች ኃጢአቶችን ሁሉ ያሸነፉትን ሰዎች የሚጠምድበት ጠንካራ የኃጢአት መረቡ ስለሆነ ብዙዎችን በዚህ ጥሏል።

የዲያብሎስ ቅናት ተራ ስሜት ሳይሆን አጥፊ ነው። ዲያብሎስ ልክ ኢዮብን እንደተዋጋው ባለው ኃይል ሁሉ ይዋጋል። በትዕግስቱና በጽናቱ ስለቀናበት በእግዚአብሔር ፊት ከሰሰው። ክፉኛም መታው። በገዳም በሚኖሩ አባቶች ምንኩስናና ብህትውና ስለሚቀናም እጅግ አስቸጋሪና ከባድ የሆኑ ውጊያዎችን ያውጅባቸዋል። በወቅቱ እጅግ ሊቅ በነበረውና በነገረ መለኮት ትምህርት የመጀመሪያው ፕሮፌሰር በነበረው በኦሪገን ዲያብሎስ ስለቀናበት ቤተ ክርስቲያን አውግዛ እስክትለየው ድረስ በጥርጥር ማዕበል መታው። ስለ እርሱም እንዲህ ተባለ “ታላቁ ማማ ሆይ! እንደምን ወደቅህ?” ስለሆነም ማንኛውንም ዓይነት መንፈሳዊ ሥራ በሠራህ ጊዜ ዲያብሎስ እንደሚቀናብህ አስብ። በጽድቅ መንገድ ስትጓዝ ምን ጊዜም ቢሆን ዝም ብሎ አይመለከትህም፣በሚቻለው ሁሉ ሊጥልህ ይጣጣራል እንጂ። ስለዚህ





መንፈሳዊ ተግባርን ከተመሰጠ ጋር በምታከናውንበት ጊዜ ሁሉ ቢተናኮልህ ተስፋ አትቁረጥ። ይልቁንም እንዲህ በለው “ይህን ጠብቄዋለሁ ይሁን እንጂ ዳግመኛ እንዳልወድቅ የእግዚአብሔርን ምህረት በመጠየቅ እጸልያለሁ።”

እግዚአብሔር አንድ ዓይነት ስጦታ ሲሰጥህ ርኩሳን መናፍስት እንደሚቀኑ ጠብቅ። በዚህ ጊዜ በትዕቢት እንዳትወድቅ አሊያም የተሰጠህን የጸጋ ስጦታ አለአግባብ እንድትጠቀምበት ለማድረግ የማያደርጉት ሙከራ አይኖርም። በዚህም መንፈሳዊ ዓላማውን አስተው ስጦታህ ለአንተም ሆነ ለሌሎች የሚሰጠውን ጥቅም ያስቀራሉ።

## 12. ምቹ ጊዜን ይጠብቃል።

ዲያብሎስ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከጾመ በኋላ መራቡን ሲመለከት ይህ ምቹ ጊዜ መሆኑን አውቆ በዳቦ እንደፈተነው ሁሉ ሰዎችን ለመፈተን ማንኛውም ምቹ ጊዜ እንዲያልፈው አይፈልግም። በጴጥሮስ ፍርሃት ተጠቅሞ ጌታውን “አላውቅም” እንዲል አድርጎታል። የአይሁድን በሰንበት ከሁሉ ነገር መከልከልን ተጠቅሞም ከዚያ በፊት ማንም ያላደረጋቸውን የኢየሱስ ክርስቶስን የማዳን ተዓምራት እንዲክዱ አልፎ ተርፎም ኃጢአተኛ ነው ብለው እንዲከሱት አድርጓል። ዮሐ 9፥11።

## 13. የማያምንና የማይታመን ነው።

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ዲያብሎስ ስትጾም ራስህን ስትገዛና ሥጋህን ስታደክም ለጤንነትህ የተጨነቀ በመምሰል ሊቀርብህ ይችላል። በመቀጠልም ስለ ጤንነትህ ስትል ለሰውነትህ እረፍት እንድትሰጥ ያማክርሃል። ዋናው ቁም ነገር ግን ስለ አንተ ጤንነት በእውነት አለማሰቡ ነው። አንተ ሌሊቱን ለጸሎት ለስግደትና መንፈሳዊ መጻሕፍትን ለማንበብ ንቁ ሆነህ ስትገኝ እንድትተኛ ይገፋፋሃል። በአንፃሩ ግን ሥጋህን ለማስደሰት ወይም ለማዝናናት ሌሊቱን ሙሉ ሳትተኛ ብታድር ንቁ ሆነህ መቆየትህ ለጤንነትህ መልካም አለመሆኑን አያማክርህም።

በዓለም ስላለው ከንቱ ነገር ሁሉ በማሰብ ብትደክም ታርፍ ዘንድ ግድ አይልህም። ሀብትን ለማከማቸት፣ሥጋዊ ተድላና ደስታን ገንዘብ ለማድረግ፣ጫጫታና ዳንኪራ የበዛበት ድግስ ለማዘጋጀትና ቁማር ለመጫወት ብትደክምም እንድታርፍ አይጠይቅህም። እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉትን ሥጋዊ ተግባራት ለማከናወን መድከምህ “አያሳዝነውም”፣ ጥቂት እረፍት እንድትወስድም አይመክርህም። እርሱ ታርፍ ዘንድ ግድ የሚልህ ለመንፈሳዊ ተግባራት ደፋ ቀና በምትልበት ወቅት ብቻ ነው። የአንተን ጤንነት አስመልክቶ “ኃዘኔታው” የሚነቃቃው አንተ መንፈሳዊ ተጋድሎዎችን ስታደርግ ብቻ ነው። ስለሆነም በመንፈሳዊ ተጋድሎህ ወቅት ለእረፍት ቢጠራህ አትስማው። እንዲህ ዓይነቱ ጥሪ የማሳነፍና የማዘናጋት

ጥበብ አይደለም። ይህን ካደረገ ዕቅዱ ሁሉ ስለሚታወቅበት ግቡን ይመታ ዘንድ አይችልም። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያቱ እንዲህ ብሏቸው ነበር። “. . . የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል” ዮሐ 16፡2። በእርግጥም ዲያብሎስ ይህን ለሚያደርጉ ሰዎች መግደልን እንደ “ቅንዓት” ወይም “ሃይማኖትን እንደመከላከል” ወይም “የተቀደሰ ተጋድሎ” ወይም ደግሞ “ምድርን ከኃጢአተኞች ማንጻት” በሚሉ የተለያዩ ስሞች ሊያቀርበው ይችላል። ይህም ፈሪሳውያን ሰዱቃውያንና የካህናት አለቆች ኢየሱስ ክርስቶስን ለመስቀል ሞት አሳልፈው በሰጡት ጊዜ በውስጣቸው የነበረው ስሜት ነው።

ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ይመጡ የነበሩትን ሕፃናት ሲገስጹና ሲከለክሉ የነበሩት ሰዎች ይህ በእነርሱ ዘንድ የጭካኔ ተግባር መስሎ እንዲታያቸው አያደርግም። ሉቃ 18፡15። እነርሱ ይህንን “ሥነ ምግባርን ማስጠበቅ” ወይም “የታላቅ ሰው መልካም ምግባር” ይበሉት እንጂ በመልካም ምግባር ስም የተሸፈነ መጥፎ ተግባር ነው። ዲያብሎስ ሐሰትን በጥበብ ስም ሸፍኖ ማቅረብ ይችላል። ይህንንም በመልካም ጠባይ አሊያም ሁኔታዎችን ከጥፋት ለማዳን በሚል ሰበብ ሊያቀርባቸው ይችላል። አንድ ሐኪም “የበሽተኛውን ሞራል ለመጠበቅና ራሱን ከመሳት ተከላክሎ ለማዳን” በሚል ምክንያት ለበሽተኛው ብዙ ውሸት የሆኑ ነገሮችን ሊነግረው ይችላል። እንደዚህ ያሉትን ውሸቶች አንዳንዶች ቅዱስ ውሸት ወይም ጉዳት የማያስከትሉ ውሸቶች (white lies) በማለት ይጠሯቸዋል። እንዲያውም በየዓመቱ በመጋቢት ወር መባቻ ላይ እንደዚህ ያሉትን ውሸቶች “ቀልዶች” “ተረቶች” ወይም ሌሎች ስያሜዎችን በመስጠት ሲጠሯቸው ይስተዋላሉ።

እንዲህ ባለ መልኩ ለዲያብሎስ ዳንኪራን ጥበብ ብሎ ማቅረብ ምንኛ ቀላል ነው? አሳፋሪ ስዕሎችንና ሐውልቶችን ሥነ-ጥበብ ብሎ መጥራትስ? በአንዳንድ ቴአትሮችና ሲኒማዎች ውስጥ የሚቀርቡት ትዕይንቶች ኃጢአትን የሚያበረታቱ ቢሆኑም እንኳ በጥበብ ስም ይጠራሉ። ሙዚቃም ክርስትናን የሚፈታተንና ጭንቀት ውስጥ የሚጥል ቢሆንም መጠሪያው ኪነ-ጥበብ ነው። በዚህ “ኪነ-ጥበብ” በሚል ስያሜ ሽፋን ሥር ዲያብሎስ ይህን ድንቅ ስም ሊይዙ የማይገባቸው በርካታ የኃጢአት ስብስቦችንና የማሰናከያ ድንጋዮችን እንዴት እንደሚሸሽግ አስተውል።

ዲያብሎስ “ንፍገት”ን በዚህ ስሙ የሚጠራው ይመስልሃልን? ማንም ስለማይቀበለው አይጠራውም። ይልቁንም “ጠንካራ ኢኮኖሚ” ፤ “ገንዘብን ለወደፊት መቆጠብ”፤“ገንዘብ አለማባከን” ወይም “በቅንጦት አለመኖር” በሚሉ ስያሜዎች ይቀይረዋል። ዲያብሎስ አንድ ባለጸጋ ሰው ለደሀው አንዳች እንዳይሰጠው ለመከልከል ከፈለገ እንዲህ በማለት ያማክረዋል። “ምጽዋት በመስጠት ልመናንና ጥገኝነትን አታበረታታ። ስለዚህ አለመስጠትህ “በፊትህ ወዝ ትበላለህ” (ዘፍ 3፡19) የሚለውን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ስለማይቃወም ሥራ ፈልገው በመስራት የራሳቸውን እንጀራ እንዲበሉ ያደርጋቸዋል” ይለዋል። “ለችግረኛና ለምስኪን የሚያስብ ምስጉን





ነው፤እግዚአብሔር በክፉ ቀን ያድነዋል፤ እግዚአብሔር ይጠብቀዋል ፤ ሕያውም ያደርገዋል ፤ በምድር ላይም ያመሰግነዋል ፤ በጠላቶቹም እጅ አያሳልፈውም ፤ እግዚአብሔር በደዌው አልጋ ሳለ ይረዳዋል ፤ መኝታውን ሁሉ በበሽታው ጊዜ ያነጥፍለታል።” (መዝ 40፡1-3) ያለውን ቃለ እግዚአብሔር ግን አያስታውሰውም።

ለኃጢአት የመልካም ምግባርን ስም መስጠት ደግሞ ሰዎች በኃጢአታቸው እንዲቀጥሉ ያበረታታቸዋል። እንዲህ ያለው ማታለል ሰዎች ስላለፈው በደላቸው ኅሊናቸው እንዳይወቅሳቸው ማድረግ ብቻ አይደለም በዚያው በቀደመው ኃጢአታቸው ወደፊትም እንዲገፉበት ያደርጋቸዋል። ዲያብሎስ የአርዮስን የመቅደንዮስንና የሰባልዮስን አስተሳሰብ ኑፋቄ በሚል ስያሜ ይጠራዋልን? አይጠራውም። ይልቁንም ኑፋቄአቸው ትክክለኛ ሃይማኖትን ለማስጠበቅና ለመከላከል የሚረዳ አስመስሎ ያሳምናቸዋል። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችንም በተዛባ መልኩ እንዲረዱ እንዲተረጉሙና እንዲቀበሉት ከማድረግ ባሻገር ሌሎችንም በተሳሳተ መንገድ እንዲያሳምኑበት ያደርጋቸዋል። ስለሆነም የማታለያ ስያሜዎች ላይ ጠንቀቅ በል! ምንም እንኳ ኃጢአት የተለያዩ ስያሜዎች ቢሰጡትም ያው ኃጢአት ነውና በዚህ ዲያብሎስ እንዳያታልልህ አስተውል!

2. ሌላ መልካም ምግባር ትይዛለህ በሚል ሰበብ የያዙትን ማስጣሉት።

የተፈጥሮ ባሕርይህ አካል እየሆኑ በመጡትና ቋሚ መልካም ምግባራትህ ዲያብሎስ በጣም ይናደዳል። ባገኘው አጋጣሚ ተጠቅሞም እነዚህን ቋሚና መልካም ምግባራትህን ሊያጠፋብህ ይጣጣራል። ይህን ለመፈጸም በጣም ቀላል መንገድ አድርጎ የሚወስደውም አዳዲስ መልካም ምግባራትን ለአንተ ማቅረብ ነው። ልምምድ ያላደረግህበትን አዲሱን መልካም ምግባር ያለ አድልዎ መፈጸም ከጀመርህ የመጀመሪያውንና ቋሚውን መልካም ምግባርህን ታጣለህ። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ከዚህ በመቀጠል እናያለን።

ሀ- በመጀመሪያ እስቲ ሕይወቱን በትህትና በጸጥታ በርጋታ በተሰበረ ልብና በግሩም ጠባይ እየመራ የቆየውን ሰው እንመልከት። ዲያብሎስ ይህ ሰው እነዚህን ባህርያቱን በሙሉ እንዲያጣ ለማድረግ ይፈልጋል። ምን ያደርጋል ታዲያ? በእርግጥ የሰውየውን ትህትና አይዘልፍም። ወይም ደግሞ “በሰዎች ሁሉ የሚወደደውን ይህ ትህትናህን ተወው” አይልም። ማድረግ የሚችለው ይህን ባህርይውን ከቦታው አናግቶ በሌላ መተካት ነው። ሌላ በጎ ምግባር ያመጣና የዚያኛው ምትክ መሆኑን ሳይገልጽ ይሰጠዋል። ግን እንዴት?

በመጀመሪያ ለሰውየው “የቤትህ ቅንዓት በልታኛለችና” ስለሚለው ጥቅስ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ይሰጠዋል። ይህ ጥቅስ የተነገረው በትህትናው በሚታወቀው በንጉሥ ዳዊት መሆኑንም ይገልጽለታል። መዝ 68፡9። ይህንኑ ቃል እጅግ በጣም ትሁት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ መቅደሱን ባጸዳ

ጊዜ ሐዋርያቱ ማስታወሳቸውን ይነግረዋል። "የገመድም ጅራፍ አበጅቶ ሁሉን በጎችንም በሬዎችንም ከመቅደሱ አወጣቸው ፤ የለዋጮችንም ገንዘብ አፈሰሰ ገበታዎቻቸውንም ገለበጠ . . ." ዮሐ 2፡15-17። በመቀጠልም "ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፏል ፤ እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት አላቸው።" (ማቴ 21፡13) ማለቱን ያሳሰበዋል። ከእነዚህ ጥቅሶች በተጨማሪ ሌሎች ተመሳሳይ ጥቅሶችን እያቀበለ ሰውየው የሌሎችን ስህተት እንዲዋጋ ያደርጋል። ከዚህ ሌላ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጻፎችና ፈሪሳውያንን በአንድ ምዕራፍ ሙሉ (ማቴ 23) ክፉኛ እንደ ዘለፋቸው ያስገነዝበዋል። "እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን" በማለት። ማቴ 23፡13፤14፤15፤23፤25፤27፤29። ከዚህ በተጨማሪ ስህተታቸውን በመግለጥና ከአንዴም ሁለት ጊዜ በላይ "ዕውሮች መሪዎች" በማለት ገስጾአቸዋል። "በውጪ አምረው የሚታዩ . . . በኖራ የተለሰኑ መቃብሮችን ስለምትመስሉ . . ." በማለትም ዘልፏቸዋል። ማቴ 23፡27። በመጨረሻም "እነሆ ቤታችሁ የተፈታ ሆኖ ይቀርላችኋል" ብሏቸዋል። ማቴ 23፡38 ዮሐንስ መጥምቅም የአይሁድን መሪዎች "እናንተ የእፉኝት ልጆች! ከሚመጣው ቁጣ እንድትሸሹ ማን አመለከታችሁ?" (ማቴ 3፡7) በማለት ዘለፏቸዋል።

እነዚህን ሁሉ ከገለጸለት በኋላ "ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በትዕዛዝ መልክ ያስተላለፈልንን ቃል አስተውል" ይለዋል። "ዝለፍና ገስጽ ምከርም" (2ኛ ጢሞ 4፡2) በማለት አዝዞሃል" ይለዋል። ይሁን እንጂ ይህንኑ ጥቅስ ሙሉ ለሙሉ አይጠቅስለትም። በተለይም "ፈጽመህ እየታገስህና እያስተማርህ" የሚለውን። ይህ ቃል የተነገረው ለኤፌሶኑ ጳጳስ ለቅዱስ ጢሞቴዎሰ መሆኑን አይገልጽለትም። ቅዱስ ጳውሎስ ራሱ በኤፌሶን የሚኖሩ ቀሳውስትን መገሰጹንም አይነግረውም። "ስለዚህ ሦስት ዓመት ሌሊትና ቀን በእንባ እያንዳንዳችሁን ከመገሰጽ እንዳላቋረጥሁ እያሰባችሁ ትጉ።" ሐዋ 20፡31 ከዚህ ሁሉ በኋላ ያ ትሁት ሰው ሌሎችን መዝለፍና መገሰጽ መቻሉን በማሳየት ይህን እንዳያደርግ ጫና ያሳድርበታል። ልክ ሰውየው ክርስቶስን ወይም መጥምቁ ዮሐንስን ወይም ቅዱስ ጳውሎስን አሊያም ጢሞቴዎስን የሆነ ይመስል።

ከዚህ ጊዜ አንስቶ ያ ምስኪን ሰው መንፈሳዊ ተግሳጽ እንዴት መቅረብ እንዳለበት ወይም ማን ማንን መገሰጽና መዝለፍ እንዳለበት ወይም የእርሱ ሥልጣን እስከ ምን መሆኑን ሳይገነዘብ ያገኘውን ሁሉ ይዘልፋል፤ይገስጻልም። ተግሣጹም በቁጣ በእርግማን በጭካኔና ሰዎችን በማዋረድ ይታጀባል። ሰዎች ሁሉ በእርሱ ዘንድ አጸያፊዎች ይሆናሉ። ምናልባትም በእርሱ ምክንያት ብዙዎች ቤተ ክርስቲያንን ትተው ይሄዳሉ። ቆይቶም ፍንጣሪውን በየቦታው የሚረጭ ፈንጂ ይሆናል። በዚህ ዓይነት መንገድ ትህትናውን ጨዋነቱንና ዝምታውን ያጣል። ሰዎችን ይጠላል፤በሰዎችም ይጠላል። ጥቂት ቆይቶም ይህ አዲስ ያመጣው ባህርይ ሙሉ በሙሉ ይታከተውና ወደ ቀደመው ባሕርይው ለመመለስ ይሞክራል። ነገር ግን አሁን የያዘው ልብ ቀድሞ ከነበረው ልብ፤አሁን ያለው





አስተሳሰብም ከበፊቱ ፍጹም የተለየ ሆኖ ያገኘዋል። በመጨረሻም ገራገርነቱን፤የልብና የኅሊና ንጽህናውን ከሌሎች ጋር የነበረውን መልካም ግንኙነትና በመልካም ምግባሩ ሌሎችን መጥቀም ማቆሙን ይገነዘባል። በዚህም ዲያብሎስ ጠንቅቆ በማያውቀው መልካም ምግባር ስም የቀደመ መልካምና ቋሚ ምግባሩን ያሳጣዋል። የመጀመሪያውን ሳይዝ ሁለተኛውንም ሳይጨብጥ በመካከል ግራ ተጋብቶ ይቀራል። ይሄኔም ሥር አለመስደዱ ዲያብሎስን ስለሚያናድደውና በቀላሉ ከእርሱ ሊቀማው ስለሚችል በሁለተኛው ምግባሩ እንዲቀጥል ይተወዋል። ለዚህም ነው የቀደሙት አባቶቻችን እኛ ልጆቻቸውን እንዲህ በማለት የመከሩን። "ዲያብሎስ የቀደመ መልካም ምግባርህን የሚያጠፋ ሌላ አዲስ ምግባር ቢያቀርብልህ 'አሁን ያቀረብክልኝ መልካም ምግባር መልካም ይሁን እንጂ እኔ አልፈልገውም' በማለት መልሰው።"

በእርግጥ አንዱ የእግዚአብሔር መልካም ሥራ ሌላውን አያጠፋውም። አንድ ሰው ግን ከሌላው ሰው የሚለየው የራሱ ባሕርይ አለው። ለአንዱ የሚሆነውም ለሌላው ላይሆነው ይችላል። ልክ እንደዚሁ ሁሉም ሰው የማስባሰብ የማደራጀት የመዝለፍ የመገሰጽ የመፍረድና የመርገም ሥልጣን የለውም። እንደዚህ ያለው ሥልጣን ከእግዚአብሔር የተሰጠው ቢሆን እንኳ ያለ አንዳች እንከን እንዴት ሊጠቀምባቸው እንደሚችልም አብሮ ይሰጠዋል። ሁሉም ሰው እንደ ቅዱስ ጳውሎስ "ወንጌልንም ባልሰብክ ወዮልኝ!" ይል ዘንድ አይችልም። ሐዋርያው ይህን ያለው ግዴታና አደራ ስለተጣለበት ነው። ". . . ግድ ደርሶብኝ ነውና።" ". . . መጋቢነት በአደራ ተሰጥቶኛል" 1ኛ ቆሮ 9፡16፤17። በአንተ ላይ የተጣለው አደራ ምንድርን ነው? ኢየሱስ ክርስቶስ ለቅዱስ ጳውሎስ የሰጠውን ጸጋ ወይም ለመጥምቁ ዮሐንስ አባት በመልአኩ ብሥራት ያደለውን ሥልጣን ወይም ደግሞ እንደ ቅዱስ ጢሞቴዎስ እጅ የመጫን ኃላፊነት የሰጠህ ማን ነው?

ለ- ከሥጋዊ ጉዳዮች ርቆ በልብ ንጽህና የሚኖረውን ደግሞ እንመልከት።

ይህ ሰው ራሱን ሙሉ ለሙሉ ከክፉ በመከልከል የሚኖር ሰው ነው። ሊያሰናክሉት የሚችሉ ጽሁፎችን እንኳ አያነብም። ሕግ የሚያስጥሱትን ትዕይንቶችም አይመለከትም። ሊያሰናክሉት ከሚችሉ ሰዎች ጋር አይቀራረብም፤ንግግራቸውንም አያዳምጥም። በዚህ መልኩ ኅሊናውን በንጽህና ይጠብቃል። የረከሰ ነገርም ወደ ልቦናው ዘልቆ አይገባም። ዲያብሎስ ይህን ንጹህ ሰው ሊዋጋውና ሊያሰናክለው ይፈልጋል። ነገር ግን ማሰናከያውን ፊት ለፊት በግልጽ አምጥቶ አያቀርብለትም ፤ ይቃወመዋልና። ምን ያደርጋል ታዲያ?

ዲያብሎስ ይህን ሰው ወጣቶችን ወደ ልብ ንጽህና የሚመራ መንፈሳዊ መምህር እንዲሆን በሩን ይከፍትለታል። ጠዋት ማታም እርሱ ብቻ በልብ ንጽህና መኖር እንደሌለበትና ለሌሎች ምስኪን ወንድሞቹ ከልብ ንጽህና ችግር ሊያወጣቸው የሚችለውን ምክር መለገስና ከጥፋት

እንዲድኑ ምክንያት መሆን እንዳለበት ይወተውተዋል። “ኃጢአተኛን ከተሳሳተበት መንገድ የሚመልሰው ነፍሱን ከሞት እንዲያድን የኃጢአትንም ብዛት እንዲሸፍን ይወቅ።” (ያዕ 5፡20) የሚለውን ጥቅስ እንዲያስተውልም ይጠቁመዋል። ወደ እርሱ የሚመጡትን ሁሉ ለመምራት እስኪወስንና አምኖ ይህን ታላቅ መንፈሳዊ አገልግሎት እስኪቀበለው ድረስ በውትወታው ይቀጥላል።

ከዚህ በኋላ ዲያብሎስ ወደሚቀጥለው ደረጃ ያሸጋግረዋል። አመራሩ በተግባር እንዲገለጥ ወደ እርሱ የሚመጡትንም ወጣቶች ችግሮቻቸውንና ስህተቶቻቸውን ማድመጥ እንደሚገባው ያሳስበዋል። ከዚያማ በቃ! ተራ በተራ እየመጡ እንዴት ወድቀው ንጽህናቸውን እንዳጡ የሚያወሱትን ወሬዎችና ወጎች በዝርዝር በመተረክ ጆሮዎቹን ይሞሉአቸዋል። ታሪኮቹ አሳፋሪ ቢሆኑም ይሰማል። በዚህም ይህ ወደ ንጽሐ ልቦና የሚመራ መምህር አስቀድሞ ሊያዳምጣቸው የማይወደውን ፣ ሲሸሻቸው የነበሩትንና እንዲሰማቸው ያልተፈቀዱለትን ጉዳዮች ሁሉ ማድመጥ ይጀምራል። አሁን ሁሉን በሚገባ ለማድመጥ ይፈቅዳል። ሁሉም እየመጣ አዳዲስና የተለያዩ የኃጢአት ዓይነቶችን በኅሊና ሰሌዳው ላይ ይስላል። ሌሎችን በመምራት ስም ይህ ወንድማችን ኅሊናው በረከሱ ስዕሎች ይጨናነቃል። የአእምሮውን ንጽህና የሚያሳጡትንና የሚያረክሱትን ወሬዎችና ወጎች ማወቅ ይጀምራል። “መናገር እንኳ ነውር ነውና” (ኤፌ 5፡12) የተባለላቸውን ሁሉ ሲነግሩት ይሰማል። እነዚህ ጉዳዮች በውስጡ የኃጢአትን ስሜት ባይቀሰቅሱበትና ባያሰናክሉትም እንኳ አእምሮውን ያረክሱበታል። መልካሙንና ክፉውን ከሚያሳውቀው ከእውቀት ዛፍ እንግዳ ፍሬዎችን ቀጥፏልና። ይህን አውቆ ለመሸሽ ቢሞክርም ዲያብሎስ “ወጣቶቹን የት ልትተዋቸው ነው?” ይለዋል።

ወጣቶቹም በአመራሩ ሰላም ያገኙ መሆናቸውንና ከእርሱ ባይለዩ ደስ እንደሚላቸው ይገልጹለታል። እርሱ ከተዋቸው ግን ወደ ቀደመው ኃጢአታቸው ሊመለሱ እንደሚችሉ በመግለጽ አእምሮውን የበለጠ ያስጨንቁታል። በሁለት እግራቸው እስኪቆሙ ድረስ እንዳይተዋቸው ይዘበዝቡታል። በዚህም ስለ ጻድቁ ሎጥ የተነገረው ቃል በእርሱም ሕይወት ይንጸባረቃል። “. . . ጻድቅ ሎጥም በመካከላቸው ሲኖር እያየና እየሰማ ዕለት ዕለት በአመፀኛ ሥራቸው ጻድቅ ነፍሱን አስጨንቆ ነበርና።” 2ኛ ጴጥ 2፡8። ወንድማችን አስቀድሞ ራሱን የሚያስጨንቀው በሚሰማው ብቻ ሲሆን አሁን ግን እነዚያ የሰማቸው ታሪኮች ከዚህ በፊት አይቶት በማያውቀው መልኩ በኅሊናው ላይ ተቀርጸውና በገሃድ የሚመለከታቸው ያህል ጥርት ብለው ሊታዩት ይጀምራሉ። በመጨረሻም ይህ ሰው በአስተሳሰቡም ሆነ በልቦናው ረክሶ ሊወድቅ ይችላል።

ይህ ወጣት ገና ከጅምሩ እንደነዚህ ያሉትን ወጣቶች ወደ ንስሐ አባቶቻቸው በመላክ ራሱን ከጭንቀት ነፃ ባወጣ ነበር። ነገር ግን ዲያብሎስ ጉዳዩን አስጀምሮ እርሱ በማያውቀውና መልካም ምግባር በሚመስለው መንገድ እንዲሰርጽበት ስላደረገው መተው ይሳነዋል። ምናልባት ግን





ወጣቶቹን ወደ መምህረ ንስሐ ለመላክ ይበቃ ይሆናል። ነገር ግን ብዛት ያላቸው ወሬዎችንና ወጎችን በአእምሮው በመቋጠሩና ኅሊናው በአዲስ እውቀት በመሞላቱ የቀደመ የአእምሮ ንጽህናውን ያጣል። “እውቀትንም የሚጨምር ኃዘንን ይጨምራልና” (መክ 1፡18) የሚለውን የጠቢቡ ሰሎሞንን አባባል እዚህ ላይ ልብ ይሏል።

ሐ. ሌሎችን በመምራት ውስጥ የዲያብሎስ ተንኮል ወሬዎችንና ወጎችን በማዳመጥ ልቦናን ማርከስ ብቻ ሳይሆን አእምሮ በጥርጣሬ እንዲዋዥቅ የማድረግ ዘዴም አለው። ለዚህ ዘዴው የሚጠቀምበት መሪ ሰው እንዲሁ በልቡ አምኖ መንፈሳዊ መጻሕፍትን የማያነብ ነገር ግን ራሱን ወደ እግዚአብሔር ያላስጠጋ ሰው ነው። ለዚህ ሰው አንድ ሌላ ሰው ጥርጥር ውስጥ ገብቶ በመጨነቅ ላይ መሆኑን በመግለጽ ምክር እንዲለግሰው ይጠይቀዋል። አንዱ ጥርጣሬ ሌላውን እያስከተለና በተለያየ አቅጣጫ መፍትሄ እየፈለገ የዚህ መሪ ሰው እምነት ከልቦናው ቀስ በቀስ እንዲያፈተልክና በአእምሮውና በሳይንሳዊ ምርምሮች መታመን እንዲጀምር ያደርገዋል። እምነትን ከሳይንስ ሳይደባልቁ የሚገዙ ጥቂቶች ናቸው። ይህ ሰው ግን የማስረዳት ችሎታው ስለሌለው የጥርጣሬው ማዕበል እያስጠመው ይሄዳል።

ማንኛውም ሰው አመራር የመስጠት ብቃት እንደሌለው ልናውቅ ይገባል። ይህ ብቃት ያላቸው አባቶች መንፈሳዊ ችግሮችን በማየት አጸያፊ ኃጢአቶችን በማድመጥና ጥርጥርን በመስማት አይናወጡም። ስለሆነም ዲያብሎስ ብልህ በመሆኑ የመሪነትን ቦታ ይህ ብቃት ለሌላቸው ሰዎች በማሳየት እንዲጎዱበት ያደርጋል። ዲያብሎስ ይህን አገልግሎት ለእነዚህ ብቃቱ ለሌላቸው ሰዎች የሚያመለክተው እጅግ በጣም አንገብጋቢና አስቸኳይ መንፈሳዊ አገልግሎት እንደሆነ አድርጎ በማጣደፍ ነው። “እንግዲህ በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሠራው ኃጢአት ነው።” (ያዕ 4፡17) የሚለውን ይጠቅሳል።

እዚህ ላይ ግን ትሁት የሆነው ሰው እንዲህ ዓይነቱ ውጊያ ሲከፈትበት በትህትናና በተሰበረ ልብ “እኔ ይህን ጉዳይ አላውቅም . . . እኔ እንኳን ሌሎችን ሊመራ ራሴን መምራት አልችልም” በማለት መመለስ ለእርሱ ቀላል ነው። ይሁን እንጂ ዲያብሎስ አንድ መንፈሳዊ ሥራ የሚያመጣውን ውጤት በሌላ መንፈሳዊ ሥራ ማጥፋት ያውቅበታል። በጣም በተመስጦ ሆኖ ለፈጣሪው ጸሎት የሚያደርስን ሰው ዲያብሎስ አንድ ሰው ወደ እርሱ በመላክ ንትርክ የፈጠሩ ሰዎችን እንዲያስማማ ያስጠራዋል። እነርሱን ለማስታረቅ ተቀመጠ ጫጫታውን፣ ጭቅጭቁን፣አጸያፊ ዘለፋውንና ስድቡን ሲያዳምጥ የተመስጠውና የጸሎቱ ውጤት ከእርሱ ይርቃል። ይህ ሰው ታዲያ ወደ ቤቱ ሲመለስ ያን የተጋጋለ ንትርክ ይዞ ስለሚመለስ ኅሊናው ለጸሎት አይታዘዘለትም። አንተ ግን በእግዚአብሔር ፊት ለጸሎት ለመቆም ለየት ያለ ዝግጅት እንደሚያስፈልግ አትዘንጋ።

ዲያብሎስ ጸሎትህ በተመስጦ የተሞላ ሆኖ ሲመለከት ሊረብሽህ ይወዳል። እንዴት? አንተ በተመስጦ ስትጸልይ "እንዲህ ያለው ጥልቅ ተመስጦ በጣም ጥሩ ነው። ሌሎች ቢያውቁት ደግሞ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ስለዚህ እንዳትዘነጋው አሁኑኑ ተነሣና በወረቀት ላይ በጽሑፍ አስፍረው" ይልሃል። በዚህም ከጸሎት ወደ ጽህፈት ሥራ ያሸጋግርሃል። በእግዚአብሔር ፊት በተመስጦ መቆምህንም አስጥሎ እንድትቀመጥ፤ እንድትጽፍና በእግዚአብሔር ፊት በመቆምህ ከመደሰት ይልቅ በሌሎች እንድትደሰት ያደርግሃል። ዋናው የዲያብሎስ ዓላማ የያዝከውን እንድትጥልና በሌለህ እንድትደሰት ማድረግ ነው። አሊያም ሌላ ታገኛለህ በሚል ከንቱ ተስፋ በእጅህ ያለውን ጥለህ የማታገኘውን ለመያዝ እንድትተጋ ማባከን ነው። አሊያም ደግሞ አንዳንድ መልካም ምግባራትን ለጊዜው ያሳይህና ኋላ ይቀማሃል።

3. መልካም ምግባራትን ያለቦታቸው እንዲጠቀሙ ማድረግ።

መጽሐፍ ቅዱስ "ለሁሉ ዘመን አለው፤ከሰማይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው" ይላል። መክ 3፡1። መልካም ምግባራትን ያለ ጊዜያቸውና ያለ ቦታቸው ከተጠቀምንባቸው ከመንፈሳዊ ጠቀሜታቸው ይልቅ ጥፋታቸው የጎላ ይሆናል። በዚህ መልኩ ከሚዋቀሩት የዲያብሎስ ደባዎች መካከል ጥቂቶቹን ከዚህ በመቀጠል እንመለከታለን።

ስለ ኃጢአታችን ማሰብ በሚጠበቅብን በንስሐ ወቅት የደስታን መልካም ምግባራት እንድናስላስል ያደርጋል። በዚህ ወቅት ከደስታ ጋር የሚዛመዱ ጥቅሶችን በማስታወስ በንስሐ ሕይወት እንድንቀጥል የሚያስፈልጉንን እንደ ጸጸትና እንባ የመሳሰሉትን ያጠፋብናል። "የሚያዝኑ ብጹዓን ናቸው፤መጽናናትን ያገኛሉና" (ማቴ 5፡4) የሚለውን ጥቅስም ይሰውርብናል። በዚህ መልኩ ዲያብሎስ አንድ ሐረግ ብቻ መዝዞ የመጠቀም ዘዴውን ተግባራዊ ያደርጋል። እንዲህ ያለ ዘዴውን ጌታችን አልተቀበለውም። ዲያብሎስ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ". . . ተብሎ ተጽፎአልና" ብሎ ሲፈትነው ". . . ተብሎ ደግሞ ተጽፏል" በማለት መልሶለታል። ማቴ 4፡6-7። በዚህም ዲያብሎስ አንድ ሐረግ ጥቅስ በመምዘዝ ያንን ሐረግ የሚያብራሩ ሌሎች ጥቅሶችን እንደሌሉ አድርጎ ሲያቀርብልን በዚያ ተመርተን ስህተት ላይ እንዳንወድቅ ጌታችን አስተምሮናል።

ከዚህ በተጨማሪ ዲያብሎስ የእርሱን ዓላማ የሚያሳኩ ሌሎች ብዛት ያላቸው ጥቅሶችን ሊጠቅስልን ይችላል። ጽናትና ቅጣት በሚያስፈልግበት ቦታ ምህረት ማድረግን ሊጠቅስ ይችላል። በአንጻሩ ምህረት ርኅራኄና ይቅርታ ሊደረግ በሚገባበት ቦታ ስለ ቅጣት የሚነገሩትን ጥቅሶች ሊያሳስበን ይነሳል። ዝምታ በሚመረጥበት ቦታ ላይም ስለ መናገር ጥቅም የሚያወሱ ጥቅሶችን ያስታውሳል። ለሌሎች የሚስማሙ (የተጠቀሱ) ጥቅሶችንም ለእርሱ እንደ ተጠቀሱ አድርጎ ማቅረብ ሌላው የዲያብሎስ ዘዴ ነው። ለምሳሌ ካህናትና ሐዋርያትን የሚመለከቱን ጥቅሶች ለአንዱ ምዕመን የተጠቀሱ





አስመስሎ በማቅረብ ይዋጋል። ጌታ ሐዋርያቱን "በምድር ላይ ማንንም አባት ብላችሁ አትጥሩ" ያላቸውን ለእርሱ (ለምዕመኑ) የተጠቀሰ አድርጎ ያቀርብለታል።

ሌላው ምሳሌ ደግሞ ጥፋትን በተመለከተ ቁጥር ያንን ጥፋተኛ ሰው ከፉኛ የሚማታውን ቁጡ ሰው ይመለከታል። ይህ ሰው ይህን አላስፈላጊ እርምጃ እንዲወስድ የገፋፋው "ዓመፃ የሚያደርጉትን ሁሉ ከእግዚአብሔር ከተማ አጠፋቸው ዘንድ ፤ የምድርን ኃጢአተኞች ሁሉ በማለዳ እገድላቸዋለሁ።" (መዝ 100፡8) የሚለውን ጥቅስ ዲያብሎስ በአእምሮው ውስጥ ስለቀረጸበት ነው።

4. ጥርጣሬን መትከል።

ተጠራጣሪ ሰው ደካማና በቀላሉ እጁን ለዲያብሎስ የሚሰጥ ስለሆነ ባላጋራችን ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ጥርጣሬን ይዘራብታል። ለምሳሌ ንስሐን አስመልክቶ ተነሳሒ መሆን በመቻልና በእግዚአብሔር ዘንድ ንስሐው ተቀባይነት በማግኘቱ መካከል ጥርጣሬን ይዘራል። እንደ ልምድ ይዞት በመቆየቱ ከባሕርያቱ አንዱ የሆነውን ኃጢአት ማስወገድ ቀላል አለመሆኑን ከገለጸለት በኋላ ይህን የሚወደውን የኃጢአት ተግባሩን ከተወ መኖር እንደማይችል አድርጎ ያሳየዋል። ብቃቱን አስመልክቶ የእግዚአብሔርን ረዳትነት በመሸሸግ በጥርጣሬ ይሞላዋል። እንዲህ የሚለውን የነቢዩንም ቃል ይሰውርበታል። "አቤቱ የሚያስጨንቁኝ ምንኛ በዙ! በእኔ ላይ የሚቆሙት ብዙ ናቸው። ብዙ ሰዎች ነፍሴን አምላክሽ አያድንሽም አልዋት" መዝ 3፡1-2።

ተነሳሒው ንስሐ በመግባቱ የሚገፋበት መስሎ ከታየውም ኃጢአቱን በወቅቱ መናዘዝ ይገባው እንደነበር ወይም ውሸት መሆኑን ወይም እግዚአብሔር ንስሐውን እንደማይቀበለው ወይም ደግሞ ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ኃይለኛ ቅጣት የሚያስጠው ኃጢአት በመሆኑ በቀላሉ ሊማር እንደማይችል አድርጎ እንዲጠራጠር ያደርገዋል። የዲያብሎስ ዋነኛ ዓላማ ተነሳሒውን ተስፋ ማስቆረጥ ነው።

ይህም ልቦናውን አጥቶ በኃጢአቱ እንዲቀጥል ያደርገዋል። ከዚህ ሌላ እግዚአብሔር ቀደም ሲል የሰጣቸውን ብዛት ያላቸው ፍርዶችና ቅጣቶች በመጥቀስ ሰውየው የእግዚአብሔርን መሐሪነት እንዲጠራጠር ያደርገዋል። ምናልባትም እግዚአብሔር እነዚህን ቅጣቶች ያወረደው ከእርሱ የሚቀል ኃጢአት በሠሩት ላይ እንደሆነ አድርጎ ያሳስበዋል። ሰይጣን የጥርጥር እሾሁን በሰዎች የግል ሕይወት ውስጥም ሊተክል ይችላል። ድንግልና ወይስ ጋብቻ? የትኛው ይመረጣል? የሚለውን አስመልክቶ ጥርጥርን ይተክላል። ከዚህ በኋላም ሰውየው የመረጠውን መንገድ እንደገና እንዲጠራጠር ያደርገዋል። ሰውየው ምንኩስናን ከመረጠ ይህን ሕይወት መምራት መቻልና አለመቻሉን ይህ ለተመረጡት ብቻ የተሰጠ መሆኑን

በመጥቀስ እጅግ በጣም ከባድ እንደሆነ አድርጎ ያጠራጥረዋል። “ይህ ነገር ለተሰጣቸው ነው እንጂ ለሁሉ አይደለም።” ማቴ 19፡11 “. . . እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ለራሱ የጸጋ ስጦታ አለው” 1ኛ ቆሮ 7፡7።

በመቀጠልም “ይህ ለአንተ የተሰጠ የጸጋ ስጦታ መሆኑን በምን አወቅህ?” በማለት ይጠይቀውና አስቀደሞ የወደቁ የቅዱሳን አባቶችን በመጥራት “የእግዚአብሔር መንፈስ ካደረባቸው ከዳዊትና ከሰሞሶን አንተ በምን ትበልጣለህ?” ይለዋል።

በአንጻሩ ሰውየው ጋብቻን ከመረጠ ዲያብሎስ “የድንግልናን አክሊል አጣህ” ይለዋል። ከዚያም አስከትሎ የቅዱስ ጳውሎስን ቃል ይጠቅስለታል። “ያላገባው ጌታን እንዴት ደስ እንዲያሰኘው የጌታን ነገር ያስባል ፤ ያገባው ግን ሚስቱን እንዴት ደስ እንዲያሰኛት የዓለምን ነገር ያስባል” “ያላገባም የተሻለ አደረገ” 1ኛ ቆሮ 7፡32፤33፤38። በመጨረሻም የቱን መምረጥ እንደሚገባው መወሰን እስኪያቅተው ድረስ አጠራጥሮ ይተወዋል።

ዲያብሎስ በአገልግሎት ወይም በበዓት ተወስኖ በመኖር መካከልም ጥርጥርን ይዘራል። አንድ ሰው በበዓት ተወስኖ መኖርን ከመረጠ ዲያብሎስ የአገልግሎትን ታላቅነት ከቀደሙት የእምነት ጀግኖችና ሐዋርያት ሕይወት በመጥቀስ ይገልጽለታል። “ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ” ዳን 12፡3። “መብራትንም አብርተው ከዕንቅብ በታች አይደለም እንጂ በመቅረዙ ላይ ያኖሩታል፤በቤት ላሉትም ሁሉ ያበራል። መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ” ማቴ 5፡15-16።

በአንጻሩ ሰውየው አገልግሎትን ከመረጠ “በምድር ያሉ መላእክትን ሕይወት አጣህ ፤ ሰው ለእግዚአብሔር ብቻ ሊያቀርባቸው የሚችላቸውን ጸጥታንና ርጋታን አጣህ። ኢየሱስ ክርስቶስ “ . . . በብዙ ነገር ትጨነቂያለሽ ፤ ትታወኪማለሽ” (ሉቃ 10፡41-42) በማለት ማርታን የገሰጸበትን መንገድ መረጥህ እንጂ እንደ ማርያም ከጌታ እግር ሥር ተቀምጠ መማር የሚያስችለውን መልካም ዕድል አልመረጥህም” ይለዋል። ይህ ዓይነቱን የዲያብሎስ ውጊያ አንድ ቅዱስ አባት እንዲህ በማለት ገልጾታል። “ዲያብሎስ በተባህትዎ የሚኖረውን መነኩስ ወንድሞችን በማገልገል ፍቅር ይዋጋዋል። ወንድሞችን በማገልገል የሚኖረውን መነኩስ ደግሞ በጸጥታ፤በጸሎትና በተመስጠ ፍቅር ይዋጋዋል።”

ዲያብሎስ በሌላ በኩል ጥርጥሩን በማኅበራዊ ግንኙነቶች ውስጥም ይዘራል። በባልና ሚስት፣በጓደኞሞች፣በሥራ ባልደረቦች፣ በአለቃና በበታች ሠራተኞች መካከል ጥርጥሩን ይተክላል። አንደኛው ሰው ሌላው ሰው ለእርሱ ያለውን ፍቅር ታማኝነትና ሀቀኝነት እንዲጠራጠር ያደርጋል። ሰዎች ባሕርያቸውን ውጥናቸውንና ዓላማቸውን እንዲጠራጠሩም ያደርጋል። ዲያብሎስ ይህን የሚያደርገው በሰዎች መካከል ያለውንና መንፈሳዊውም ሆነ





ማኅበራዊው ሕይወት የተመሠረተበትን ፍቅር በማጥፋት ወደ ጠብና ክርክር መምራት ስለሚፈልግ ነው። በጣም ቀላል የሆኑትንና ያለ ችግር ሊታለፉ የሚችሉትን አጋጣሚዎች ሰይጣን በተለያዩ ጥርጣሬዎች በማጀብ ውስብስብ አድርጎ ያቀርባቸዋል።

እንዲሁ ዲያብሎስ በእምነት ላይም ጥርጥርን ይዘራል። ዛሬ ሰዎችን የሚያማቅቁበት ኑፋቄና ቀጥተኛ ያልሆነ የመናፍቃን ትምህርት የመነጨው ከዲያብሎስ ጎሊና ነው። የተለያዩ የሃይማኖት ድርጅቶችና በመካከላቸው ያለው ቅራኔ አልፎ ተርፎም እስከ ክሂደተ እግዚአብሔር የሚያደርሰው እምነት ሳይቀር በዲያብሎስ የተፈጠሩ ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪ ዲያብሎስ ከእግዚአብሔር ጋር መኖር እንደማይቻል አድርጎ ጥርጥርን ሊዘራ ይችላል። በቀጭኗ መንገድና በጠባቧ በር ማንም ሊገባ እንደማይችል በማጠራጠር የክርስትና ሕይወት ከባድና አስቸጋሪ መሆኑን ይገልጻል። ማቴ 7፡13-14። እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቀው የፍጽምና ደረጃ ላይስ ማን ይደርሳል? ይላል። ማቴ 5፡48። በመጨረሻም የርኩሳን መናፍስትን ውጊያስ ማን ሊያመልጥ ይችላል? በማለት ያጠራጥራል። በዚህ ሁሉ መካከል ግን ለሰዎች የሚሆነውንና ማለቂያ የሌለውን የእግዚአብሔርን እርዳታ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋና ሥራ ይሸሽጋል።

እንደዚሁ ዲያብሎስ ተነሳሒው የንስሐ አባቱን እንዲጠራጠር ያደርገዋል። የንስሐ አባቱ ስለ እርሱ ያለውን ትኩረትና ፍቅር እንዲሁም ምሥጢር መጠበቅ አለመጠበቁን አስመልክቶ ተነሳሒውን ያጠራጥረዋል። የንስሐ አባቱ የሚሰጠው ቀኖና ትክክልና አሁን እርሱ ባለበት መንፈሳዊ ደረጃ የሚመጥን መሆን አለመሆኑ ላይም ጥርጣሬን በኅሊናው ይከታል። እውቀቱንና መንፈሳዊነቱንም እንዲጠራጠር ያደርገዋል። የዲያብሎስ ዋናው ፍላጎት የተቻለውን መንገድ ሁሉ ተጠቅሞ ታዳኙን ከንስሐ አባቱ መለየት ነው። ምክንያቱም ከተናዘዘ የአጋንንትን ውጊያዎች፣ ደባዎቻቸውንና ተንኮላቸውን መምህረ ንስሐው ስለሚያጋልጥ ነው። ዲያብሎስ ይህን ሁሉ የጥርጥር መንፈስ በተነሳሒው ልቦና የሚዘራው የንስሐ አባቱን ተጠራጥሮ እንዳያምነው፤ኃጢአቱን እንዲሸሽግና በመጨረሻም ትቶት እንዲሄድ ነው። ከዚህ ሁሉ በላይ የሚያስደንቀው ደግሞ “ለምን እንደ አንተ ላለ ሰው ኃጢአትህን ትናዘዛለህ?” በማለት ምሥጢረ ንስሐን እንዲጠራጠር ማድረጉ ነው።

ዲያብሎስ መልካም ምግባርንም እንድንጠራጠር ያደርጋል። ለምሳሌ “ትህትናና ራስን ማዋረድ ማንነትን ከማዳከም በስተቀር ምን ይፈይዳል? መብትህን በኃይልህም ቢሆን ማስከበር ስትችል ሌሎች ሲያታልሉህና ሲያጭበረብሩህ መመልከትህ ምን ይባላል?” ይልሃል። ልክ እንደዚሁ ከሌሎቹም መልካም ምግባራት እንድትርቅ የጥርጥር መርዙን ይረጭብሃል። አንተ ግን እንደነዚህ ያሉ ጥርጥሮችን አትቀበል። ጥርጥር ባደረብህ ጊዜ ሁሉ “ይህ የዲያብሎስ ሥራ ነው” በል።

ጥርጣሬን ሁሉ በውስጥህ አትቀበል። ተጠራጣሪም አትሁን። ጥርጣሬህም አይቀጥል። ስለ ጥርጣሬህ መወያየት ከቻልህ አድርገውና ስህተት መሆኑን አረጋግጥ። አለበለዚያም እግዚአብሔር ጥርጥርን ሁሉ ከአንተ ያርቅልህ ዘንድ ወደ እርሱ ጸልይ። " . . . የምትደላደሉ የማትነቃነቁም ሁኑ" (1ኛ ቆሮ 15:58) የሚለውንም የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አስብ።

5. ተስፋ ማስቆረጥ።

ዲያብሎስ ተስፋ ከማስቆረጡ አስቀድሞ ረዘም ያለ የዝግጅት መግቢያ ይሰጣል። እነዚህ ዝግጅቶች ለተከታታይ ውድቀቶች በመዳረግ ታዳኙ በመጨረሻ "እኔ ተስፋ የለኝም። እንዲህ ዓይነት ሰው ስለሆንኩ እድን ዘንድ አልችልም።" በማለት እስከ መጮህ የሚያደርሱት ናቸው።

እነዚህ ቅደመ ዝግጅቶች ትህትናን አስመልክቶ ያለ ማቋረጥ በሚያጠምደው ሰው ልቡና ውስጥ የሚያስቀምጣቸው ክፉ አሳቦቹ ሊሆኑም ይችላሉ። በየዕለቱ "እኔ ደካማ ረዳት የሌለኝና በኃጢአት የተሞላሁ ነኝ።" እንዲል ያደርገዋል። እንዲህ በማለቱም ወደ ትህትና ከመሄድ ይልቅ በመንፈሱ ይደክምና ከወደቀበት ሊነሣ የማይችልበት ደረጃ ላይ የደረሰ ይመስለዋል።

ተስፋ የማስቆረጥ ውጊያ ጅምር ልክ እንደ ይሁዳ በታላቅ አወዳደቅ ሊጠቃለል ይችላል። ዲያብሎስ በዚህ ውጊያው ለተሠራው ኃጢአት ምንም ዓይነት ይቅርታ ሊደረግ እንደማይችል አድርጎ ያሳያል። ዲያብሎስ ጥቃቅን ስህተቶችን በማጉላት እነዚህን ስህተቶችን የፈጸማቸውን ሰው ተስፋ በማስቆረጥ ይጥለዋል። በዚህ ረገድ ዲያብሎስ ጮሌ ነው። ይህ ሰው ከመውደቁ አስቀድሞ የሠራው ኃጢአት በጣም ቀላል መስሎ ይታየዋል። ዲያብሎስም ይህንኑ ያረጋግጥለታል። ያን ኃጢአት ከፈጸመው በኋላ ግን ዲያብሎስ ቀላል መሆኑን ድጋሚ በመግለጽ ያንኑ ኃጢአት ደጋግሞ እንዲፈጽመው ያበረታዋል። አሊያም እጅግ አጉልቶና የከፋ አድርጎ በማሳየት ሰውየውን ወደ ተስፋ መቁረጥ ይመራዋል። "እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን ኃጢአት ይቅር የሚል ይመስልሃል?" በማለት። በዚህ ጊዜ ይህ ኃጢአተኛ መንፈስ ቅዱስን እንደተቃወመ ይሰማዋል። የሠራው ኃጢአት መንፈስ ቅዱስን ከመሳደብ ጋር ምንም ግንኙነት ባይኖረውም እንዳለው አድርጎ ስለሚገምት ይቅርታን የሚያገኝ አይመስለውም። ማር 3:29። በዚህም መንፈስ ቅዱስ ከልቡናው ሙሉ ለሙሉ እንዲወጣ ያደረጋል። በመጨረሻም ለዚህ ሰው ወደ ንስሐ መመለስ ያዳግተዋል፤ይቅርታንም ያጣል። ምክንያቱም ለኃጢአት ስርየት ንስሐ፤ ለንስሐም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በልቡናው ውስጥ መኖር አለበትና ነው።





ዲያብሎስ ንስሐ መግባት እንደማይችል አድርጎ ወደ ተስፋ መቁረጥ ሊመራ ይችላል፤እንዲህ በማለት "ኃጢአትን መተው ትችላለህን? አትችልም። ኃጢአት ከደምህ ጋር ተዋህዷል ጽናትህ አብቅቶለታል፤ ተስፋህ ተሟጧል፤ንስሐ የመግባት ምኞቱ እንኳ በውስጥህ የለም። ምን ያህል ጊዜ ነው ንስሐ ለመግባት ሞክረህ ያቃተህ? ምን ያህል ጊዜስ ኃጢአትህን ከተናዘዝህ በኋላ ተመልሰህ ከፊተኛው የከፉ ኃጢአቶችን የፈጸምከው?" እንዲህ እንዲህ እያለ ሰውየው ውጊያውን መቋቋም አቅቶት እስኪወድቅ ድረስ ይሞግተዋል። በመጨረሻም "አሁን ሙሉ ለሙሉ እጄ ላይ ወድቀሃል። ከአሁን በኋላ ወደምፈልገው የእጄ መዳፍ አገላብጥሃለሁ። ስለሆነም ምንም ውጤት የማታገኝበትን ትግል መታገልህ ለከንቱ ነው።" ይለዋል።

በእርግጥ እነዚህ ሁሉ ማስፈራሪያዎች መሠረት የሌላቸውና የሐሰት ዛቻዎች ናቸው። አንድ ሰው ምንም እንኳ ያለበት ሁኔታ በጣም የከፋ ቢሆንም እግዚአብሔር ንስሐውን ይቀበላል። ብዙ ታላላቅ የሚባሉ ቅዱሳን አባቶች የከፋ በደል ቢሠሩም እንኳ እግዚአብሔር ይቅር ብሏቸዋል። ነገር ግን ዲያብሎስ ሰዎች በኃጢአት ሲወድቁ ጥረቱ ሁሉ ወደ ተስፋ መቁረጥ እንዲደርሱ ነው። ውደቀቱ ጊዜያዊ ሳይሆን ቋሚና ዘላለማዊ እንደሆነ አድርጎ ነው የሚያሳምነው። በነቢዩ ሚክያስ የትንቢት መጽሐፍ ላይ የተጠቀሱት ቃላት ምንኛ ድንቅና አጽናኝ ናቸው! "ጠላቴ ሆይ፡ ብወድቅ እነሳለሁና ፤ በጨለማም ብቀመጥ እግዚአብሔር ብርሃን ይሆንልኛልና በእኔ ላይ ደስ አይበልሽ።" ሚክ 7:8። ከዚህ በተጨማሪም "ጻድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃልና፤ይነሣማል።" ምሳ 24:16። ሰው ተደጋጋሚ ውድቀት ቢወድቅም መጽሐፍ ቅዱስ ጻድቅ ብሎ ነው የጠራው። ።

ተስፋ ወደ መቁረጥ ከሚያደርሱን ምክንያቶች አንዱ ዲያብሎስ በመንፈሳዊ ክፍለ ጊዜያችን የሚሰነዝርብን ጥቃት ነው። እንዲህ ያለው የኀላ የዲያብሎስ ደባ በብዙዎች ዘንድ ይታወቃል። እስቲ ይህን ደባውን በምሳሌ እንመልከት። በአዲስ ዓመት ዋዜማ የተባረከ ዘመን ለመቀበል በማሰብ ምሽቱን በመዝሙር በማኅሌትና በጸሎት ለማሳለፍ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ታድራለህ። ሲነጋጋም ቅዳሴ አስቀድስህና ቅዱስ ቁርባን ተቀብለህ ወደ ቤትህ ታመራለህ። በመንገድ ላይ ሳለህ ዲያብሎስ አንድ ነገረኛ ሰው ይልክብህና ይተናኮልሃል። በዚህ ጊዜ ትበሳጭና ትበድላለህ። ከዚህ በኋላ ተስፋ የማስቆረጥ ክብሪቱን ይጭርበሃል። "ይህን ሁሉ ካደረግሁ በኋላ እንዴት እሰናከላለሁ? በቃ ምንም ዋጋ የለኝም" ትላለህ። ነገር ግን ተስፋ አትቁረጥ። ይህ የተነቃበት ማታለያ ነውና። ከነቢዩ ጋር ሆነህ "ብወድቅም እነሳለሁ" በል። ዲያብሎስ ውጊያውን በዚህ እንደማይገታም እወቅ። በማንኛውም የአዲስ ዓመት የመጀመሪያ ቀን ፤ በመንፈሳዊ በዓላት ቀን ፤ በጾም መጀመሪያ ቀን ፤ መንፈሳዊ ጸሎት ካደረስክና ቅዱስ ቁርባን ከተቀበልህ በኋላ ዲያብሎስ አንተን ለመጣል ክንዱን እንደሚሰነዝር አትዘንጋ። እንዲህ በሚቃጣበት ጊዜም "ማታለያ ዘዴህን አውቄብሃለሁ ፤ ሌላ ዘዴ ፈልግ" ትለዋለህ። በመንፈሳዊ ክፍለ ጊዜዎችህ በምታሳየው

መንፈሳዊ ጥረትና ውጤት ዲያብሎስ ተራ ቅናትን ስለሚቀና የሚከፍትብህ ውጊያዎች ስፍር ቁጥር የላቸውም።

ሌላው የዲያብሎስ ተስፋ ማስቆረጫ መንገድ ሰውየው ሊያገኘው የማይችለውን ከፍተኛ ደረጃ እንደሚያገኘው አድርጎ ማጓጓት ነው። ባለው ኃይል ሁሉ ሊያገኘው የማይችለውን ከፍተኛ መንፈሳዊ የዕድገት ደረጃ እንደሚያገኘው አድርጎ ያሳምነዋል። ይህን የተመለከቱ የንስሐ አባቱ ረጋ ማለት እንዳለበትና አሁን ባለበት ደረጃ ጥቂት መቆየት እንዳለበት ሲመክሩት ዲያብሎስ የንስሐ አባቱን መንፈሳዊነት እንዲጠራጠር ያደርገዋል። አንድ ሰው በጣም ጥሩ መሠረት ከሌለው እንዴት አድርጎ ነው አንድ ወይም ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ቀናት በከፍተኛ መንፈሳዊ የዕድገት ደረጃ ላይ መቆየት የሚችለው? አይችልም። ስለሆነም ይወድቃል። በዚህ ጊዜ ዲያብሎስ ጠጋ ብሎ ሊወቅሰውና ተስፋ ሊያስቆርጠው ይጀምራል። "ለመንፈሳዊ ሕይወት ብቃት የለህም። ባሕርይህ ከመንፈሳዊው ሕይወት ጋር አይጣጣምም" ይለዋል። እንዲህ እንዲህ እያለ አድቅቆ ይጥለዋል። ነገር ግን ያ ሰው እንደ መምህረ ንስሐው ምክር ዕድገቱን ቀስ በቀስ ቢያደርግ ኖሮ ዲያብሎስ እንዲጀምረው የሰጠውን ደረጃ በመጨረሻ ያገኘው ነበር።

ዲያብሎስ ጻፎችና ፈሪሳውያንን የእርሱን ጠባይ ጠባያቸው እንዲያደርጉ አሳምኖአቸው ነበር። መንፈሳዊ መመሪያን በመስጠት ረገድ "ከባድና አስቸጋሪ ሸክም ተብትበው በሰው ትከሻ ይጭናሉ ፤ እነርሱ ግን በጣታቸው ስንኳ ሊነኩት አይወዱም።" (ማቴ 23፡4) ተብሎ ተጽፎባቸዋል። እነዚህ ከባድ ሸክሞች አንዳንድ ጊዜ የሚሸከማቸውን ሰው ተስፋ የሚያስቆርጡት ይሆኑና "ይህን ማን ይችላል? ማንስ ሊድን ይችላል?" በማለት ይናገራል። ከአሕዛብ ወገን ወደ እምነት ስለመጡት ግን ሐዋርያት እንዲህ ነበር ያሉት "ከአሕዛብ ወደ እግዚአብሔር የዞሩትን እንዳናስቸግራቸው" ሐዋ 15፡19። የላኩባቸውም መልዕክት ይህንኑ የመሰለ ነው። " . . . ከሚያስፈልገው በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናል።" ሐዋ 15፡28። ቅዱስ ጳውሎስም እንዲህ ብሏል። "ገና ጽኑ መብል ለመብላት አትችሉም ነበርና ወተት ጋትኋችሁ ፤ ገና ሥጋውያን ናችሁና እስከ አሁን ድረስ ገና አትችሉም።" 1ኛ ቆሮ 3፡2 ስለሆነም ዲያብሎስ ከደረጃችሁ በላይ በሆነ ነገር ቢፈትናችሁ አትስሙት። ይልቁንም "አንተ ሰይጣን ከአጠገቤ ወግድ። ለእኔ መልካም አታስብልኝምና። አንተ ያሉህ ወደ መልካም ፍጻሜ የማያደርሱ የራስህ የሆኑ ጠማማ መንገዶች ናቸው።" በለው። በአንድ ወቅት ዲያብሎስ አንዱን ጻድቅ አባት ተነስቶ እንዲጸልይ ሲቀሰቅሰው "እኔ በወደድሁ ሰዓት እጸልያለሁ እንጂ አንተ የምትለውን አልሰማም" በማለት አሳፍሮታል። ሰይጣን ሰውን ለመጣል ሲፈልግ ወደ ላይ ከፍ ያደርገዋል። ከጣለው በኋላ ደግሞ ክፉ በማሳሰብ ተስፋ ያስቆርጠዋል። ተስፋ የማስቆረጥ ውጊያ ዲያብሎስ የሚወደው ውጊያ ነው። ምክንያቱም ሰው ተስፋ ሲቆርጥ በራሱም ሆነ በእግዚአብሔር ላይ እምነት ያጣል። መንፈሳዊ ሕይወት መምራት የሚችልባቸው አማራጮች ላይም ስለማይተማመን ለውድቀት ራሱን





ያጋልጣል። ዲያብሎስ የሚፈልገውም ይህንኑ ነው ፤ ታዳኙ እንዳይታገለው አድርጎ መጣል።

በእንዲህ ዓይነት መልኩ የጣለውን ሰው ዲያብሎስ በመጨረሻ እንዲህ ብሎ የሚናገረው ነው የሚመስለው። "አሁን ከጭብጤ አታመልጠኝም። በእርግጠኝነት ወደ ሲዖል ትወርዳለህ። ምንም ዋጋ የለህም። ስለዚህ ይህንንም የሚመጣውንም ሕይወት ከምታጣ በዚህኛው ሕይወትህ በዓለሙ ትምንሽንሽ ዘንድ እመክርሃለሁ።" እንዲህ ያለውን ሰው ዲያብሎስ ሕይወቱ ደካማና ብኩን መሆኑን ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ሕይወት መምራት ከባድ መሆኑን ጭምር ያሳምነዋል። አልፎ ተርፎም ከእርሱም እጅ ሆነ ከእግዚአብሔር ፍርድ እንደማያመልጥ ያረጋግጥለታል። እንዲህ ዓይነቱ ተስፋ የማስቆረጥ የዲያብሎስ ውጊያ እጅግ በጣም አደገኛ ውጊያ ነው። ለዚህ ሁሉ ግን መልሱ ቀላል ነው። "ሰልፉ ለእግዚአብሔር ነውና" 1ኛ ሳሙ 17፡47። ይህንን በክርስቶስ ድል እንደምናደርግም ተነግሮናል። 2ኛ ቆሮ 2፡14። ምንም እንኳ ደካሞች ሥጋውያንና ውጊያው የበረታ ቢሆንብንም ኃይልን በሚሰጠን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን እንችላለን። ፊል 4፡13። በጸጋውና በውስጣችን በሚሠራው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንታገዛለን። ይህ ብቻ አይደለም እኛን ለማገዝ በሚላኩ መላእክትም እንደገፉለን። ዕብ 1፡14። በቅዱሳን ሁሉ አማላጅነትም ብርታት እናገኛለን። ዲያብሎስ በእኛ ላይ ምንም ኃይል ስለሌለው በዛቻዎቹ አንደናገጥም። የሐዋርያው ቃል ምንኛ መልካም ናቸው! "ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል" ያዕ 4፡7። የእግዚአብሔርን ፍርድ በተመለከተም እርሱ አንድ ጊዜ በመስቀል ላይ ባሳየው ፍቅር ታላቁንና ቸል ልንለው የማይገባውን መዳናችንን ፈጽሞልናልና። ዕብ 2፡3። ስለ እኛም "በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነፃን የታመነና ጻድቅ ነው።" 1ኛ ዮሐ 1፡9። ሊያጥበንና ከበረዶም ይልቅ ሊያነጻንም ይችላል። መዝ 50፡7። እንዲህም ብሎናል "ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች፤እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች"ኢሳ 1፡18።

ምንም እንኳ ዲያብሎስ ከላይ በተመለከትነው መሠረት ተስፋ በማስቆረጥ ውጊያ ቢዋጋንም መጽሐፍ ቅዱስ ከሦስት ዋና ዋና መልካም ምግባራት መካከል አንዱ ተስፋ መሆኑን በመግለጽ ያበረታታል። 1ኛ ቆሮ 13፡13። እግዚአብሔርም ለእኛም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን ብዙ ቃል ኪዳኖችን ገብቷል። " . . . የገሃነም ደጆችም አይችሏትም" ማቴ 16፡18 እንዲሁም "በእግዚአብሔር ኃይል ለተጠበቃችሁ ለእናንተ . . ." 1ኛ ጴጥ 1፡5። የሚል ቃልም አለን። በእጁ መዳፎችም ቀርጾናል። ኢሳ 49፡16። መጽሐፍ ቅዱስ ከዚህ ሌላም የሚነግረን አለው። "እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና" 1ኛ ጢሞ 1፡7። ስለሆነም ሐዋርያው ከአንድም ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ መታከት እንደሌለብን ነግሮናል። 2ኛ ቆሮ 4፡1፤16፤ገላ 6፡9። በመንፈሳዊ ጉዞ ላይ ሳለህ ተሰነካክለህ ብትወድቅ ድጋሚ ተነስተህ መጓዝ እንደማትችል ሆነህ

ተስፋ አትቁረጥ። ነገር ግን ተነሳና ጉዞህን ቀጥል። ዲያብሎስ በእርምጃዎችህ ስለሚቀና ሊያደናቅፍህ ይፈልጋል። እንቅፋቱ ግን ወደ ተስፋ መቁረጥ አያድርስህ። ይልቁንም በመንፈሳዊ ጉዞህ ውጤታማ ከሆንህ ዲያብሎስ እንደማይተውህ አውቀህ የበለጠ ኃይል ጨምረህ ተነስ። ዲያብሎስ ለምን ብሎ የወደቀው ሰው ላይ ኃይሉን ይጨርሳል? ከእነዚህ ይልቅ በጉዞአቸው ላይ የማይናወጡትን፤ የሚቃወሙትን፤ውጊያውን የሚያከሽፉበትንና በእነዚህ ተግባሮቻቸው የሚፈራቸውን ይዋጋቸዋል። ስለ እነዚህም ይህ መመሪያ ተሰጥቷቸዋል። "የምትደላደሉ የማትነቃነቁም . . . ሁኑ" 1ኛ ቆሮ 15፡58።

ተስፋ አትቁረጥ። በእግዚአብሔር ድፍረት ይኑርህ። ምንም እንኳ የዲያብሎስ ውጊያዎች ከባድ ቢሆኑም ተስፋ አትቁረጥ። ብዙ ጊዜ ብትወድቅ ትዕዛዛቱን ብትረሳና ምግባርህም ጎዶሎ ቢሆን ተስፋ አትቁረጥ። ጅምርህ የተዳከመ ውጤት አልባና በከንቱ የባከነ ቢሆንም ተስፋ አትቁረጥ። ለራስህ እንዲህ በል። "እነዚህ ሁሉ ተራ ውጊያዎች ናቸው። ቢሆንም ወደ እግዚአብሔር እጠጋለሁ። እግሮቼን ብጎትትም ወደ እግዚአብሔር የማደርገው ጉዞዬን አላቋርጥም። በጉዞዬ ላይ አንድ መቶ ጊዜ ብወድቅም እንኳ ተነስቼ ጉዞዬን እቀጥላለሁ። ተስፋ መቁረጥ ከዲያብሎስ ነውና ምንጊዜም ቢሆን ተስፋ አልቆርጥም።"

6. ዕቅዱን ይለዋውጣል።

ዲያብሎስ ሰዎችን በተወሰነ የውጊያ ስልት ብቻ አይዋጋም። ዕቅድና ስልቱን መቀያየር ለእርሱ በጣም ቀላል ነው። ይህ የሚፈልገውን ሰው ለመጣል የሚረዳው ከሆነ ይጠቀምበታል። ከዚህ በማስከተል አንዳንድ ምሳሌዎችን እናያለን።

ሀ. ዲያብሎስ አንድን ወጣት በዝሙት ክፉኛ በመዋጋት ያደከመውና አልፎ አልፎ ይጥለዋል። በዚህ ጊዜ ይህ ወጣት ንስሐ በመግባት ይህን ኃጢአት ሊያስፈጽሙት ከሚችሉት ምክንያቶች ሁሉ በማንበብ በመስበክና በጉባኤ በመገኘት ይርቅና የምክንያቶቹን ደጆች በሙሉ ዘግቶ ራሱን በትጋት መጠበቅ ይጀምራል። በተመሳሳይ ጊዜ ከእንባ ጋር በጸሎት ወደ እግዚአብሔር በመጮህ ያድነው ዘንድ ይማጸናል። ታዲያ እንዲህ ያለ ትጋት ያለውን ጠንቃቃ ወጣት ዲያብሎስ እንዴት ሊያሸንፈው ይችላል? እንዲህ ነው። ዲያብሎስ "አሁን እተወዋለሁ። ይህን ኃጢአት ሙሉ ለሙሉ አሸንፌዋለሁ ብሎ ማሰብ እስከሚጀምርና እስኪዘናጋ ድረስ ለረዥም ጊዜያት አልዋጋውም። ከዚያ በኋላ ግን በሌላ ኃጢአት እዋጋዋለሁ።" ይላል።

ከዚህ በኋላ ለአንድ ወይም ለሁለት ወይም ለሦስት ዓመታት ያህል በዚህ ዝሙት እንዲወድቅ የሚያደርጉትን ማሰናከያዎች ማስቀረት ብቻ ሳይሆን ውጊያውንና ሰውየው ስለዚህ ኃጢአት ማሰብ እንኳ እስኪያቆም ድረስ እርግፍ አድርጎ ይተወዋል። ሆኖም ግን በኩራት ኃጢአት ተዋግቶ ይጥለዋል። ይህ ምስኪን ወጣት ከዝሙት ኃጢአት በመዳኑ ሐሴት በማድረግ





ላይ ሳለ ዲያብሎስ ጾሙን ንባቡንና አገልግሎቱን ከበፊቱ የበለጠ ጨምሮ እንዲያከናውን ይፈታተነዋል። አእምሮው ከዚህ ኃጢአት በመገላገሉ ተደስቶና በመንፈሳዊ ተጋድሎው ረክቶ እያለ ዲያብሎስ ይህን ተጋድሎ ለሌሎች እንዲያስተምር ይጋብዘዋል። ሌሎች ወንድሞቹ ዝንጉዎች መሆናቸውንና እርሱ ጥሎአቸው እንደሄደ ያሳየዋል። በዚህ ጊዜ ነው በኩራት ኃጢአት የሚወድቀው። ከዚህ በተጨማሪ "አባትህ አይጸልይም፤እናትህ አይጾሙም፤ወንድሞችህ ቅዱስ ቁርባን አይቀበሉም፤ ቤተሰቦችህ መጽሐፍ ቅዱስ አያነቡም።" በማለት ሌሎችን ክፉኛ እንዲኮንንና እንዲገስጽ ዲያብሎስ ያማክረዋል።

ይህ ዘለፋው እየበረታ ይሄድና ሌሎች ከእግዚአብሔር በመራቃቸው ሊሰድባቸውና ሊጠላቸው ይጀምራል። ልቡ በኩራት ታጅቧልና። ይህ ሰው እርሱ ራሱ እንከርዳድ ሆኖ ሳለ እንክርዳዱን ለመንቀል የሚታገል ሰው ነው። በጽድቅ ስም ሊሳደብ፤በቁጣ ሊናገር፤ ሊራገም፤ሎሎችን ሊጠላና አላዋቂነቱን ሊያሳይ ይነሣል። በከንቱነትና በኩራት ተሞልቶም ልክ እንደዚያ ፈሪሳዊ "እግዚአብሔር ሆይ እንደ ሌላ ሰው ሁሉ ቀማኞችና ዓመፀኞች አመንዝሮችም ወይም እንደዚህ ቀራጭ ስላልሆንኩ አመሰግንሃለሁ" (ሉቃ 18፡11) በማለት በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ሊጸልይ ይጀምራል። በዚህ ጊዜ ዲያብሎስን ስለዚህ ከዝሙት ኃጢአት ስለተገላገለው ሰው ብትጠይቀው "በዝሙት ኃጢአት ውስጥም ሆነ በኩራት ኃጢአት ውስጥ ሞት አለ። የሁለቱም ደመወዝ ሞት ነው።" በማለት ይመልስልሃል።

ሰው በሳምባ ምች ወይም በካንሰር ወይም ደግሞ በቀዶ ህክምና ላይ ሳለ ቢሞት ያው ሞተ ነው የሚባለው። የሞቱ ምክንያቶች ይለያዩ እንጂ ሞት ያው ሞት ነው፤መጨረሻው አንድ ነው። ወጣቱ አመለጥኩት ያለው ዝሙትም ውጊያን የመቋቋም ኃይሉ እየተዳከመ ሄዶ ዝንጉነትና ቸልተኝነት ሲያጠቃው በእርግጥ አንድ ቀን ይመጣበታል። በዚህ ጊዜ ግን ዲያብሎስ ራሱን ማወቅ እስኪሳነው ድረስ ክፉኛ ይዋጋዋል። ይህኔም ዲያብሎስ ለምን እንደዚህ እንዳደረገ ብትጠይቀው እንዲህ ብሎ ይመልስልሃል። "ይህ ወጣት ከዝሙት ውጊያው ባረፈበት ወቅት ይህ ውጊያ ዳግመኛ ተመልሶ እንደሚመጣበት ባለማሰብ ከሕይወቱ ሙሉ ለሙሉ እንደራቀ አድርጎ ይቆጥራል። እንዲህ ያለው ውጊያም የሚበረታው እርሱን በመሰሉ ከፍተኛ መንፈሳዊ ደረጃ በደረሱት ላይ ሳይሆን በጀማሪዎች ላይ እንደሆነ አድርጎ ይቆጥራል። አልፎ ተርፎም ብዙዎች ይህን ውጊያ የሚቋቋሙበትን ዘዴ ከእርሱ ምክር መጠየቅ እንደጀመሩ ያስባል። ስለሆነም በዚህ መንገድ የተፈጸሙና አስቀድሞ ያልሰማቸውን ሊሰማቸውም የማይገቡትን ጉዳዮች መስማት ይጀምራል።" ይህ ወጣት ከዚህ የዝሙት መሰናክል ጋር የተያየዙ ጉዳዮችን የሚያትቱ መጻሕፍትንም መልስ መስጠት ያመቸው ዘንድ ማንበብ ቀጥሏል። እንደነዚህ ያሉ መጻሕፍትን ግን ጠንቃቃና ትጉህ በነበረበት ወቅት አያነብም ነበር። አእምሮው በጊዜ ርዝመት እርሱ ባስተዋለው መልኩ በተወሰኑ ስሜቶችና አመለካከቶች ብቻ ይወጠራል። ከዚህ ሌላ ሌሎችን በመራገሙና በኩራቱ ጸጋ እግዚአብሔር ይለየዋል። ይህ ጊዜም ዲያብሎስ

በቀላሉ በቀደመ ኃጢአቱ ወግቶ ለመጣል ምቹ ጊዜ ይሆንለታል። በዚህም የዲያብሎስ ዕቅድ ይለዋወጥ እንጂ ግቡን መምታቱ አልቀረም።

አሁን ዲያብሎስ እንዲህ ይላል "ከመጀመሪያ ኃጢአቱ ለጊዜው ስላሳረፍኩት ለዚያ ውጊያ ዝግጅቱም ሆነ ጥበቃው አይኖረውም። በመሆኑም አሁን የምነግረውን አሳብና ኃጢአት ይቀበላል። በዚህ ቸልተኝነትና ዝንጋዔ መካከል ለዓመታት በረሳው ኃጢአት በቀላሉ ተዋግቼ እጥለዋለሁ።" ዲያብሎስ እንዲህ ነው። በአንድ ዓይነት ውጊያ ብቻ የማይዋጋህ ለአንተ ካለው ፍቅር ወይም ሐዘኔታ ሳይሆን ሌላ የውጊያ ወጥመድ ስላዘጋጀልህ ነው።

ለ. አንድ ሌላ ሰው ደግሞ በንዴት፤ሌሎችን በመራገም፤በስድብና ጸያፍ ቃላትን በመናገር (በአንደበት ኃጢአት) በተደጋጋሚ እየተሰናከለ ይወድቃል። በአንድ ወቅት ከዚህ ክፉ ምግባሩ መታቀብ እንደሚገባው በማመን ይህን የአንደበት ኃጢአት ለማራቅ ዝም ማለትን መለማመድ ይጀምራል። በዚህ ጊዜ ዲያብሎስ ምን የሚያደርግ ይመስላችኋል?

እንዲህ ይላል "ዕቅዴን እቀይራለሁ። በአንደበት ኃጢአትና በንዴት ሳይሆን በከንቱነት ኃጢአት እዋጋዋለሁ።" በመጀመሪያ ይህ ሰው ከእርሱ የሚሻል ማንም እንደሌለ ሙሉ ለሙሉ እንዲያምን ያደርገዋል። ከአንደበት ኃጢአት ሙሉ ለሙሉ አሳርፈዋለሁ። በምትኩ በተጋነነ መልኩ መንፈሳዊ አገልግሎቶችን እንዲሰጥና ፈጣን እድገት እንዲያሳይ ያለ ምንም ውጊያ እተወዋለሁ። በዚህ ጊዜ ይህ ሰው እርሱን የሚመስለው ማንም እንደሌለ በመቁጠር መኩራት ይጀምራል። የንስሐ አባቱ ይህን ፈጣን ለውጥና ከንቱነት አንስተው ሊወቅሱት ቢሞክሩም ግድ ስለሌለው አይሰማቸውም። ለማንም አይታዘዝም። የማንንም አሳብም አይቀበልም። ማንንም አያማክርም። ሁሉንም አያከብርም። በአንደበት ኃጢአት ከመውደቁ አስቀድሞ በከንቱነት ኃጢአት ስለሚጠለፍ ወድቆ ይጠፋል። ከዚህ በኋላም ከንቱነቱ ከሌሎች ጋር እንዲጋጭ ስለሚያደርገው ዲያብሎስ በመካከል ሳይገባ ያለ አንዳች ጥርጥር በአንደበት ኃጢአት ይወድቃል። በዚህ ላይ ደግሞ የዲያብሎስ ጠብ ጫሪነት ከተጨመረ አወዳደቁ እጅግ የከፋ ይሆናል።

እንዲህ እንዲህ በማድረግ ዲያብሎስ የውጊያ ዕቅዱን ያለማቋረጥ ይለዋውጣል። የሰውየውን ሁኔታ በመመልከት የሚስማማውንና የሚጥለውን ውጊያ ይመርጥለታል። መቼ እንዴትና በምን መዋጋት እንዳለበት ጠንቅቆ ያውቃል። በአንዱ ኃጢአት አሁን ያልወደቀው ከጥቂት ጊዜ በኋላ በሌላ ወይም በዚያው ኃጢአት ተጠልፎ ይወድቃል። ወጥመዶቹ ብዙዎችና በጥንቃቄ የተጠመዱ ናቸውና።

ሐ. ሌላው የዲያብሎስ ዕቅድ ለውጦ የመዋጋት ምሳሌ እንዲህ ነው። አምና በዐቢይ ጾም መግቢያ ላይ ጾም ጥቅም እንደሌለው አድርጎ የተዋጋውን





ወጣት በዘንድሮ ዐቢይ ጾም መግቢያ ላይም በዚያ ውጊያ ይጀምረውና በከንቱ ኩራት ይደመድምበታል። ጾምን በተመለከተ በጥርጣሬ ሊሞላው ይጀምራል። "ከእንስሳት ተዋጽኦ መታቀብ ማለት ምን ማለት ነው? ይልቁንም ከኃጢአትና በውስጥህ ካሉት አውሬዎች ጋር መዋጋት ይሻልሃል። ያለ ንጽህናና ቅድስና ብትጾምስ ምን ዋጋ አለው? እንዲህ ያለው ጾምህ ተቀባይነት ያለው ይመስልሃልን?" ይለዋል። ያ ወጣትም ". . . ሌላውን ሳትተው ይህን ልታደርጉ ይገባችሁ ነበር።" (ማቴ 23፡23) የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ያስባል። ከዚያም "ሥጋዬን ከመብል ነፍሴንም ከኃጢአት እንዲታቀቡ አደርጋለሁ" ይላል። በተጨማሪም ". . . ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ።" (1ኛ ቆሮ 9፡27) የሚል ቃል ስላለ ሥጋዬን ከላመ ከጣመ ከልክዬ ነፍሴን ከኃጢአት እንድትታቀብ አደርጋታለሁ።" ይላል። በዚህ ጊዜ ደግሞ ዲያብሎስ ይቀርብና "አንተ ደካማ ስለሆንክ ሰውነትህ ጾምን አይቋቋምልህም። በተለይ ደግሞ በዚህ ዕድሜህ ከእንስሳት የሚገኘው ፕሮቲን ያስፈልግሃል።" ይለዋል። ወጣቱም በመመለስ "ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም" (ማቴ 4፡4) የሚለውን የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ይጠቅስለታል። ቀጠል አድርጎም "አዳምና ሔዋንን የምድርን ሐመልማል ፤ የዛፍን ፍሬ ፤ የሚያፈራውን ዘርና የምድርን ቡቃያ እየተመገቡ በኖሩበት ዘመን ከእንስሳት የሚገኘውን ፕሮቲን ባለማግኘታቸው ምንም አልሆኑም" (ዘፍ 1፡29፤ 3፡18) ይለዋል።

በዚህ ጊዜ ዲያብሎስ "ጥሩ እንግዲያው ጹም። ነገር ግን በጣም ረጅም ስለሆነ ከዐቢይ ጾም መግቢያ አንስተህ ባትጾም ጥሩ ነው። አለበለዚያ ዲያብሎስ በከንቱ ትምክህት ሊዋጋህ ይችላል። የዲያብሎስ ውጋያዎችና የሚወረውራቸው ፍላፃዎች ኃይለኛ መሆናቸውን አትዘንጋ።" ይለዋል። አሁን ወጣቱ አቋሙን ሳይቀይር "መጾሜን አልቀንስም። ጌታችን እንደ እርሱ ፍጹማን እንሆን ዘንድ ይፈልጋልና። (ማቴ 5፡48) አሁን እኔ የምጾመው ጾም እኮ ቅዱሳን አባቶቼ ከሚጾሙት ጋር ሲነጻጸር ምንም አይደለም።" በማለት ያ ወጣት አምናንም ዘንድሮንም በጾሙ ይገፋበታል። ከዚህ በኋላ ዲያብሎስ ይህን ወጣት ከጾም እንዲታቀብ ማድረግ የሚቻለው በከንቱ ትምክህት መሆኑን በመረዳት የውጊያ ዕቅዱን ይለውጣል። ለዚያ ወጣትም እንዲህ ይለዋል። "ጾም እንዴት ጠቃሚ ነው! ዋናው ጥቀሙ የሚታወቀው ግን ረዘም ላለ ጊዜ ከጾሙ በኋላ ነው። አሁን አንተን እንደማይህ ግን በዐቢይ ጾም ከነግህ እስከ ሠርክ ብቻ ነው የምትጾመው። ስለዚህ ጉዳይ የንስሐ አባትህን አማክራቸው። (የንስሐ አባቱ እንደማይቀበሉት በማወቅ ነው ይሄን የሚለው) በማለት ወጥመዱን እዚህ ጋ ያጠምዳል።

በእርግጥም መምህረ ንስሐው በአሳቡ ባለመስማማት ሁሉን ነገር ቀስ በቀስ እ'ዲያደክናውን ይመክሩታል። በዚህ ጊዜ ዲያብሎስ በመካከል ይገባና "መምህረ ንስሐህ ጠለቅ ያለ የጾም ልምምድ ስለሌላቸው በዚህ ላይ የሚሰጡህ መመሪያ ለመንፈሳዊ ሕይወትህ እንቅፋት ይሆንብሃል። በዚህም ምክንያት በጾምህ ስለማትገፋ ጣፋጭ የሆነችውን የጾም ጣዕም ሳታጣጥማት ትቀራለህ። አስፈላጊ መስሎ ከታያቸውም በሆሳዕና ሳምንት ጾምህን

እንድታቋርጥ እንዳይመክሩህ እሰጋለሁ። ስለዚህ የንስሐ አባትህን ብትቀይር ይሻልሃል። አለበለዚያም ጾምንና የመሳሰሉትን በተመለከተ ለእርሳቸው ባታማክራቸው መልካም ይሆንልሃል። በአጠቃላይ እነዚህን ጉዳዮች ለእኔ ብትተውልኝ እንዴት መወሰን እንደምትችል እረዳሃለሁ።" ይለዋል።

በዚህም ዲያብሎስ ጾምን አስመልክቶ የውጊያ ዕቅዱን ጥርጣሬን ከመትከል የንስሐ አባቱን እንዲጠራጠር ወደ ማድረስ በሚያስችለው መልኩ ይለውጠዋል። የእርሱ ዋና ዓላማ የሚዋጋው ሰው መውደቅ እንጂ የውጊያው ዓይነት ብዙም አያስጨንቀውም። ወጣቱን ከመንፈሳዊ አባቱ ከለየው በኋላ ያለ መሪ በፈቀደው መንገድ መሄድ ይጀምራል። በልቦናውም መሪው ከእርሱ የተሻለ የመምራት ብቃት እንደሌለው አድርጎ ስለሚቆጥርና መሪውን ስለሚኮንን ልቦናው በከንቱ ኩራት ይሞላል። እነዚህ ሁሉ በመንፈሳዊው ጉዞ ላይ ሳለ ጎትተው የሚጥሉት እንቅፋቶች ይሆናሉ።

መ. ዲያብሎስ ማንኛውንም ዓይነት ሁኔታ ለመቋቋም የውጊያ ስልቱን ያለማቋረጥ ይለዋውጣል። ይህ ዲያብሎስ ክብ ዲያብሎስ በመባል ይታወቃል። ይህም ማለት በወደደው አቅጣጫ እንደ ኳስ መንከባለል ስለሚችል ነው። እንዲህ ያለው ዲያብሎስ የኩብ ቅርጽ ካለውና በአንድ ዓይነት አቅጣጫ ከሚጓዘው ዲያብሎስ ይለያል። ክብ ቅርጽ ያለው ሰይጣን አንተ በምትሄድበት አቅጣጫ ሁሉ ተንከባሎ መሄድ ይችላል። ለምሳሌ ፤ በማዕድ ተቀምጠህ ነገር ግን የማትበላ ከሆንክ "እንደ ሌሎቹ ሁሉ የማትበላ በመሆንህ ከምግብ መታቀብህን አደንቃለሁ።" ይልሃል። ልክ እንደ ሌሎቹ መብላት ስትጀምር ደግሞ "ቅዱሳኑም ይህን ያደርጋሉ። መልካም ምግባራቸውን ለመሸሸግ በትክክል እየጾሙ የሚበሉ ይመስላሉ።" ይልሃል።

በምትናገርበት ጊዜም "ይህ የሚያደምጡህን የሚያስደምም ድንቅ የጥበብ ቃል ነው።" ሲልህ አርምሞን ከመረጥህ ደግሞ "ዝምታ የቅዱሳኑ መልካም ምግባር ነው።" ይልሃል። ከዲያብሎስ ጋር ሁን እንጂ የሚነግርህን አትመነው። የሚናገራቸው ቃላትና የሚሰጣቸው ፍርዶችም አያነዋውጡህ። በውዳሴ ከንቱ ከተዋጋህ ኃጢአቶችህንና ደካማ ጎኖችህን በማስታወስ ራስህን ገስጽ። ወይም ደግሞ የሚጎድልህን የጽድቅ ሕይወት ከሰማኸው ሙገሳና ውዳሴ ጋር አመዛዝነው። በአጠቃላይ ዲያብሎስ በአንተ ላይ የውጊያ ዕቅዱን በለዋወጠ ቁጥር አንተም አመለካከትህን እየለዋወጥህ ተዋጋው።

ዮሐንስ ሐጺር የተባለው ቅዱስ አባት ለዚህ ምሳሌ ይሆነናል። ይህ ሰው ዲያብሎስ እጅግ አድርጎ ስለሚያወድሰው በገዳሙ ውስጥ ያሉት መናንያን ሁሉ ወደ እርሱ በመምጣት የቃሉን ቡራኬ ይጠይቁት ነበር። ይህም አባት በትህትና ራሱን ዝቅ በማድረግ ወደ እርሱ ስለሚመጡት ሁሉ "እኔ ምስኪንና ጎስቋላ ሰው ነኝ።" ይላቸዋል። "በእርግጥም ኃጢአተኛ ስለሆንክ መሞት ይገባሃል" ሲሉት ደግሞ "የእግዚአብሔር ፍቅርና ምህረት የት ሄዶ?" ይላቸዋል። ስለዚህ ርኩሳን መናፍስት ሁልጊዜ እንዲህ ይሉት ነበር። "በጣም ታስደንቀናለህ! እኛ ከፍ ከፍ ስናደርግህ ራስህን ታዋርዳለህ ፤





እኛ ስናዋርድህ ደግሞ ራስህን ከፍ ታደርጋለህ።" አንተም በዚህ ዓይነት መንገድ ራስህን ከዲያብሎስ ውጊያ መጠበቅ ትችላለህ። ርኩሳን መናፍስት ባወደሱህ ቁጥር ኃጢአትህን አስታውስ። ከአንተ ጋር ያላቸውን ውጊያ ሲያቆሙም እንዲህ በል! "ምናልባት እኔ የማላውቀውን ሌላ ወጥመድ እያዘጋጁ ይሆናል። አቤቱ ጌታ ሆይ ድካሜን ይቅር በል!"

ዲያብሎስ ባልደረስክበት መንፈሳዊ የብቃት ደረጃም ሊዋጋ እንደሚችል አትዘንጋ። በአንድ ወቅት ገና ምንኩስናውን የጀመረው ወጣት በምንኩስና ሕይወት ረዥም ጊዜ ወዳሳለፈው ታላቅ አባት ቀርቦ ዲያብሎስ ውጊያ ከፈተብኝ በማለት አምርሮ ሲነግረው የሰማው ዲያብሎስ ለዚያ ታላቅ አባት ተገልጦ "ይህ ዲያብሎስ ተዋጋኝ የሚለው ሰው ማነው?እኔ እስከነጭራሹ መመንኮሱን እንኳ አልሰማሁም" በማለት ተናግሯል። አደገኛዎቹ የዲያብሎስ ውጊያዎች እጅግ በጣም ከባድ ናቸው። ምናልባትም በእኛ ላይ ገና አልታወጁ ይሆናል። ቅዱሳንና ሰማዕታት የተዋጉዋቸው ውጊያዎች ግን እጅግ በጣም መራር ናቸው። እግዚአብሔር በዲያብሎስ ውጊያ ከመቁሰል ያድነን!

በከንቱ ኩራት የሚዋጋው ዲያብሎስ መሠረቱ ውዳሴ ሲሆን ከዚህ በተለየ መልኩ ስለ ውዳሴ ፈንታ በኃዘን የሚዋጋም አለ።

7. ኃዘን።

ይህ ዲያብሎስ ተነሳሒያንን የሚዋጋበት በጣም የተጋነነ ስልቱ ነው። በደሎቻቸውን አውቀው ለንስሐ የደረሱትን ወደ ዘላለም ጥፋት እንዲደርሱ በዚህ ዘዴው ይዋጋቸዋል።

ዲያብሎስ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት ጥቅሶች ሁሉ አንድ ጥቅስ ብቻ በማውጣት ሁልጊዜ በፊታቸው ያሳያቸዋል። ይህም "ከፊት ኃዘን የተነሳ ልብ ደስ ይሰኛልና።" (መክ 7፡3) የሚለው ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ጊዜ ማልቀሱ እንጂ አንድ ጊዜ እንኳ መሳቁ እንዳልተጠቀሰ ያሳስባቸዋል። አንድ ሰው በኃጢአት ክፉኛ ተወግቶ ሲወድቅ ዲያብሎስ ይበልጥ እንዲህ እያለ ኃዘንን ይጨምራል። "ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም።" 1ኛ ዮሐ 3፡9 ፤ 5፡18። በዚሁ ላይ ጨምሮም "አንተ እንኳን የእግዚአብሔር የንስሐ አባትህም ልጅ ልትሆን አይገባህም። ለእርሱ እንኳን አሳፋሪና አዋራጅ ሰው ነህ። ሰዎች አንተን እየተመለከቱ መምህረ ንስሐህን 'የአንተ ልጆች እንደዚህ ያሉት ናቸው' እያሉ ያደከሙታልና ይህን ጻድቅ ብትተወውና ባታስወቅሰው ይሻልሃል። እርሱ ሁልጊዜ እንደዚህ ሆነህ እያየህ በአንተ ምክንያት አብሮ ከሚረገም ብትተወውና ብቻህን ብትረገም ይሻልሃል።" ይለዋል። እንዲህ አድርጎ ከእግዚአብሔርና ከንስሐ አባቱ ተለይቶ እንዲሄድ ያደርገዋል።

መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ በሚገልጥበት ጊዜ እንኳ "በዚህ በረከስ እጅህ እንዴት የእግዚአብሔርን ቅዱስ መጽሐፍ ለመንካት ትደፍራለህ? በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ቃላት ሁሉ እንደሚፈርዱብህ አታውቅምን?" ይለዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ አንተ ላሉት 'እኔ የተናገርሁት ቃል እርሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል' (ዮሐ 12፡48) ማለቱን አታስተውልምን?" ይለዋል። እንዲህ በማድረግ ነፍሱን በኃዘን ሞልቶ መጽሐፍ ቅዱስን በምሬትና ተስፋ በመቁረጥ ማንበብ እንዲተው ያደርገዋል።

የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ከሆነም ለቦታው የሚገባ አለመሆኑን በመግለጽ አገልግሎቱን እንዲተው ያደርገዋል። እንዲህ በማለት "አገልግሎት የተሰጠው ለቅዱሳን እንጂ ለአንተ አይደለም፤አንተ ኃጢአተኛ ነህ። የማስናከያ ድንጋይ ስለምትሆን መምህራን በሚቀመጡበት ወንበር አንተ ትቀመጥ ዘንድ አይገባህም። አንተ የፈጸምካቸውን በደሎች በማስታወስ ቀንና ሌሊት እንዳትጸጸት ይልቁንም እንድትረሳው አገልግሎትህ ምክንያት ሆኖብሃል።" ለጸሎት በሚነሳበት ጊዜም "የኃጥአን መስዋዕት (ጸሎት) በእግዚአብሔር ዘንደ አጸያፊ ነው።" (ምሳ 15፡8፤28፡9) የሚለውን ጥቅስ በማስታወስ እንዲህ ይለዋል። "ይህን ራቅ ብሎ የቆመውን ምዕመን አትመለከትም? ዓይኖቹን ወደ ሰማይ ሊያነሳ እንኳ አልወደደም (ሉቃ 18፡13)። አንተ ግን ትዕዛዛቱን ጥሰህ ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር በመቆምህ ደፋርና ማስተዋል የጎደለህ ነህ። ስለዚህ እስቲ ስለ ራስህ እፍረት ይሰማህና ይህን የረከሰ ጸሎትህን አቁም።" በማለት ይወተውተዋል። እንዲህ አድርጎ ጸጸት ወደ ሌለው ኃዘን በመምራት ከጸጋ እግዚአብሔር አቆራርጦ ከእርሱ ጋር ብቻ እንዲሆን ግድ ይለዋል።

ተስፋ ቆርጦ፤መጽሐፍ ቅዱስ ማንበቡን ትቶ፤ያለ ንስሐ አባትና ያለ አገልግሎት ቀርቶ ምናልባትም ጉባኤውንና ወንድሞቹንም በኃዘኑ ምክንያት ተለይቶ ከእርሱ (ከዲያበሎስ) ጋር ብቻ መሆኑን ሲያውቅ እንደወደደ ይጫወትበታል። ከዚህ ሁሉ በኋላ "ለኃዘንህ ሁሉ ምክንያቱ መንፈሳዊ መሆንህ ስለሆነ ከዚህ አካባቢ ራቅ!" ማለት ለዲያብሎስ ምንኛ ቀላል ነገር ነው?! ይህንኑ ቃል በዘመዶቹ በሐኪሙና እርሱን ከኃዘኑ ለማጽናናትና ለማዝናናት በሚደክሙት አድሮ ለመናገርስ ምን ይከብደዋል? ዲያብሎስ ይህን ዘዴ የሚጠቀመውም ከእግዚአብሔር ሙሉ ለሙሉ የሚለይበትን ሌላ የውጊያ ስልት እስከሚያቀናብር በሚኖሩት ጥቂት ጊዜያት ውስጥ ነው። ከዚህ በኋላ ከኃዘን ወደ ፍጹም ተስፋ መቁረጥ አሸጋግሮ ይጥለዋል። ለዚህ ያበቃውም ኃዘኑ ነው። ዲያብሎስ በኃዘን በሚዋጋበት ጊዜ ታዳኙን ከተስፋና ከይቅርታ ማራቅ ዓይነተኛ ዘዴው ነው። የጠፋው ልጁን በታላቅ ደስታ ተቀብሎ ሌሎችም ደስ እንዲላቸው ከጠራውና ከሁሉ የተሻለውን ልብስ ካለበሰው አፍቃሪ አምላኩ (ሉቃ 15፡22-24)ይለየዋል። ከዚህ ሌላ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሏል። "እንዲሁ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር መላዕክት ፊት ደስታ ይሆናል።" ሉቃ 15፡10። በመጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳን ተስፋ ሳይቆርጡ ስለ ኃጢአታቸው ማልቀስ እንደሚገባቸውም ተዘግቧል። " . . . ተስፋ እንደ ሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ . . ." 1ኛ ተሰ





4፡13። ስለ ኃጢአታችን ማዘን ከእግዚአብሔር አይለየንም። ይልቁንም ኃጢአታችንን ሁሉ ይቅር ስለሚልልንና ለእርሱ ያለን ፍቅር ስለሚጨምር ይበልጥ ወደ እርሱ እንድንቀርብ ያደርገናል። ከዚህ በተጨማሪም እግዚአብሔር እንዲህ ብሎናል። "በደላቸውን እምራቸዋለሁና፤ኃጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ አላስብምና።" ኤር 31፡34። እግዚአብሔር ኃጢአተኛው በኃጢአቱ መሞቱ ሳይሆን ኃጢአቱን ትቶ መመለሱ ነው የሚያስደስተው። ሕዝ 18፡23።

በኃዘኑ ምክንያት ተስፋ የቆረጠ ሰው ችግር ደግሞ የእባቡን ይኸውም የዲያብሎስን ምክር መስማቱ ነው። ይሁን እንጂ ቃለ እግዚአብሔር መጽናኛ ነው፤የእግዚአብሔር ልቦና ምንጊዜም በፍቅር የተሞላ ነውና። ኃዘን ቢኖርም ወደ ንስሐ ለመምራትና ለልቦና መዋረድ እንጂ ከእግዚአብሔር ለመለየት አይደለም። ዲያብሎስ ኃዘንን በክፉ መልኩ ከተጠቀመበት በዚህ ወጥመዱ ውስጥ የሚወድቀውን ሰው ክፉኛ ይጎዳዋል ፤ያጠፋዋልም። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታውን አላውቀውም ካለ በኋላ መሪር እንባን አውጥቶ ስላለቀሰ ነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጦ "ግልገሎቼን አሰማራ . . . ጠቦቶቼን ጠብቅ . . . በጎቼን አሰማራ።" በማለት የተናገረው። ዮሐ 21፡15-17። ከዚህ የበለጠ ታዲያ ምን ተስፋ አለ? ስለዚህ ልብን ደስ የሚያሰኘው የፊት ኃዘን ከተስፋና ከፍቅር የሚለይ መሆን የለበትም።

8. ፍጥነት።

የዲያብሎስ ሥራዎች በፍጥነት ላይ የተመሠረቱ ናቸው። በነገር ሁሉ ሰዎችን ለጥፋት ያጣድፋል። የእግዚአብሔር ሥራዎች ግን በጸጥታ ፤በእርጋታ፤በትዕግስት፤በሰከነ መንፈስና በትክክለኛው ሰዓት የታጀቡ ናቸው። የእግዚአብሔር ማዳንና ቃል ኪዳን ለዚህ በቂ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል።

ዲያብሎስ አንድ ክፉ አሳብን ካሳሰበህ በኋላ በፍጥነት እንድትፈጽመው አሁንም አሁንም ደጋግሞ ያስታውስሃል። የዲያብሎስ አሳብ በልብህ ሲገባ ትፈጽመው ዘንድ ጽኑ ፍላጎት ያድርብሃል። ይህን አሳብ ለማንም ልታማክርበት፤ልትወያይበት፤ልትመረምረው፤ በተመስጦ ልታገናዝበውና ከሁሉም አቅጣጫ ልትመለከትበት የሚያስችልህን ጥቂት ፋታ እንኳ ሳይሰጥህ በፍጥነት እንድታከናውነው ውስጥህን በማንገብገብ የሚያስገድድህን ስሜት ይፈጥርብሃል። ዋናው የፍጥነቱ ወይም የማጣደፉ ምክንያትም እንዳታሰላስልና እንዳትመክርበት ነው። ይህን ፍጥነት ሲጠቀምም አንተና እርሱ ብቻ እንጂ ማንም በመካከላችሁ እንዲገባ አይፈልግም። ስለሆነም ጓደኞችህ፤ዘመዶችህ፤መምህረ ንስሐህ፤አስተማሪህና ሌሎችም በዚህ ጉዳይ ላይ ልምምዱና መንፈሳዊነቱ ያላቸው ወገኖችህን አወያይተህ ጠቃሚ ምክር እንዳታገኝ ያደርግሃል። የሚመክርህ በፍጥነት እንድታከናውነው ብቻ ነው።

ሌላው የሚጣደፍበት ዋናው ምክንያት ደግሞ ጉዳዩን ለፈጣሪህ በጸሎት የምታሳስብበትን ጊዜ ለማሳጣት ነው። ይህን ጉዳይ ለእግዚአብሔር አማክረህ የሚሰጥህን ምላሽ ወይም ደግሞ በጾም ተወስነህ የእግዚአብሔርን መመሪያ የምትጠብቅበትን ጊዜ ለመሻማት ነው። ይህ አሳቡ ምንም ዓይነት ምክርና ውይይት የሚያስፈልገው አለመሆኑን እስኪያሳምንህ ድረስ ይጫንሃል። ይህን በተመለከተ ቅዱሳን አባቶቻችን "በቶሎ እንድትፈጽመው የሚያስቸኩልህ አሳብ ሁሉ ከዲያብሎስ ነው።" ይላሉ። በእርግጥም እነዚህ አሳቦች በመስጠም ላይ ያለ ሰውን ለማዳን አሊያም በመቃጠል ላይ ያለ ቤትን ለማጥፋት የመጣደፍን ያህል የሚያስቸኩሉህ ሊሆኑ አይገባም። ንስሐ ገብተህ ወደ እግዚአብሔር የሚመልሱህና ከፍቅሩ የሚያጣብቁህም አይደሉም። ሰው በአፋጣኝ ሊፈጽማቸው የሚገቡት ሌሎችም ብዙ ነገሮች እንዳሉ ማስተዋል የሚችለው ወደ ንስሐ ሲደርስ ስለሆነ አብዝቶ ይጸጸታል። አንዳንድ ጊዜ ለማገናዘብና አሳብን ለመቀየር ጊዜ እስከምናጣ ድረስ ፍትህወትና ኃጢአት አእምሮአችንን ያጨናንቁታል።

ሌላው ዲያብሎስ ፍጥነትን የሚጠቀምበት ዋና ምክንያት ማንነቱ እንዳይታወቅ ነው። ምናልባትም ከሚያቀብላቸው ክፉ አሳቦችና ምክሮች በስተጀርባ በጸሎት በመካራከርና አርቆ በማሰብ ማንነቱ እንዳይገለጥ ውሸትና ተንኮልን አብሮ ያቀብላል። ስለሆነም ውሸቱና ተንኮሉ እንዳይታወቅ ያጣድፋል። እንዲህ ያለውን የዲያብሎስ ደባ በማጋለጥና ምክር በምስጠት ረገድ የንስሐ አባት ጥቅም ከፍተኛ ነው። "የሚመክርና የሚመራ የሌላቸው ሰዎች እንደ ዛፍ ቅጠል ረግፈው ይቀራሉ።" የሚለውም አባባል ይህንኑ የንስሐ አባት ድርሻ የሚያጎላ ነው። ይህ የተባለላቸውም ማንንም ሳያማክሩና ከማንም ሳይመከሩ ተፋጥነው ስለሚፈጽሙ ነው። ዲያብሎስ ክፉኛ ስለሚያጣድፋቸውም ተንኮሉ ከመገለጡ አስቀድሞ አሳቡን ይፈጽሙለታል።

የእግዚአብሔር ልጆች ግን ወደ ኅሊናቸው የመጣውን አሳብ ሁሉ አይቀበሉትም። በአንድ ወቅት ቅዱስ መቃርስ በምድረ በዳ መካከል በገዳም ያሉ የተሰወሩ አባቶችን ሄደህ እያቸው የሚል አሳብ ይመጣለታል። ነገር ግን ይህን አሳብ ከእግዚአብሔር መሆን አለመሆኑን ለማወቅ ለሦስት ተከታታይ ዓመታት ከዚህ አሳብ ጋር ሲዋጋ ኖሯል። ይህ ታላቅ አባት ለዚያውም የበቁና የተሰወሩ አባቶችን ለመጎብኘት ዕድሉን አግኝቶ ይህን ያህል መታገሱ ምንኛ ድንቅ ነገር ነው?!

ቅዱሳን በመታገሳቸውና በመቆየታቸው ብዛት ጥቅም እንጂ ጉዳት አላገኛቸውም። አንድ አሳብ ከዲያብሎስ ባይሆንም እንኳ በቶሎ አይፈጽሙትም። ቆይታቸው እግዚአብሔር በዚያ አሳብ ላይ ያለውን ፈቃድ እንዲገልጥ ስለሚያስችላቸው ይጠቅማቸዋል። ከዚህ በኋላም "ከእግዚአብሔር የሆነው ጸና፤ከእግዚአብሔር ያልሆነውም ተወገደ" ይላሉ።

በአንድ ወቅት ቅዱስ ጋሌዎን ለተባለው አባት ደግሞ ዲያብሎስ በመነኮስ መልክ ይገለጥና ከተሰወሩት አባቶች አንዱ መሆኑን ገልጾለት





አብረውት ያሉት ሌሎች የተሰወሩ አባቶች ወደ እርሱ ማኅበር እንዲመጣ የጋበዙት መሆኑን ያሳስበዋል። በዚህ ጊዜ ቅዱስ ጋሌዎን ስለዚህ ጉዳይ ለንስሐ አባቱም ሆነ ለእግዚአብሔር ሳያማክር ብድግ ብሎ ያን ዲያብሎስ በመከተል ጭልጥ ወዳለ ምድረ በዳ ይወርድና ይጠፋል። ከዚያም ያ አስቀድሞ የተገለጠለት ዲያብሎስ "በዚህ ምድረ በዳ ውስጥ ብቻህን ትሞታለህ" በማለት አላግጦበት ይሄዳል። በመጨረሻ ግን እግዚአብሔር በቸርነቱ ከጠፋበት መልሶ አዳነው።

## ፱. የተራዘመና ዝግ ያለ አቀራረብ።

ይህ ደባው ቀደም ሲል የተመለከትነው የፈጣን አቀራረቡ ተቃራኒ ነው። የዲያብሎስ የውጊያ ዘዴዎች የተለያዩ አንዳንድ ጊዜም እርስ በእርሳቸው የሚቀዋወሙ ይምሰሉ እንጂ ዓላማቸው አንድ ነው። የውጊያ ዘዴው እንደየ ጉዳዩ ይለያያል። በአጠቃላይ ግን ሰዎች ባያውቁትም እንኳ ዲያብሎስ በአንድ ዓይነት ዘዴ ብቻ አይዋጋም። አንዳንድ ጊዜ ሰውየው ምንም ባልተዘጋጀና ባልተጠነቀቀበት ሰዓት በድንገትና በፍጥነት ምቱን ይሰነዝራል። በሌላ ጊዜ ደግሞ ሰውየው ሊያስተውለው በማይችለው መንገድ በረዥምና ዝግ ባለ መንገድ ቀርቦ ያጠቃል። ምንም እንኳ ይህ የተራዘመና ዝግ ያለ አቀራረቡ ብዙ ጊዜ ቢፈጅበትም የእርሱ ጭንቀት የሚፈጅበት ጊዜ ላይ ሳይሆን ሰዎችን መጣሉ ላይ ነው። ይህ አዝጋሚ አቀራረቡ ምናልባት ኃጢአትን በቀላሉ ሊቀበሉ በማይችሉ ሰዎች ላይ ተፈጻሚነት ሊኖረው ይችላል። እነዚህን ሰዎች በእርጋታ በዝግታና ቆይቶ በሚጨምር የቀስ በቀስ እርምጃ ወደ ጥፋታቸው ይመራቸዋል። ይህም ማለት አንዱን ኃጢአት በደረጃ ከፋፍሎ እያንዳንዱ ደረጃ ራሱን በየጊዜው እንዲያሳድግ ያደርገዋል ማለት ነው።

ኃጢአትን ለመሥራት የመጀመሪያው ደረጃ ምናልባት ኃጢአት ላይሆን ይችላል። የኅሊና መድከምም እንዲሁ። በንጉሥ ዳዊት ውድቀት ውስጥ የመጀመሪያው ደረጃ ከጦር ግንባር መቅረቱ ነው። ሁለተኛው ንጉሥ ሳዖል እንደዚያ ከአገር አገር በየምድረ በዳው ሲያሳድደው ከቆየ በኋላ ድሎትና ቅንጦትን ወደ ሕይወቱ መጋበዙ ነው። ንጉሥ ዳዊት እነዚህን ሁለት ስህተቶች ጥፋት መሆናቸውን ሳያውቅ አልፏቸዋል። ይሁን እንጂ እነዚህ ስህተቶቹ መንፈሳዊ ፍቅሩን ባይበዛም በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ ስነ አእምሮአዊ ተጽዕኖ ጥለውበት አልፈዋል። ከዚህ በኋላ ነው ዳዊት ወደ ሦስተኛው ደረጃ ማለትም ብዙ ሚስቶችን ወደ ማግባት የተሸጋገረው። ይህ በወቅቱ የተፈቀደ ጉዳይ ቢሆንም ሥጋዊ ፈቃዱን ይበልጥ እንዳበረታታበት የማይካድ ነው። የተፈቀደ ይሁን እንጂ የብቃት ደረጃም አይደለም። አውቆትም ይሁን ሳያውቀው ሥጋው በነፍሱ ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል። በመቀጠል አራተኛው ደረጃ ተከተለ። ይህም ወደ ቤቱ ሰገነት በመውጣት ሊያየው ያልተፈቀደለትን የሌሎችን ጓዳና የግል ምሥጢር (ጉዳይ) ማየት ሲሆን ከዚህ ጊዜ አንስቶ ያዳልጠው ጀመር። አምስተኛው ደረጃ ይህን ታላቅ

መዝሙረኛ በፍትህወት ኋላም በዝሙት የጣለ ኃይለኛ በትር ሆነ። ስድስተኛውና የመጨረሻው ደረጃም ንጉሡ ኃጢአቱን ለመሸሸግ የሞከረባቸውና መንፈሳዊነቱን አሳጥተው ከድጡ ወደ ማጡ የከተቱት የተለያዩና በዛ ያሉ አሳፋሪ ኃጢአቶች የተካተቱበት ደረጃ ነው።

ምናልባት ዲያብሎስ እነዚህን የኃጢአት ደረጃዎች ለረዥም ጊዜ ሲያዘጋጅ ቆይቷል። በመጨረሻ የሚሰነዝረው ጡጫ ግን ብርቱ እንዲሆን ይወድዳል። ይህ እንዲሆን ግን በእርሱ በኩል ረዘም ያለ የዝግጅት ጊዜ ይፈልጋል። ከዚያ ተመልሶ ሲመጣ ግን ያ ቤት አምሮ ተወልውሎና አጊጦ ተጠቂው ሊቋቋመው በማይችለው መልኩ ለሥራው ዝግጁ ሆኖ ያገኘዋል። ለመከላከል ቢሞክርም እንኳ ኃይሉ ተሟጦ ስላለቀ በቀላሉ ይወድቃል። እስቲ በተጋድሎው የሚታወቀውን የባህታዊው የቅዱስ ያዕቆብን ታሪክ እንመልከት።

የዚህ ቅዱስ አባት ታሪክ ልክ እንደ ንጉሥ ዳዊት የውድቀት ታሪክ ዲያብሎስ እንዴት በረዥምና ዝግ ባለ አቀራረብ ሊጥል እንደሚችል ያሳየናል። ይህ ታላቅ ባህታዊ አባት ምንም እንኳ ርኩሳን መናፍስትን የማስወጣት ታላቅ ጸጋ ቢኖረውም ዲያብሎስ ሊጥለው ችሏል። የእግዚአብሔር ምህረት ለንስሐ ባያደርሰው ኖሮ ዲያብሎስ በሦስት ለሞት በሚያበቁ ምቶች መትቶት ነበር። ይህ እንዴት ሆነ? ታሪኩ እንዲህ ነው።

በአንድ ወቅት አንዲት የንጉሥ ሴት ልጅ ማንም ሊያወጣው ባልቻለ ርኩስ መንፈስ ትያዛለች። ይህችኑ ልጅ ወደዚህ አባት ያመጧትና ከጸለየላት በኋላ ርኩስ መንፈሱ ትቷት ይወጣል። ይሁን እንጂ ወደ አገሯ ከተመለሰች በኋላ መልሶ ይይዛታል። አሁንም መልሰው ወደዚሁ አባት ያመጧትና ድጋሚ ከጸለየላት በኋላ ይወጣላታል። ተመልሳ አገሯ እንደ ገባች አሁንም ተመልሶ ይገባባትና ለሦስተኛ ጊዜ ወደ ቅዱስ ያዕቆብ መልሰው ያመጧታል። ይህ የዲያብሎስ ዕቅድ ሰዎቹ ተመላልሰው በመምጣት እስኪሰለቹ ድረስ ተደጋግሞ ይቀጥላል። በመጨረሻ ግን ንጉሡ ልዕልቲቱን በዚህ ቅዱስ አባት ዘንደ ለመተው ይወስናል። በዚህ መሠረት እዚያው አንድ ክፍል ቤት ይሠራላትና ርኩሱ መንፈስ ባስቃያት ቁጥር ወደ እርሱ በማምጣት እየተዟት መውጣት ይጀምራሉ። ሰዎቹ መረጋጋት መጀመሯን ሲመለከቱ እዚያው ይተዟትና ወደ አገራቸው ይመለሳሉ።

ከጊዜ ብዛት በዚህ አባትና በልዕልቲቱ መካከል የተፈጠረው መግባባት ወደ ኃጢአትነት ያድጋል። የልዕልቲቱን ከእርሱ ማርገዝ እንዳወቀም ይህ በሌሎች ዘንድ ከታየ እንደሚዋረድና ንጉሡም ከስማ ሊገድለው እንደሚችል ይረዳል። በዚህ ጊዜ ዲያብሎስ ግደላት ብሎ ሲያማክረው ይገድላትና ራቅ ወዳለ ምደረ በዳ ወስዶ ይቀብራታል። ከወራት በኋላ ስለ ልጁ ጤንነት እንዲጠይቁ ንጉሡ መልዕክተኞችን ወደዚህ አባት ይልካል። በዚህ ጊዜ ያ አባት በመዋሸት ልጅቱ በአንድ ወቅት ዲያብሎስ ክፉኛ ከጣላት በኋላ ከቤት ውስጥ ተፈትልካ በመውጣት እንዳመለጠችና





ማንም ደርሶ ሊይዛት ባለመቻሉ እንደጠፋች ይነግራቸዋል። የሚታመን ሰው ስለሆነም ያምኑታል። በዚህም ዲያብሎስ በሦስት ዋና ዋና ፍላፃዎች ማለትም በዝሙት በግድያና በሐሰት ክፉኛ ወግቶ ይጥለዋል። ይህ ሁሉ የሆነው ቀስ በቀስ ሲሆን ጅምሩ ፍፃሜውን የጠቆመበት አንዳችም አጋጣሚ አልነበረም። በዚህም ዲያብሎስ ምን ያህል በከፍተኛና በሚያስደንቅ ትዕግስት የተንኮል ሸማውን እንደሚሸምን ያመለክተናል። ረዥምና ዝግ ያለ የዲያብሎስ ውጊያ ግቡ ታላቅ ነው። በእያንዳንዱ እርምጃ ተጠቂው ወደ ኃጢአት ይቀርባል ፣ ይላመደዋል በመጨረሻም ይደክማል። ከኃጢአት አሳብ ርቆ ሳለ ፈቃዱ ፍጹም ጽኑ በመሆኑ ሁሉን በሚገባ ይመረምራል። እየደጋገመው ሲመጣ ግን ይለምደዋል። ቀስ በቀስ ይህ ነገር በህሊናውና በህዋሳቱ ሲሰርጽ በእያንዳንዷ የጥፋት እርምጃ ፈቃዱ እየላላና እየደከመ ስለሚሄድ አውቆትም ይሁን ሳያውቀው ለመቋቋም የሚያዳግተው ደረጃ ላይ ይደርሳል።

ለረዥምና ዝግ ላለ የዲያብሎስ ውጊያ ዓይነተኛ ምሳሌ የሚሆነን ሱስ (ልማድ) ነው። ማንኛውም ሱስ ወይም ልማድ ሲጀምሩት ሱስ ሆኖ አይጀምርም። ሰውየው ከጅምሩ ቢቀጨው ተቀጭቶ መቅረት ይችል ነበር። ነገር ግን በረዥምና ዝግ ባለ ውጊያ ሊቆጣጠርና ሊያቆመው ስለማይችል እርሱን ይቆጣጠረዋል። ምናልባት ዲያብሎስ በመጀመሪያ የሚናገረው አንዲት ቃል ብቻ ነው። “ሞክር” ወይም “ቅመስ” የምትለዋን። ከዚያ በመቀጠል ነው “ሕይወት ልምምድ ናት ሁሉን የምትወስነው አንተ ነህ። በወደድክ ጊዜ ልታቆመው ወይም ልትተወው ትችላለህ።” የሚለው። እንዲህ እንዲህ እያለ ሰውየው መቋቋም እስኪያቆም ወይም ለመቋቋም ፍላጎቱን እስኪያጣ ድረስ ይዋጋዋል። ይሁን እንጂ ሱስን ወይም ልማድን ማስወገድ ለሚወድ ሁሉ ማስወገድ ይቻላል። ዲያብሎስ ግን እንደማትችል ይነግርሃል። ተስፋ ብትችል እንኳ ድጋሚ ወደ ተውከው ሱስ ትመለሳለህ ይልሃል። ተስፋ ማስቆረጥ የታከለበት ውጊያ ስለሆነ አትንበርከክ። ሱሰኝነት የሚመጣው ከሚደጋገም የፈቃድ ተግባር ነው። ይህን ተደጋጋሚ የፈቃድ ተግባር በሌሎች ተደጋጋሚና ተቃዋሚ የፈቃድ ተግባራት ማስወገድ ትችላለህ። በእንዲህ ያለ ተግባርህም ጽናት እንጂ ማወላወል ሊታይበት አይገባም። እንዲህ ያለውን የዲያብሎስ አዝጋሚ የውጊያ ዕቅድ እንዴት መቋቋም እንደምትችል የምንነግርህ ነገር ቢኖር ምንም እንኳ አሳቡ መልካም መስሎ ቢታይህና እንዲህ መስሎ እንዲታይህ በማድረግ ዲያብሎስ ቢያሳምንህም የመጀመሪያውን ደረጃ አለመፈጸም እንዳለብህ ነው።

ውሸቱን እወቅበት። በተለይም ይህ የሚቀጥል ደረጃ መሆኑን ከነገረህ ዲያብሎስ አሳቡን በአንደኛው ደረጃ ላይ ሳያቆም በርቀት ላለው ግቡ መወጣጫ የሚሆኑ ሌሎች ደረጃዎችን ያለማቋረጥ እንደሚዘረጋ አትዘንጋ። ስለዚህ ተጠንቀቅ! ምንም ቀላል መስሎ ቢታይህና ሊያድግ እንደማይችል ብታስብም የመጀመሪያውን ደረጃ ተቃወም።

## 10. ጥቃቅን ጉዳዮች።

ሰሎሞን በመዝሙሩ እንዲህ ይለናል። "የወይናችንን ቦታ የሚያጠፉትን ጥቃቅኑን ቀበሮዎች አጥምዳችሁ ያዙልን።" መኃ 2፡15። እዚህ ላይ ዋናው ቁም ነገር ጥቃቅን መሆናቸው ሳይሆን ወይኑን ማበላሸታቸው ነው።

በዚህ መሠረት እነዚህ ጥቃቅን ቀበሮዎች በመጀመሪያ የሚያደርሱት አደጋ ወደ ነፍስ ዘልቀው መግባታቸው ነው። ትላልቆቹ ቀበሮዎች ምናልባት እነርሱን የሚያስገባ ስፊ ቀዳዳ በወይኑ ቅጥር ዙሪያ ላያገኙ ይችላሉ። ጥቃቅኖቹ ግን በቀላሉ ሾልከው ይገባሉ። አንድ ሰው ታላላቅ ከሚባሉት ኃጢአቶች ራሱን ሊጠብቅና ሊርቅ ይችላል። ካወቃቸው ደግሞ ዲያብሎስ የሚያውቀውን ትልቅ ኃጢአት ለሌላ ጊዜ በማስተላለፍ በማያውቃቸውና በጥቃቅኖቹ ኃጢአቶች ይዋጋዋል። ዲያብሎስ አንድን ሰው በጥቃቅን ኃጢአት የሚዋጋው ስለ እነዚህ ኃጢአቶች ብዙም ስለማይጠነቀቅና ቸል ስለሚላቸው ነው። ለምሳሌ አንድን ሰው "በእነዚህ ነገሮች እንዳትጠቃ" ብለህ ስታማክረው "እንዲህ ያሉት ጥቃቅን ነገሮች የሚያስፈሩኝ ይመስሉሃልን? እነዚህ የሚያጠቁት ወጣንያንን ነው። እኛ እንደዚህ ካሉት ነገሮች ሁሉ በላይ ነን" በማለት በአባባልህ እየተገረመ ይመልስልሃል። ከዚህ በኋላ በእነዚሁ ጥቃቅን ባላቸው ኃጢአቶች ዲያብሎስ ሊዋጋው ይጀምራል። ታላቁና በእግዚአብሔር ተወዳጅ የነበረው አባታችን አብርሃም በመፍራቱ ሚስቱ ሣራን እህቴ ናት ስላለ በእነርሱ ዘንድ ሊጠብቋት ይችላሉ ብሎ ማን ሊያስብ ይችላል? ፍርሃትና ውሸትን የመሰሉ ኃጢአቶች የነቢያትና የአባቶች ሁሉ አባት ለተባለው ታላቅ መንፈሳዊ አባት ለአብርሃም በእርግጥም ጥቃቅን ነበሩ።

ሰው ሰውነቱን ለማርከስ የግድ ከባድ የተባለውን የዝሙት ኃጢአት ብቻ መፈጸም የለበትም። "ሥጋን ሁሉ ያሳድፋል" (ያዕ 3፡6) ተብሎ በተነገረለት በአንደበት ኃጢአትም ሊረክስ ይችላል። አንደበታችን አነስተኛው የሰውነታችን አካል ይሁን እንጂ "ዓመፀኛ ዓለም" ነው። ስለ አንደበት "የሚገድል መርዝ የሞላበት ወላዋይ ክፉት ነው" ተብሏል። ያዕ 3፡8። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እንደተናገረው የሰውን ሰውነት በሙሉ አንደበቱ ሊያረክሰው ይችላል። " . . . ከአፍ የሚወጣው ግን ሰውን የሚያረክሰው ይህ ነው።" ማቴ 15፡11፤18። በጣም የሚያስደንቀው ግን ዲያብሎስ የአንደበት ኃጢአት በጣም ቀላል ጉዳይ እንደሆነ አድርጎ ሊያሳምን መቻሉ ነው። በእርግጥም የዲያብሎስ ቀላል ጉዳዮች ሰውን ማጥፋት ይችላሉ። መርከብ ከወለሉ ላይ በምትፈጠር አነስተኛ ቀዳዳ ሊሰጥም ይችላል። ሰውም ይሞት ዘንድ በግዙፍ አውሬ መሰልቀጥ የለበትም፤በዓይን ልትታይ የማትችል ደቂቅ ሕዋስ ለሞት ልታደርሰው ትችላለችና። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ እንዲህ ብሏል። "በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል።" ማቴ 5፡22። ለዲያብሎስ "ሞኝ" እና ሌሎችም ተመሳሳይ ቃላት ጥቃቅን ከሚባሉት





ጉዳዮች መመደባቸውን ለማሳመን ምንኛ ቀላል ነው?! ምናልባት ሐናንያና ሰጲራ ኃጢአታቸው ጥቃቅን ከሚባሉት አንዱ እንደሆነና ለሞት ቅጣት ሊያበቃቸው እንደማይችል አስበው ይሆናል። ጠቢቡ ሰሎሞንም ከአንግዶች ሴቶች መጋባቱን እንደ ቀላል ጉዳይ ተመልክቶት ይሆናል። ነገር ግን ውጤቱ ለድኅነቱ ምን ያህል አደገኛ ሁኔታን እንደፈጠረበት እናነባለን። 1ኛ ነገ 11፡1-11። በእርግጥም ጥቃቅን የተባሉ ጉዳዮች ሁሉ ጥቃቅን ሆነው አይቀሩም። ዲያብሎስ ይህን ስም ይስጣቸው እንጂ ላይሆኑ ይችላሉ። እንደ ሰሎሞን፣ዳዊትና ሐናንያ በጣም አደገኛ ወደ ሆነ ውጤት ሊመሩ ይችላሉ። ጥቃቅኖቹ ጉዳዮች አድገው በጣም አደገኛ ጉዳዮች ሊሆኑ ይችላሉ።

እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን በገነት መካከል ባለችው ዕጸ በለስ እንደፈተሻቸው የእኛንም ፈቃድ ለእኛ ቀላል መስሎ በሚታየን ነገር ግን የውስጥ ማንነታችን በሚያጋልጡ ፈተናዎች ሊፈትሽ ይችላል። እነዚህ ጥቃቅን ጉዳዮች ግን ምንና እንዴት ያሉ ሊሆኑ ይችላሉ? የመጣለትን አሳብ ሁሉ ለማንም ሳያማክር ለራሱ የሚጠብቅ ሰው ለዚህ ምሳሌ ይሆናል። ዲያብሎስ እንዲህ ያለውን ሰው፤"ታዲያ ይሄ ምናለበት? ምን ችግር አለበት? ለዚህ ጉዳይ ሌሎችን እንዴት ታማክራለህ? ምክንያትህ እኮ በቂ ነው።" ይለዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ለሚሰሙት ላነበቡትና ለሚያስቡት ጉዳይ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ካለመስጠት ወይም በአነጋገርና ራስን በመውቀስ ረገድ ልል ከመሆን የተነሳ ነገሮችን እንደ ጥቃቅን ጉዳዮች አድርጎ መመልከት ሊመጣ ይችላል። ከዲያብሎስ ጥቃቅን ጉዳዮች ለመዳን አለማወላወል ወይም ጽናት ወሳኝ ነው። በጥቂቱ የመታመን መልካም ምግባርም ከዚህ አደጋ ሊጠብቀን ይችላል። ጌታ "ከሁሉ በሚያንስ የታመነ በብዙ ደግሞ የታመነ ነው።" ብሏልና። ሉቃ 16፡10።

## 11. ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ።

ዲያብሎስ በሚቻለው ሁሉ አንተ መንፈሳዊ ሥራ እንዳትሠራ ሊያግድህ ይሞክራል። አንድን መንፈሳዊ ሥራ አሁን ካላደረግሁ ብለህ ቆርጠህ መነሳትህን ሲመለከት ለሌላ ጊዜ እንድታስተላልፈው ይመክርሃል። "ምን ያጣድፍሃል? ጉዳዩ በእጃችን ስለሆነ ሌላ ጊዜ ልናከናውነው እንችላለን። ምናልባትም ረጋ ብለን ማጤናችን ጉዳዩን በሚገባ ለመመርመርና በቀላሉ ልናከናውነው የምንችልበትን ዘዴ ሊጠቁመን ይችላል።" በማለት ከተናገረን በኋላ ቀጠል አድርጎ በሚያሳምን መልኩ "ለማንኛውም ግን አሁን ቅድሚያ ሰጥተን ልናከናውናቸው የሚገቡን አንገብጋቢ ጉዳዮች አሉ። እነዚህን ከጨረስን በኋላ ወደዚህኛው እንመለሳለን።" ይለናል። የማስተላለፍ ዋና ዓላማ ሥራን ለማከናወን ካለን ጽኑ ፍላጎት ማራቅ ወይም አጋጣሚውን ማሳጣት ወይም ማከናወን ያለብንን ጉዳይ እንረሳው ዘንድ ወደ ጎን ማድረግና ሌላው ጉዳይ ከዚህኛው የበለጠና ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ አስመስሎ ማሳየት ነው።

ሰዎች እግዚአብሔርን ልክ ነፃነታቸውን የሚነፍግ በፍላጎቶቻቸው መካከል የሚቆምና ከነመኖራቸውም የማይቆጥራቸው ጠላታቸው አድርገው እንዲመለከቱት ለማድረግ ዲያብሎስ ዘወትር ይጥራል። ሰዎችም ከእነዚህ ዓለማዊ ፍላጎቶቻቸው በመራቅ ወደ እግዚአብሔር ከመቅረብ ይልቅ በእነርሱው ምክንያት የእግዚአብሔር ጠላቶች ሆነው ይቀራሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ ዲያብሎስ ገደብ የለሽ ነጻነትን ሃይማኖት ነክ በሆኑ ግንዛቤዎች ውስጥ ያስፋፋል። ማንም ሰው መጽሐፍ ቅዱስን በመሰለው መንገድ እንዲተረጉም እንዲረዳና የተረዳውንም ለሌሎች እንዲያስረዳ ነፃ መሆኑን ይነግረዋል። ስለሆነም አእምሮ በእነዚህ የግል አመለካከቶች መካካል ግራ ይጋባል። በእነዚህ "ማንም የራሱን እምነት ለማስፋፋት ነፃ ነው፤የግድ በሃይማኖት ጥላ ሥር የመሰባሰብ ግዴታ የለበትም" በሚል የተሳሳተና ገደብ የለሽ ነፃነት ስም በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ሃይማኖት ነን ባይ ድርጅቶች በክርስትና ሥር ተከስተዋል። ቤተ ክርስቲያን ግን አንዲት እምነቷም አንድ እንጂ የተቀዋዋሚዎች ስብስብ አይደለችም። መጽሐፍም ስለዚህች አንዲት ሃይማኖት ይናገራል። "አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት" ኤፌ 4:5። ከዚህ በተጨማሪም "ያመኑትም ሕዝብ አንድ ልብ አንዲትም ነፍስ ነበሩአቸው።" የሚል ቃል አለ። ሐዋ 4:32። ከዚህ ሌላም ምንም እንኳ የምዕመናን ቁጥር እጅግ የበዛ ሊሆን ቢችልም እንኳ ቤተ ክርስቲያን አካሏ አንድ ራሷ የተባለ ክርስቶስም አንድ ነው። ኤፌ 5:23። ራሷ ክርስቶስ መሆኑን ካመንን ደግሞ ምንጊዜም የክርስቶስ ልብ አላት። 1ኛ ቆሮ 2:16። ይህም ልብ ምንም የሚቃዋወም ነገር የሌለበት አንድ ልብ ነው።

ታዲያ የእምነት ነፃነት ስንል ምን ማለታችን ነው? ገደቡስ? እኛ ማንም የወደደውንና የሚያምንበትን ነፃነት አንቃወምም። ማንንም ደግሞ እርሱ ከሚፈቅደው ውጪ አስገድዶ ማሳመን አይቻልም። ማንም የቤተ ክርስቲያንን እምነት በተሰጠው ነፃ ፈቃድ ከተቀበለ የቤተ ክርስቲያን አባል ሲሆን ያልተቀበለው ደግሞ በውጪ ይቀራል። ቤተ ክርስቲያንም በአንዲት ሃይማኖቷ ትጸናለች። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሰዎችን ነፃነት በመድፈር ማንንም በግድ አታሳምንም። ሆኖም ግን ማንም እምነቱ ባይኖረውም እንኳ የቤተ ክርስቲያን አባል ነኝ ብሎ መናገር ይችላል። እዚህ ላይ ዲያብሎስ ይህ ነፃነት መኖሩን ቢያውቅም እንኳ አይቃወምም። ምክንያቱም ሰውየው ይበል እንጂ እምነቱ ከሌለው የቤተ ክርስቲያን አባል ተብሎ ተቀባይነት እንደማያገኝ ስለሚያውቅ ነው። ይህ ግልጽ ነገር ነው። ስለዚህ ሰው የቤተ ክርስቲያንን እምነት ካልተቀበለ ያልተቀበለው በራሱ ነፃ ፈቃድ ነው። እዚህ ላይ የሐዋርያው የቅዱስ ዮሐንስ ቃል ሊጠቀስ ይችላል። "ከእኛ ዘንድ ወጡ፤ዳሩ ግን ከእኛ ወገን አልነበሩም ፤ከእኛ ወገንስ ቢሆኑ ከእኛ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር።" 1ኛ ዮሐ 2:19።





ይህን የምንለው በነፃ እምነት ስም በዓለም ዙሪያ ባሉ አንዳንድ የነገረ መለኮት ኮሌጆች ውስጥ ሊቀበሏቸው በሚገባቸው በቤተ ክርስቲያን ቀኖናዎችና ጸሎተ ሃይማኖት ሳይወሰኑ የወደዱትን ትምህርት አስተምረው የሚሄዱ መምህራን ስላሉ ነው። አንዱ በነገረ መለኮት የፕሮፌሰርነት ማዕረግ ያለው ሰው ወደ እነዚህ ጉባኤዎች ገብቶ የወደደውን ርዕስ ያስተምራል። በዚህ ዓይነት መልኩ ከእነዚህ ኮሌጆች ውስጥ ከአሕዛብ ወገን የሚሆኑ ሌሎች የነገረ መለኮት ፕሮፌሰሮች ይወጣሉ። በዚህም ዲያብሎስ በሐሰት ነፃነት ስም ዱላውን በሚገባ ለመቃጣትና ለመምታት ይችላል። "ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት" (ይሁዳ 3) የቆመችው ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ግን ለእንደዚህ ያለ ትምህርት አትጋለጥም። መናፍቃንና ቅን ያልሆነ አመለካከት ያላቸውን ሰዎች አውግዛ በመለየት ነቅ የሌለባትን አንዲት የቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት በማስጠበቅ ለሚቀጥለው ትውልድ ታስረክባለች። ለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሥልጣን ይህን ያለው። "ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን።" ገላ 1:8። ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊውም እንዲህ ብሎናል "ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት፤ ሰላምም አትበሉት፤ሰላም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው ይካፈላልና።" 2ኛ ዮሐ 10-11። ከሌሎቹ ሐዋርያት ሁሉ በላይ ስለ ፍቅር ከተናገረው ሐዋርያ ይህን መስማት ለጽናታችን መሠረት ነው። ስለሆነም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እምነቷን ትጠብቃለች፤ከመናፍቃን ትከላከላለች በነፃነት ስም ገብተው ሊስፋፉ የሚሞክሩ የግለሰብ አመለካከቶችንም አትቀበልም። ከዚህ የተነሳም ዲያብሎስ የቤተ ክርስቲያንና የክህነትን ሥልጣን ሲቃወም እንመለከታለን። ይህ ሥልጣን ግን ትውልድ ባለበት ዘመን ሁሉ የሚጸና ሥልጣን ነው። አንድ ሰው ከበደለ በኋላ ንስሐ እስካልገባ ድረስ ይህን ስህተቱን የሚያወግዘውንና በእግዚአብሔር የተሰጠውን ይህን የካህኑን ሥልጣን በመቃወም ላይ ነው። ማቴ 18:18። ዮሐ 20:23።

ዲያብሎስ የተሳሳተ አመለካከቱንና አሳቡን ቤተ ክርስቲያንን ለመዋጋት ብቻ ሳይሆን በማንኛውም መስክ ያለውን ክፉን የሚከለክል ሥልጣን ሁሉ በመዋጋት ይጠቀማል። ዓላማው ክፉ ሥራዎች ሁሉ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ነው። በቤተሰብ ውስጥ አባት በልጁ ላይ ያለውን ሥልጣን የልጁን ክብር ለማስጠበቅ በሚል ሽፋን ይዋጋበታል። አስተማሪዎች በትምህርት ቤቶች ወይም በኮሌጆች ውስጥ በተማሪዎቻቸው ላይ ያላቸውን ሥልጣን ጠንካራ ትውልድ ለመፍጠር በሚል ሰበብ እንዲጠቀሙበት በማድረግ ይዋጋበታል። የመንግሥትንም ሥልጣን በዴሞክራሲና በሕዝቦች መብት ሽፋን ይዋጋበታል። የእግዚአብሔርን ሥልጣን እንኳ ሰው በራሱ ሥልጣን አለው የሚል አስተሳሰብ በማስረጽ ይዋጋል። በተመሳሳይ መልኩ የካህናትን ሥልጣን መንጋውን ለመጠበቅ እንዳልተሰጣቸው አድርጎ ይዋጋል። ዲያብሎስ ስህተቱን ተከታትሎ የሚያርምበትን ጠባቂ አይፈልግም። እግዚአብሔር ግን እንዲህ ይላል። "የሰው ልጅ ሆይ ፤ ለእስራኤል ቤት ጠባቂ አድርጌሃለሁ ፤ ስለዚህ የአፌን

የሚያገለግሉ ባሮች ቢሆኑም እንዳይረክሱ ተለይተው መመገብን ከመጠየቅ ወደ ኋላ አላሉም። ልቦናዎቻቸውና ነፍሶቻቸው ነፃና ማንም የማይገድባቸው በመሆናቸው ለፈቃደ እግዚአብሔር እንጂ ለብዙኃኑ ፈቃድ አላዘነበሉም።

ስለሆነም አንተም ደፋር ሁን፤በዓላማህ ጽና የብዙኃኑም ዝንባሌ የተሳሳተ ከሆነ ተቃወመው። ለዲያብሎስ ምክሮችና ማስፈራሪያዎች እጅ አትስጥ። ከአንተ በእድሜ የሚበልጡ ታላላቅ ሰዎች ማንኛውንም የተሳሳተ ድርጊት ሲፈጽሙ ብታይ እንኳ አትፈጽም። የተመረጡት እነርሱ ናቸውና በትክክለኛዋ መንገድ ላይ የሄዱት ጥቂት ቢሆኑም ተስፋ አትቁረጥ። ጌታችን ይህን አስመልክቶ እንዲህ ብሏልና "ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ መንገዱም የቀጠነ ነውና፤የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።" ማቴ 7፥14። የብዙኃኑ በሐሰት ጎተራ መግባት ሐሰትን እውነት እንደማያደርጋት አስተውል! የተሳሳተው ተሳስቷል ይባላል እንጂ የብዙኃኑ መሳሳት ስህተቱን ሊያስተካክለው አይችልም። እውነተኛው መንገድ አስቸጋሪ በመሆኑ በዓላማቸው የጸኑ ጥቂቶች እንጂ ሁሉም ሊጓዙበት እንደማይችሉ የተረጋገጠ ነው። ዲያብሎስ በሁሉም ውስጥ ፍርሃትን ስላሰረጸ አንተ አትፍራ። ብዙኃኑ ፋሽን በመከተል፣በመዝናናት፣ በተድላና በደስታ ቢጠመድ አንተ አትጠመድ። ሰዎች የአነጋገር ዘይቤያቸው ከበፊቱ እየተቀየረ ሲሄድ ከተመለከትህ አንተ አነጋገርህን አትቀይር። እንዲህ የሚያደርገውን ይህን ትውልድ የምትቋቋምበት አቅምህ እየደከመ ከሄደ ከመዝሙረኛው ጋር "አቤቱ አንተ ጠብቀን ፤ ከዚህችም ትውልድ ለዘላለም ታደገን።" በል። መዝ 11፥7። የዚህ ዓለም ማዕበል ጠልፎ ቢወስድህ እንኳ እግዚአብሔር ያድንህ ዘንድ ይቻለዋል።

16. መፈታተን።

ከመጀመሪያው ኃጢአት አንስቶ ዲያብሎስ ታዳኞቹን ለማጥመድና ለመጣል ፈተናን እያቀረበ መፈታተኑን አላቋረጠም። ለቀደሙት ወላጆቻችን ያቀረበው የመጀመሪያ ፈተና "እንደ እግዚአብሔር መልካምንና ክፉን የምታውቁ ትሆናላችሁ።" (ዘፍ 3፥5) የሚል ነበር። በመቀጠልም ሰዎችን "በሥጋ ምኞት፤የዓይን አምሮትና ስለ ገንዘብ መመካት" (1ኛ ዮሐ 2፥16) ይፈታተን ጀመር። ንጉሥ ሰሎሞንንም በዚሁ ፈትኖታል። መክ 2፥1-10። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስንም በገዳመ ቆሮንቶስ በስስት ፣ በትዕቢትና በፍቅረ ንዋይ ፈትኖታል። ማቴ 4። አምላካችን ግን ዲያብሎስን አሳፍሮ መልሶታል። የዲያብሎስ ፈተናዎች ቀድሞ የሚያዘነብሉውን ወይም ሊያዘነብል የሚችለውን የሰዎችን ልቦና ነው የሚያጠምዱት። የማያወላውል ጽኑ ልቦና ያለው ግን እንዲህ ያሉትን ፈተናዎች ይቃወማል እንጂ አይፍረከረከም። ንግሥቲቱ ኤልዛቤል አስቀድማ ንጉሥ አክአብን በቍጥጥር ሥር አድርጋ እንደነበረ ሁሉ ንጉሥ ኢዩንም እንደዚያው ለመቆጣጠር ተኳኩላ ነበር። "ዓይኗን ተኳለች ፤ራስዋንም አስጌጠች።" 2ኛ ነገ 9፥30። ይሁን እንጂ ኢዩ በዚህ የሐሰት ውበት አልተፈተነም። በንቀት ዓይን





ከተመለከታት በኋላ ከሰገነቱ ላይ ወደ ታች ወርውረው እንዲጥሏት አዘዘ እንጂ።

አንዳንድ ጊዜ ዲያብሎስ ፈተናዎቹን የልብ ትርታን የማድመጥን ያህል አጢኖ የሚያቀርባቸው ይመስላል። ታዳኙ በቀረበበት ፈተና መድከም አለመድከሙን ጠጋ ብሎ ትርታውን ያዳምጣል። ጠጋ ብሎ ሲያዳምጥ አለመደንገጡን ከተመለከተ ምንም እንኳ ኢየሱስ ክርስቶስ ቢያሸንፈውም ልክ በእርሱ ላይ እንዳደረገው ሌሎች ፈተናዎችን እያፈራረቀ በዚያ ሰው ላይ ያቀርባል። ዲያብሎስ በዚህ ረገድ ረዘም ያለ የሥራ ልምድ ስላለው ለእያንዳንዱ ሰው የሚስማማውን ፈተና ለመምረጥ ብዙ አይቸገርም። አንድ ሰው የሚወደውን ነገር ስለሚያውቅ በዚያ በሚወደው ነገር ይፈትነዋል። ኢየሱስ ክርስቶስን በዳቦ የፈተነው መራቡን ስላወቀ ነበር። " . . . በኋላ ተራበ።" ማቴ 4፥2። ንጉሥ ሳዖልንም የሚያማክረው ማጣቱን ከተመለከተ በኋላ ነበር በመናፍስት ጠሪ የፈተነው። ቀዳ ሳሙ 28፥4-7። እስራኤላውያንንም በወርቅ ጥጃ የፈተናቸው ሙሴ ወደ ሲና ተራራ በወጣበት መንፈሳዊ አመራር በጠፋበትና ለትንቢት ክብር በጎደለበት ምቹ ጊዜ ነበር። ዘጸ 32፥1-4።

ብዙ ጊዜ የዲያብሎስ ፈተና ከማንኛውም መንፈሳዊ ተግባርና ከንስሐ የሚያደናቅፍ ስለሆነ ጠንካራና ውጤታማ ነው። አንድ ሰው ባለው ኃይል ሁሉ ቆርጦ ንስሐ ለመግባት ሲነሳ ከዚህ ቀደም ለረዥም ጊዜ የተመኘውን ነገር ግን ብዙ ጊዜ ሞክሮ ያጣውን ኃጢአት ይሰጠዋል። በራሱ የመጣ ይመስል እንዴት እንደመጣ በማያስተውለው መልኩ ድንገት ከፊት ለፊቱ ያስቀምጥለታል። በዚያም ተሸንፎ ይወድቅ ዘንድ ሊፈታተነው ይጀምራል። ለምሳሌ አንድ ሰው ክርስትናውን የሚፈታተኑ መጻሕፍትን ማንበብ ያቁም እንበል። በዚያው ቀን ዲያብሎስ ይህ ሰው ቀደም ሲል ለረዥም ወራት ሊገዛው ጓጉቶ ሲፈልግ ያጣውን መጽሐፍ በአንድ ጓደኛው እጅ ይልክለታል። በዚያ መጽሐፍ ውስጥ በተጻፉት ፈተናዎች ፊት ራሱን ደካማ ሆኖ ስለሚያገኘው ያነበውና ይወድቃል። አንድ ወጣት ለዝሙት ንስሐ ቢገባ ኃጢአቱ በራሱ ሲፈላለገው ይገኛል። ይህ ምስኪን ሰው ሊያልፈው የማይችለው አጋጣሚ እንደሆነ አድርጎ ይረዳል። ዲያብሎስም "አጋጣሚውን ተጠቀምበት! ከዚያ በኋላ ንስሐ ትገባለህ።" ይለዋል።

ስለሆነም ዲያብሎስ አንድ ሰው ከኃጢአት መሸሹን ሲመለከት በቀስሉ ላይ የትኛው ቦታ የበለጠ እንደሚጠዘጥዘው በሚገባ ስለሚያውቅ እጅግ ከባዱን ፈተና ያመጣበታል። ስለዚህ ንስሐ ከገባህ በኋላ ያ ኃጢአት በሚያስደንቅ ሁኔታ ከተከታተለህ "መልካም አጋጣሚ" በማለት ፈንታ "ይህ በትክክል የዲያብሎስ ሥራ ነው።" በል። ይህ እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ ድንገት የሆነ ነገር ሳይሆን በሚገባ የተጠና የዲያብሎስ ዕቅድ ነው። ይህን የሚገልጥልንና እንድናመልጠው የሚረዳን አምላካችን ስሙ የተመሰገነ ይሁን! ቅዱሱና ኢትዮጵያዊው መነኩሴ በሽሂት ምድረ በዳ

እንዲሆን ነው። ከዚህ በኋላ ግን ድንገት ከበድ ያለውን ውጊያ በመክፈት ሊጥለው ይመጣል። እንዲህ በማድረግ ንስሐ ቢገባ እንኳ ተመልሶ ስለሚበድል የጽድቅ ሕይወት ለመምራት ብቃት እንደሌለው አድርጎ ራሱን እንዲቆጥር ያሳምነዋል። አለበለዚያም የሰጠውን ኃጢአት ለጊዜው ይነጥቀውና እንዲናፍቀው ያደርገዋል። ይህን የሚያደርገውም አንድ ሰው ለረዥም ጊዜ አንድ ዓይነት ኃጢአትን እየደጋገመ በመሥራቱ ተሰላችቶ ሊጠላው ስለሚችል ነው። በዚህ ጊዜ ዲያብሎስ ለጥቂት ጊዜ ይነጥቀውና ያንኑ ኃጢአት እጅግ በከፋ መልኩ አጠንክሮ ባላሰበው ዘዴና ሰዓት በማምጣት በቀላሉ ይጥለዋል። ይህም ማለት ዲያብሎስ ኃጢአትን እንዳንዋጋው መንፈግ እንዲጥለንም መስጠት ይችላል ማለት ነው። እንዲህ በማድረግም በሰዎች ነፍስ ያላግጣል። ነፍሳችን እንድትነሳና እንድትወድቅ በማድረግ ጽናቷን ያናጋል። የእግዚአብሔር ልጆች ግን ምንም እንኳ ዲያብሎስ በፍርሃት ተስፋ በመቁረጥና ቅድስና ከአቅማቸው በላይ እንደሆነ እየገመቱ እንዲኖሩ ቢፈልግም እንዲህ ባለው ውጊያ ወደበለጠ ጥንቃቄ ራስን መግዛትና ትሕትና ያድጋሉ። ይሁን እንጂ ዲያብሎስ በዚህ የውጊያ ስለቱ አእምሮን ብቻ ሳይሆን መላ ሕዋሳትን መዋጋቱን "ክርስትና ወደ ላቀ ሞገስና ብቃት የሚደርስበት ሃይማኖት ቢሆንም ይህ የላቀ ሞገስና ብቃት በተግባር ሊገለጽ ስለማይችል ማንም አያገኘውም።" በማለት ይቀጥላል። በዚሁ ጉዳይ ላይ ምሳሌ በመሆን ሊጠቀሱ የሚችሉ ጻድቃንና ቅዱሳን አባቶችን ግን ይሸሽጋቸዋል።

## 20. ውጪያዊ መልካም ምግባራትን ማጉላት።

ዲያብሎስ ሰዎች መንፈሳዊ የሆኑና የሚታዩ መልካም ምግባራትን በሽሽግ ከማከናወን ይልቅ በገሃድ እንዲከናወኑ ያባብላል። እዚህ ላይ "የሚታዩ" የሚለው ቃል ለሰውየው ብቻ እንጂ ለሌሎች መታየትን አያጠቃልልም። እንዲህ ባሉ ውጪያዊ ምግባራት ሰውየው ራሱን እንዲያደንቅና የደረሰበት ደረጃ ላይ ያልደረሱትን በንቀት እንዲመለከት ያደርገዋል። ይህ ውጊያ በመነኩሱም ሆነ በምዕመኑ ላይ ያነጣጥራል።

አንድ መነኩሴ መንፈሳዊ ተጋድሎውን ሲጀምር ዲያብሎስ በጾም ፣በስግደት፣በንቃት፣በአርምሞና በባዕት በመጽናት ግልጽና በውጪ በሚታዩ ምግባራት ላይ ብቻ እንዲያተኩር በማድረግ በውስጥ ሊገኙ የሚገባቸውን ደስታ ፣ ሰላም ፣ ቅድስና ፣ ትሕትና፣ዝግታና የመሳሰሉትን እንዲዘነጋ ያደርገዋል። በጾም ወቅት ዲያብሎስ ሥጋዊውን ምግባር እንጂ መንፈሳዊውን አይዋጋም። በዚህም ጾመኛው ከምግብ የሚከለከልበትን ጊዜና ርዝመቱን ስለሚበሉ ምግቦች፤ከላመ ከጣመ ስለመከልከልና የሚጠጣ ውኃን ብዛት ስለመቀነስ ብቻ እንዲያሰላስልና በሥጋዊው ምግባር ላይ እንዲያተኩር ያደርገዋል። በዚህም የጾምን መንፈሳዊ ጥቅምና ምግባራት ማለትም ትዕግስትን በመንፈስ መጠንከርንና ራስን በሁሉም መንገድ ስለመግዛት ይረሳል። ዲያብሎስ ከላይ የተገለጸው ሥጋዊ የአጿጿም ዘዴ ለሰውየው ምንም መንፈሳዊ ጥቅም እንደማያስገኝለት ከማወቁም በላይ ይህ ዘዴው





ወደ ፊት ሰውየው ጾምን ሙሉ ለሙሉ እንዲተው ጥርጊያውን እንደሚከፍትለት ይረዳል።

ስግደትንም በተመለከተ ተመሳሳይ ሁኔታን ይፈጥራል። በዚህ ጊዜም ሰውየው የስግደቱን ቁጥር እንዴት መጨመር እንደሚችል በማተኮር ላይ ብቻ እንዲወሰን ያደርገዋል እንጂ በስግደቱ ጊዜ ነፍሱና ግንባሩ ወደ ምድር መጠጋታቸውን እንዲያስብ አያደርገውም። መዝ 118፡25። በስግደት ጊዜ በተጓዳኝ ሊደረጉ የሚገባቸውን ጥልቅ መንፈሳዊ ተመስጦና ጸሎትም ያስረሳዋል። ምንም እንኳ የስግደቱ ቁጥር የበዛ ቢሆንም ምንም ጥቅም የማያገኝበት የሰውነት እንቅስቃሴ ሆኖ ይቀራል። ይህም ወደ ከንቱ ኩራት ይመራዋል።

በተባህትዎ መኖርንም ባህታዊው ስለ ውጪያዊው ገጽታው እንጂ ስለ መንፈሳዊነቱ እንዳይጨነቅ በማድረግ ይዋጋዋል። በተባህትዎ ከሰው ተለይቶ የሚኖረው ባህታዊ አእምሮው ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ የሚሆንበትና ለዓለሙ ሙሉ ለሙሉ የሚሞትበት መንፈሳዊ ሕይወት መምረጡን ሳይሆን አንድ የጉዞ ምርጫ መከተሉን ብቻ እንዲያስብ ያደርገዋል። ዲያብሎስ እንዲህ ያለውን ባህታዊ ከሰው ተለይቶ በዋሻ በመኖሩ ብቻ እንዲደሰት ያደርገዋል። ከዚህ በኋላ ይህ ባህታዊ በዋሻው ውስጥ ሊያደርጋቸው የሚገቡትን መንፈሳዊ የተጋድሎ ተግባራት ፍጹም በመዘንጋት ልቦናው በገዳሙና በውስጡ ባሉት መናንያን ላይ እንዲታበይና እንዲቆጣ ያደርገዋል። ቅዱስ ይስሐቅ የተባለው አባት "አንድ በዋሻው ውስጥ እንዴት መቆየት እንደሚገባው የማያውቅ ነገር ግን ለአምሳ ዓመታት የቆየ ሰው ሊገኝ ይችላል።" በማለት ተናግሯል።

ስለ ተባሕትዎ የተባለው ለዝምታም ይገለጻል። አርምሞ ወይም ዝምታ አንድን ሰው ከእንደበት ኃጢአት በመከልከል ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ እንዲነጋገር ዕድልን የሚከፍት መንገድ ነው። ይሁን እንጂ አንድ ሰው ዝም በማለቱ ብቻ ሐሴት የሚያደርግ ከሆነ በአንደበቱ ይፈጽመው የነበረውን ሰዎችን መርገም፣ቁጣ፣ንዴትና ግትርነት በአእምሮው ሊፈጽመው ይችላል። በተመሳሳይ መልኩ በዝምታው መካከል ልቦናው ከእግዚአብሔር ጋር የማይነጋገር ከሆነ እንዲህ ያለው ዝምታ መንፈሳዊ አይደለም።

በተመሳሳይ መልኩ አንድ ሰው አሁንም በድንግልናው ብቻ የሚደሰት ሊሆን ይችላል። ይህ ሰው ድንግልናው ከጋብቻ እንዳራቀው ብቻ እንጂ በልቦናው ድንግል በአእምሮውም ያልረከሰ መሆን እንዳለበት አይገነዘብም። የድንግልና ዋናው ቁም ነገር የፍቅርን ሁሉ ቅድሚያ ለእግዚአብሔር መስጠት ነው። ይህ ካልሆነ ግን ያ ሰው ያለው ድንግልና ከውጪ ብቻ የሚገለጽ እንጂ ከውስጥ (ከልቦናው) ባዶ ነው። የእኛም ዋና ዓላማ ከልብ የሚወጣው ውሳጣዊ መንፈሳዊ ተግባር ላይ ማተኮር መሆን አለበት። እርሱ ከሁሉም ይበልጥ ጠቃሚ ነውና። እግዚአብሔርም "ልጄ ሆይ ፤ ልብህን ስጠኝ።" ነው ያለው። ምሳ 23፡26። ስለሆነም ሰው ሁሉ ከልብ

ንጽህና ከእግዚአብሔር ፍቅርና ከውሳጣዊ ምግባራት መጀመር አለበት። ከንጹህ ልቦና የተቀደሰ ጸሎት ፣ ትክክለኛ ስግደት ፣ መንፈሳዊ አገልግሎትና ሌሎችም መልካም ምግራት ይወጣሉና። በውጪ ለሚታዩ ምግባራት የሚጨነቅ ሰው የእርሱ ሕይወት በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊ ሆኖ ሳለ ከአንዱ ንሰሐ አባት ሌላው ይሻላል በማለት እያንቋሸሸ መቀያየሩ የሚያስደንቅ ነው።

## 21. ቁጡ ማድረግ።

ዲያብሎስ ይህን በጻድቁም ሆነ በኃጥኡ ላይ ያነጣጥራል። በዚህ ረገድ ሰውየው በሚያየው ስህተት ላይ ሁሉ እንዲቆጣ በማድረግ ያለማምደዋል። በተመሳሳይ መልኩ ይህ ሰው የእርሱን አመለካከት የሚቃወሙትን ሁሉ ይቆጣቸዋል። ከዚህ ቁጣ በስተጀርባም ኩራትና ልበ ደንዳናነት ተሸሽገው ይመጣሉ። በዓለሙ መካከል በትህትናቸውና በዝግታቸው የሚታወቁ ብዙ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። በአንፃሩ ግን ከመንፈሳውያን ሰዎች መካከል አንዳንድ በጣም ቁጡና በሃይማኖት ስም ምንም ነገር የማያስደስታቸው ሰዎችን እናገኛለን። እነዚህ ሰዎች ከእነርሱ በቀር እግዚአብሔርን የሚያውቅና መንገዱንም የሚከተል ሰው ያለ አይመስላቸውም። በዚህ ቁጡነታቸውም ማንም ተራ ምዕመን ሊፈጽማቸው የማችላቸውን ብዙ ስህተቶች ሲፈጽሙ ይስተዋላሉ። በዚህም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች የሆኑትን ትዕግስትና በጎነትን እንዲዘነጉ ያደርጋቸዋል።

## 22. መሰናክሎችን ማኖር።

ማንኛውም መንፈሳዊ ድርጊት በዲያብሎስ ለሚዘጋጁ መሰናክሎች የተጋለጠ ነው። ሐዋርያው "ፈቃድ አለኝና፤መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም።" (ሮሜ 7፡18) በማለት እንደተናገረ አንድ ሰው መልካም የሆነውን መንፈሳዊ ተግባር ለመፈጸም ከተነሳሳ በኋላ ያ መልካም ምግባሩን እንዳይፈጽመው ዲያብሎስ ባለው ኃይል ሁሉ ይቃወመዋል። መሰክሎቹም ድንገተኛ አጋጣሚዎች፣ዝንጋዔ (መርሳት)፣ጊዜ ማጣትና የጠላት ወይም የሐሰተኛ ወንድሞች ተቃውሞ ሊሆኑ ይችላሉ። በእነዚህ መካከልም ዲያብሎስ ብቅ ብሎ "ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ቢሆን ፤መፍትሄውን ሊሰጥህ ይገባው ነበር" ይላል። ወይም ደግሞ መልካም ምግባር ስላለው ሰው ወደ ሌሎች በመሄድ "ይህ ሰው የእግዚአብሔር ሰው ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ያሳልፍለት ነበር።" በማለት በእነዚህ አባባሎች በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ይመታል።

## 23. ዓይናፋር ማድረግ ፤ በይሉኝታ መያዝ።

ዓይናፋርነትን ግለሰቡ በአግባቡ ከተጠቀመበት መልካም ምግባር ነው። ይሁን እንጂ ዲያብሎስ አላግባብ ሰዎችን ወደ ውድቀት ይመራበታል። ምናልባት አንድ ሰው ጸያፍ የሆኑ ቃላትን በመጠቀም የአንድን ሰው ክብር





በሚያቃልሉና ሊነገሩ የማይገቡ ወጎችን ከሚያወጉ ሰዎች መካከል ሊቀመጥ ይችላል። ይህ ሰው እንዲህ ያለው ነገር ያልጠበቀው በመሆኑ ከመካከላቸው ወጥቶ ለመሄድ ያስባል። በዚህ ጊዜ ግን ዓይናፋር የሚያደርገው ዲያብሎስ ተገልጦ በይሉኝታ ቁጭ እንዲል ያስገድደዋል። በመቆየቱም አእምሮውን ሊገቡ በማይፈልጋቸው ክፉ አሳቦች ያጨናንቃል። አሁንም ስለ ዓይናፋርነት ሲል አንድ ሰው አእምሮው የማይቀበለውን ምርጫ ሊያጸድቅ ይችላል። በሌላም በኩል አንድ ሰው ሊወስንበት በማይገባው ሰው ላይ የተበየነን ፍርድ ወይም ውሳኔ ስለ ዓይናፋርነት ሲል በልቡ ባያስበውም ተስማምቶ ይፈርምበታል። ድምፀ ተአቅቦ ለማድረግ ቢሞክርም እንኳ ይኸው ዓይናፋርነት (ይሉኝታ) ያግደዋል።

በተመሳሳይ መልኩ የብዙኃኑ ዝንባሌ ከእርሷ የተለየ የሆነ አንዲት ልጃገረድ ዲያብሎስ ቀሚስ በመልበሷ ሊደሳፍራት ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ ዲያብሎስ በመንፈሳዊነት በጸሎትና በጾም ታዋቂ እንዳትሆኚ በሚል ሰበብ ያሳፍራታል። አልፎ ተርፎም መስቀል እንዳታስር ሊያሳፍራት ይችላል። በተመሳሳይ መልኩ አንድ መንፈሳዊ ወጣት በአስተማሪው ወይም በአለቃው የተጋበዘውን ሲጋራ እምቢ ለማለት ሊያፍር ይችላል። በዲያብሎስ አሳፋሪነት ሊከተሉ የሚችሉ ኃጢአቶች ምንኛ የበዙ ናቸው!? መንፈሳዊ ሰው ግን እንደዚህ ዓይነቱን ዓይናፋርነት ሊቃወመው ይገባል። ይህ ሰው ሁኔታዎች በጣም አስቸጋሪ ሲሆኑበት የእርሱን መንፈሳዊ አቋም ለሌሎች ጠንክሮ ማሳመን አሊያም ከእንደዚህ ዓይነቱ ፈታኝ ሁኔታ በዘዴና በጥበብ የሚያመልጥበትን ቀዳዳ ማዘጋጀት አለበት። ሌላው ሁሉ ቢቀር እንደዚህ ወዳለው ፈታኝ ሁኔታ የሚመራውንና ከዓይናፋርነት ጋር ግብግብ ወደሚገጥምበት አዝማሚያ የሚወስደውን ወዳጅነት ከወዲሁ መራቅ መቻል አለበት። ኃጢአተኞች መንፈሳዊነትን ለማውገዝ ደፋርና ዓይናውጦች ሲሆኑ መንፈሳውያኑ በመንፈሳዊነታቸው ማፈራቸው የሚያስደንቅ ነገር ነው።

## 24. ጊዜን ማስባከን።

አማኝ ዓይናፋር በሚያደርግ ዲያብሎስ አንዳንዴ እንደሚፈተን ሁሉ በሌላ ጊዜም ጊዜን በከንቱ በሚያስባክን ዲያብሎስ ይፈተናል። የሰው የሕይወት ዘመን ዲያብሎስ በከንቱ ሊያባክነው የሚወደው ጊዜ ነው። ምንም አድርግ ምን የባከነ ጊዜ ማለት በነፍስህም ሆነ በሥጋህ እንዲሁም በአእምሮህ አንተም ሳትጠቀም ሌሎችንም ሳትጠቅም ያለፈብህ ጊዜ ማለት ነው። በዚያ ጊዜ ውስጥ ኃጢአትን ባታደርግ ለሰይጣን አይጨንቀውም። ለእርሱ ቁም ነገሩ ያ የሕይወትህ ክፍለ ጊዜ ለአንተም ሆነ ለሌሎች ፍሬ ሳይገኝበት በከንቱ ያለፈ ጊዜ መሆኑ ላይ ነው። በዚህ መልኩ የሚባክኑ ጊዜዎች ደግሞ የተለያዩና ብዙ ምክንያቶች ያሏቸው ናቸው።

ከእነዚህም መካከል ያለ ምንም ዓላማ ለረዥም ጊዜ የሚደረጉ ፋይዳ ቢስ ውይይቶች አሉ። በዚህ መልኩ የሚደረጉ ውይይቶች ከክርክርና ከጭቅጭቅ ባሻገር ናላን ከማዞር ሌላ ጠቀሜታ ስለሌላቸው ጊዜን በከንቱ

ያባክናሉ። ከዚህ በተጨማሪ ሽርሽርና የማታ ጭፈራ፣አላስፈላጊ ቅንጦት፣ ቧልትና ቀልድ በሕይወትህ በጣም ብዙ ጠቃሚ ሥራዎችን ልታከናውንበት በምትችለው ጊዜ ላይ ነው ደንቃራ የሚሆኑብህ። አንዳንዶችም "ጊዜ እንግደል" በሚል ሰበብ በየቡና ቤቱ ብዙ ጊዜዎችን ያሳልፋሉ። ጊዜውን በከንቱ በማሳለፉ የሚስማማ ሰው ለሕይወቱ የሚሰጠው ዋጋ በጣም አነስተኛ በመሆኑ የተስማማ ሰው ነው።

25. ረዳቶችን ማስማራት።

ዲያብሎስ ከክፉት ሠራዊቱ፣ከምትወዳቸው ጓደኞችህ፣ከዘመዶችህ ከምታውቃቸው አሊያም ከእንግዶች መካከል ረዳቶች ስላሉት በውጊያው አውድማ ብቻውን አይሰማራም። ዲያብሎስ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ በአንዳንድ ሰዎች አንደበት ላይ አድሮ "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ ከመስቀል ውረድ" ብሎታል። ማቴ 27:40። "ለሰዉም ቤተ ሰዎቹ ጠላቶቹ ይሆኑበታል።" (ማቴ 10:36) ተብሎ እንደተጻፈ ዲያብሎስ ቤተሰቦችህን ጠላት አድርጎ ማስነሳት ይችላል።

ዲያብሎስ ከዘመዶችህ መካከል በጣም የምትወዳቸው ሰዎች ሕይወትህን ሊያበላሹ የሚችሉበትን መንገድ በመምከር ያስነሳቸውና መንፈሳዊ ምግባራትህን ከማከናወን በመታቀብ አምልኮትህን እንድታስታጉል ሊያደርግ ይችላል። እነዚህን ሰዎች እንዲያፌዙብህ አድርጎ ሊያሰማራቸውም ይችላል። ስለዚህ ራስህን ጠብቅ! የምታገኛቸውን ማናቸውንም ዓይነት ምክሮች ፈትንና መልካም የሆነውን ብቻ ያዝ። 1ኛ ተሰ 5:21። እነዚህ ወገኖችህን ግን "እናንተ የሰይጣን መልእክተኞች ናችሁ" ከማለት ራስህን ከልክል። ክፉ ባልንጀራ ከዲያብሎስ ወገን ሊሆን ይችላል። "ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን ዓመል ያጠፋል።" ይላልና። 1ኛ ቆሮ 15:33። ስለዚህ ምንጊዜም ቢሆን በክፉዎች ምክር ባለመሄድ፣ በኃጢአተኞች መንገድ ባለመቆምና በዋዘኞችም ወንበር ባለመቀመጥ የመዝሙረኛውን የመጀመሪያ መዝሙር የሕይወትህ መመሪያ አድርግ። መዝ 1። እነዚህ ሁሉ ዲያብሎስ ተቀምጦ መመሪያ የሚሰጥባቸው ወንበሮች ናቸውና።

ዲያብሎስ ራሱ በአካል ተገልጦ ይዋጋኛል ብለህ ግን አታስብ። ይህ እግዚአብሔር መንፈሳዊ ብቃቱ ላላቸውና ሊቋቋሙት ለሚችሉት አባቶች ፈቅዶ የሚያደርገው ነገር ካልሆነ በስተቀር ለሌሎች እጅግ ከባዱ ጦርነት ነው። ዲያብሎስ ሊተነኩስህ ሲፈልግ የሚተነኩስህን ሰው ይልክብሃል። ያ ሰው ደግሞ የዲያብሎስ ሥራ አስፈጻሚ ወይም ረዳት ነው። ወደ ኃጢአት የሚመራህንና በድለህ እንድትወድቅ ሊፈታተንህ ሲፈልግም ልክ እንደ ተንኳሹ የሚፈታተንህን ይልክብሃል። በአጠቃላይ ኃጢአተኞች በሙሉ የዲያብሎስ ድጋፍ ሰጪዎች ናቸው። ከእነዚህም መካከል የቧልትና የፌዝ ቦታዎች፣በእግዚአብሔር መኖር የማያምኑ ፈላስፎች፣ጥርጣሬን የሚዘሩ ሰዎችና ክፉን የሚያደርጉ ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ናቸው። እንደነዚህ ስላሉት ነቢዩ ዳዊት ከወገኖቹ ጋር በመሆን "አቤቱ የአኪጦፌልን ምክር ስንፍና





አድርገው እንድትለውጥ እለምንሃለሁ።" ብሏል። 2ኛ ሳሙ 15:31። በዚያን ወቅት አቤሴሎም በአባቱ በዳዊት ላይ በተነሳሳ ጊዜ አኪጦፌል ያቀበለው ምክር ለዳዊትና ለሕዝቡ ጎጂ ምክር ነበር። እንዲሁ ዲያብሎስ ዓለሙን በኑፋቄና በመወላወል ማዕበል ለመምታት ሲፈልግ ራሱን በአካል መግለጥ የለበትም። ይልቁንም ይህን ኑፋቄውን ባሉት የሰው ረዳቶች በማስተማር በማስፋፋትና ሌሎችም በዚሁ ጥርጥር እንዲያምኑ በማድረግ ይጠቀማል እንጂ።

ስለዚህ በማንኛውም ጊዜና ሰዓት እግዚአብሔር ከዲያብሎስ ደባዎች እንዲያድነን መጸለይ አለብን። ከዲያብሎስ ብቻ አይደለም ከመላእክቱ፣ከሠራዊቱ፣ከአጋሮቹና ከረዳቶቹ፣ከጠላት ኃይልና ፈቃዱን በምድር ላይ ከሚፈጽሙ ሁሉ እንዲያድነን መጸለይ አለብን።

የዲያብሎስ ደባዎች ወይም ስለ ዲያብሎስ የምናውቀው ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ብቻ አይደለም። የክፋት ጎተራው ምንጊዜም ቢሆን አይሟጠጥም። ደባዎቹም አያልቁም። ቀድሞም አሁንም ወደፊትም ደባዎቹ አሉ - ይኖራሉም። ደባዎቹን በየጊዜው ይለዋውጣል። እግዚአብሔር ምህረቱን በእኛ ላይ አድርጎ ከዲያብሎስና ከደባዎቹ ሁሉ ያድነን! አሜን።

# ምዕራፍ አራት

## 1. የዲያብሎስን ውጊያዎች እንዴት ማሸነፍ ይቻላል?

ቀደም ባሉት ሁለት ምዕራፎች ስለ ዲያብሎስ፣በውጊያው ውስጥ ስለሚታወቅባቸው ባህርያቱና ስለ ደባዎቹ የተነጋገርነው እንድትፈሩት ለማድረግ ሳይሆን ራሳችሁን እንድትጠብቁ ነው። ምንም እንኳ ዲያብሎስ ብልህና ኃይለኛ ቢሆንም እርሱን ማሸነፍ ይቻላል። ይህ እንዲያውም በጣም ቀላል ነገር ነው።

### ሀ. ማሸነፍ ይቻላል።

ምንጊዜም የዲያብሎስን ውጊያዎች ማሸነፍ ከባድ እንደሆነ አድርገህ የምታስብ ከሆነ ትዝላለህ፣ትደክማለህ፣እጅህን ትሰጣለህ፣ ትወድቅማለህ። ነገር ግን ዲያብሎስ በሚዋጋህ ጊዜ እንደምታሸንፈው እርግጠኛ ከሆንህ እግዚአብሔር ከምትችለው በላይ እንድትፈተን (እንድትወጋ) አይፈቅድምና ታሸንፈዋለህ። ዲያብሎስን ተዋግተው ድል ስላደረጉት ቅዱሳን አባቶች ዘወትር በተመስጦ አስብ። ዲያብሎስ እጅግ በጣም ፈታኝ ውጊያ ቢከፍትበትም ድል ስላደረገው ስለ ጻድቁ ስለ ዮሴፍ ታሪክ አስታውስ። በዲያብሎስ ውጊያ ከወደቁት ከዳዊትና ከሶምሶን ታሪክም ትምህርት መቅሰም ትችላለህ። የእነዚህ አባቶች መውደቅ መንስኤው ምን እንደሆነ እወቅ። የወደቁ አባቶች ታሪክ ተጽፎ የተቀመጠው ከእነርሱ አወዳደቅ ተምረን ራሳችንን እንድንጠብቅ ለእኛው ጥቅም ሲባል ነው። በመጽሐፍ ቅዱስና በታሪክ ብዛት ያላቸው ዲያብሎስን የማሸነፍ ገድሎች ተጽፈው እናገኛለን።

ምንም እንኳ ሰው እጅግ በከፋ ኃጢአት ቢወድቅም ንስሐ መግባት እንደሚችል እናውቃለን። ይህ በሶምሶንና በጠቢቡ ሰሎሞን እንዲሁም በሌሎች ታላላቅ ሰዎች ታሪክ ውስጥ በግልጽ የታየ ነው። ስለዚህ ከባድ ኃጢአት ሠርተን ስንጎሰቁል ዲያብሎስ ተስፋ ለማስቆረጥ ቢዋጋን እነዚህን የንስሐ ታሪኮች በማስታወስ ልንበረታታና ልንጽናና ይገባል። ቅዱስ እንጦስ ያን ያህል ከባድ የተለያዩና ብዛት ያላቸው ውጊያዎች ቢከፈትበትም አሸንፏል። ከሌሎች ቅዱሳን አባቶችም ተመሳሳይ ትምህርት መውሰድ እንችላለን።

እግዚአብሔር ሲፈጥረን ኋላም የእኛን ሥጋ ሲለብስ ይህ አፈጣጠራችንን ቀድሶታል። ለዚህም ነው በቅዳሴ ጎርጎርዮስ "እኔነቴን በአንተ ቀድሰህዋል።" በማለት የምናመሰግነው። ይህ እኛነታችን ዲያብሎስን ለማሸነፍ ታላቅ ብቃት አግኝቷል። መንፈስ ቅዱስ የሚያድርበት የእግዚአብሔር ቤተ መቅደሶች ነን። 1ኛ ቆሮ 3፡16። ከውኃና ከመንፈስ በመወለድም የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል። ዮሐ 3፡3-5። የተሰጠንን ኃይል ስናስታውስ በዙሪያችን የከበበንንም ተጨማሪ መንፈሳዊ ኃይል ማስታወስ





ይገባናል። የእግዚአብሔር መንፈስ ከእኛ ጋር ስላለ በውጊያው አውድማ ላይ ብቻችንን አለመሆናችንን መርሳት የለብንም። መንፈስ ቅዱስ ስለ ኃጢአት ይወቅሰናል (ዮሐ 16፡8)፤ሁሉን ያስተምረናል (1ኛ ዮሐ 2፡27)፤ወደ እውነት ሁሉ ይመራናል (ዮሐ 16፡13)። ታዲያ እንዴት አድርጎ ነው ዲያብሎስ የመንፈስ ቅዱስ ኅብረትና (2ኛ ቆሮ 13፡14) የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ (1ኛ ቆሮ 16፡23) ከእኛ ጋር እያለ ሊያሸንፈን የሚችለው? የምንኖረውም ከክርስቶስ ጋር እንጂ ብቻችንን አይደለም። (ገላ 2፡20)። ከዚህ በተጨማሪ መዳንን እንወርስ ዘንድ ወደ እኛ የሚላኩና የሚያገለግሉን ቅዱሳን መላእክት በዙሪያችን አሉ። (ዕብ 1፡14)።

ድል ባደረጉና በዙሪያችን ልክ እንደ ደመና በከበቡን ምስክሮች መታጀባችንን ከተመለከትን "ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት" እናስወግድ። ዕብ 12፡1። እንበረታታና እንጽናና ዘንድም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረንን እናስታውስ። "እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።" ማቴ 28፡20። "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?" ሮሜ 8፡31። እያንዳንዳችንንም እንደዚህ ብሎናል። "አልጥልህም አልተውህም . . . በምትሄድበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና።" ኢያ 1፡5፤9። "እኔ ከአንተ ጋር ነኝ ፤ ማንም ክፉ ሊያደርግብህ የሚነሳብህ የለምና አትፍራ።" ሐዋ 18፡10። በውጊያችን ቀናኢ እንሆን ዘንድ እስቲ ተዋግተው ድል ላደረጉት እግዚአብሔር የገባላቸውን ቃል ኪዳን እናስታውስ። ለምሳሌ እግዚአብሔር ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የገባውን ቃል ኪዳን እንመልከት። "እኔ ደግሞ ድል እንደነሳሁ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጥሁ ድል ለነሳው በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ።" ራዕ 3፡21፤3፡5። "ድል ለነሳው ከተሰወረ መና እሰጠዋለሁ።" ፤ "የንጋትንም ኮከብ እሰጠዋለሁ።" ፤"የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ።" ራዕ 2፡17፤28፤10። በእርግጥም እነዚህ ልብን በቅንአትና በኃይል የሚሞሉ ቃል ኪዳኖችን የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ!

ውጊያችንን የሚዋጋልን እግዚአብሔር መሆኑን እስቲ በትክክል እናረጋግጥ። ዲያብሎስ ምንም እንኳ ኃይለኛ ቢሆንም ወሰን በሌለው በእግዚአብሔር ኃይል ፊት ምንም አይደለም። ዲያብሎስ የሚያገሳ አንበሳ ተብሎ ቢሰየምም እግዚአብሔር የዚህን አንበሳ አፍ መልአኩን ልኮ ዘግቶታል። ዳን 6፡22። በእርግጥም "ሰልፉ ለእግዚአብሔር ነው።" 1ኛ ሳሙ 17፡47። "እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል ፤ እናንተም ዝም ትላላችሁ።" ዘጸ 14፡14። የሚዋጋው እግዚአብሔር ስለሆነ ዲያብሎስን በፍጹም አትፍሩት።

### ለ. አትፍራ።

ምንም እንኳ ዲያብሎስ ብልህና ደበኛ ቢሆንም በእግዚአብሔር ልጆች ፊት ደካማ ስለሆነ አትፍራው። ስለ ዲያብሎስ መድኃኒታችን እንዲህ ብሏል። "ሰይጣን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ።" ሉቃ 10፡18።

ቀበሮ ይህን ድምጽ በመጀመሪያ ስትሰማ ትፈራለች ትረበሻለች ትደነግጥማለች። ቀስ በቀስ ትደፋፈርና በዚያ ከበሮ ላይ የማጥቃት እርምጃ ወስዳ ውስጡን ስታየው ባዶ ነው። ከበሮው ያስቃታልም ያስጠላታልም። ይህ ምሳሌ በጣም ግዙፍ መስሎ ከሚታየውና አንዲት እስፒል በትንሹ ስትነካው ወደ ባዶነት ከሚለወጠው ፊኛ ምሳሌ ጋር ይዛመዳል። ዲያብሎስም ልክ እንደዚሁ ነው። ጩኸት ብቻ እንጂ ኃይል የለውም። ሊያስፈራራህ ይሞክራል። ነገር ግን የፈቀደውን ሁሉ በአንተ ላይ ሊያደርግ የሚያስችለው ፍጹም የሆነ ነፃነት የለውም። እግዚአብሔር ዲያብሎስን እንደ ፈቃዱ በወደደው መጠን ሊያግደው ይችላል። በጻድቁ በኢዮብ ታሪክ ውስጥ እንደምንመለከተው ዲያብሎስ እግዚአብሔር በወሰነለት መጠን እንጂ እንደ ራሱ ፈቃድ ኢዮብን አልተዋጋውም። ኢዮ 1 እና 2። ዲያብሎስ ትፈራው ዘንድ እጅግም ኃይል የለውም። በቀላሉ እንኳ ብንወስድ ገጽህንና መላ ሰውነትህን አንድ ጊዜ በትዕምርተ መስቀል ብታማትብ ከአጠገብህ ይጠፋል። ዲያብሎስ ኃያል እንደሆነ አድርገህ እንድትገምተው ይሞክራል። ነገር ግን አትመነው። ምንጊዜም ቢሆን በቅዱሳኑ ፊት ድል ተነስቶ እንደ ተዋረደ አስታውስ! ከሚጥላቸው ሰዎች ውስጥ ሊያስወጡት ኃይል ያላቸው ሰዎች እንዳሉና እንደነዚህ ባሉት በእግዚአብሔር ልጆች ፊት ዘወትር በፍርሃት እየጮኸ በመውጣት እንደሚሸሽም አስብ! በዚህ ዓይነት መልኩ የዲያብሎስን ደካማነት ከተረዳህ በድፍረት ተቃወመው።

ሐ. ዲያብሎስን ተቃወም።

"ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል።" (ያዕ 4:7) የሚለውን የሐዋርያውን የቅዱስ ያዕቆብን ቃል ዘወትር በማስታወስ መመሪያችን ማድረግ መልካም ነው። " . . ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል" የሚለው ቃል የዲያብሎስን ደካማነት ይገልጽልናል። ምክንያቱም ሐዋርያው "ተቃወሙ ከእናንተ ይሸሻል" አለን እንጂ "ተቃወሙ ከእናንተ ይለያል" አላለንምና። ዲያብሎስ የሰውየውን አቋም ለመረዳት የልብ ትርታውን ያዳምጣል። መፍራቱን ከተረዳ እጅግ በመደሰት ያን ሰው አሻንጉሊት ሊያደርገው ይጀምራል። ጠንካራና የሚታገለው ከሆነ ግን እንዳይሸነፍ በመስጋት በፍርሃት ከዚያ ሰው ይሸሻል። ምንም እንኳ ቅዱስ ጴጥሮስ በመልዕክቱ "ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና" በማለት ቢጽፍልንም ቀጠል አድርጎ "በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት" (1ኛ ጴጥ 5:8-9) ስላለን ኃይለኛ ነው ብላችሁ እንዳትታለሉ ይሁን። ይህም ማለት እንደ አንበሳ በማግሳቱ ልትፈሩት ሳይሆን ልትቃወሙት ይገባችኋል ማለት ነው። የዲያብሎስን እንደ አንበሳ ማግሳት ስታስታውሱ የነቢዩ የዳንኤልንም ቃል አስታውሱ። "አምላኬ መልአኩን ልኮ የአንበሶችን አፍ ዘጋ።" ዳን 6:22። ባለህ ኃይል ሁሉ ጸንተህና ጠንክረህ ዲያብሎስን ተቃወመው። እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ መልካም ወታደር ውጊያውን ተቃወም እንጂ እጅ አትስጥ። ባለህ ኃይል ሁሉ እየተዋጋህ የእግዚአብሔርን እርዳታ ጠይቅ። እዚህ ላይ በሰሎሞን የመዝሙር መጽሐፍ ውስጥ የተባለውን ለመጥቀስ እወዳለሁ። "እነሆ የሰሎሞን አልጋ





ናት፤ከእስራኤል ኃያላን ስድሳ ስድስት ኃያላን በዙሪያው ናቸው። ሁሉም ሰይፍ የያዙ ሰልፈኞች ናቸው፤በሌሊት ከሚወድቀው ፍርሃት የተነሳ ሰው ሁሉ ሰይፉ በወገቡ አለ።" መኃ 3:7-8። ስለሆነም ከዲያብሎስ የሚከፈቱብህን ውጊያዎች ሁሉ እንዴት እንደምትዋጋቸው ተማር። ነቢዩ ዳዊትም እንደተናገረ ሰይፍህን በወገብህ ታጠቅ። "ኃያል ሆይ ፤በቁንጅናህና በውበትህ ሰይፍህን በወገብህ ታጠቅ።" መዝ 44:3።

ዲያብሎስ በአሳብህና በስሜትህ ቢዋጋህ ተቃወመው እንጂ እጅህን አትስጠው። የሚሰጥህን ነገር ሁሉ አትቀበለው። አእምሮህንም ሆነ ልቦናህን አትክፈትለት። ባለህ ኃይል ሁሉ ተቃወመው እንጂ ተስፋ በመቁረጥ ከእርሱ ጋር አትላመድ። አሳቦቹን፣ፈተናዎቹን፣ምኞቶቹንና መንገዶቹን ሁሉ ተቃወም። "ከኃጢአት ጋር እየተጋደላችሁ ገና ደምን እስከ ማፍሰስ ድረስ አልተቃወማችሁም።" (ዕብ 12:4) የሚለው የሐዋርያው ቃል ቢኖርም ጠንቃቃ እንጂ ቸልተኛ አትሁን። ብዙ ጊዜ ለወታደሮች "እርሱ አንድ ጥይትና አንድ ሰው እስኪቀር ይዋጋል።" እንደሚባለው አንተም በውጊያህ ላይ ሰማዕት እስክትሆን (" . . ደምን እስከ ማፍሰስ") ድረስ ተዋጋው። በአእምሮህ ወይም በፈቃድህ ውስጥ የመርፌ ቀዳዳን የምታህል ክፍተት እንኳ እንዳልሰጠኸው እርግጠኛ ሁን። አለዚያ ያቺን ማስፋቱን በመቀጠል ከፍተኛ ችግር ላይ ይጥልሃል። ስለዚህ ተቃወምና አባረው። ምንም ደጋግሞ ኃጢአት መልካም እንደሆነ ማስረጃ እያቀረበ ቢከራከርህም በአሳቡ አትስማማ። ኃጢአትን በተመለከተ ከዲያብሎስ ጋር ምንም ዓይነት ክርክርና ጭቅጭቅ ቢደረግ መግባባት አይቻልም። አንድ ቅዱስ አባት "ዲያብሎስ አድሮበት ከሚዋጋህ ሰው ጋር አትደራደር" በማለት የተናገረውን ቃል ተከተል። ዲያብሎስ ኃጢአትን ካቀረበልህ በኋላ ያን ኃጢአት አስመልክቶ ሊከራከርህ የሚወደው የኃጢአት ድርድር ዙሪያ ለረዥም ጊዜ በማቆየት በዚያው ኃጢአት እንድትደክም ለማድረግ ነው። ከዚህ በኋላ ተሸናፊ ነህ። ስለዚህ አእምሮህን ሙሉ ለሙሉ መቆጣጠር በምትችልበት በመጀመሪያዋ ደረጃ ላይ ሳለህ ተቃወመው። መቃወምህን ካዘገየኸው የእርሱ ኃይል እየበረታ ሲመጣ የአንተ ፈቃድ ቀስ በቀስ እየቀነሰ ይሄዳል። ከዲያብሎስ ጋር የሚኖርህ ቆይታ እየተራዘመ በሄደ ቁጥር ተቃውሞህ ይቀንሳል። ልክ ደሊላ ሶምሶንን ነፍሱ እስከ ሞት እስክትጨነቅ ድረስ ወትውታ የኃይሉን ምሥጢር እንዳወቀች ማለት ነው።

ምን ጊዜም ቢሆን "የዚህን አሳብ መጨረሻውን እስከማይ እቆያለሁ" አትበል። እውነቱን ልንገርህና መጨረሻውን በሚገባ ስለምታውቀው ራስህን እንዲህ እያልህ አታታለው። አእምሮህን በጥቂቱም ቢሆን ለዲያብሎስ ከፈትህ ማለት ለእግዚአብሔር አለመታመንህን አሳየህ ማለት ነው። ስለዚህ ከዲያብሎስ፣ከመንገዶቹና ከሠራዊቱ ሁሉ ራቅ! በሴራዎቹ እስክትወድቅ ድረስ አትዘግይ። ይልቁንም "ሂድ! አንተ ሰይጣን" (ማቴ 4:10) በማለት አጥብቀህ ተቃወመው። ይሄኔ በተቃውሞህ ጽኑ መሆንህን ያውቃል። ማንኛውንም የዲያብሎስ አሳብ በጽናት ከተቃወምህ ዲያብሎስ በአንተ ላይ አከብሮታዊ ፍርሃት ያድርበታል። ዲያብሎስ ባለው ጽኑ ጥበብ ተቃውሞን

ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና።” (2ኛ ጢሞ 1፡7) በማለት ተናግሯል። በመሆኑም የእግዚአብሔር ልጆች በውጊያው አውድማ ላይ አይወድቁም። ጀግኖች በመሆናቸውም ዲያብሎስም ሆነ ኃጢአት አያሸንፋቸውም። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ስለ እግዚአብሔር ልጆች የጻፈው መልእክት ምንኛ ድንቅ ነው። “ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአት እንዳያደርግ፤ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተወለደው ሁሉ ራሱን እንዲጠብቅ ክፉውም እንዳይነካው እናውቃለን።” 1ኛ ዮሐ 5፡18። የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑቱ ሁሉ የማሸነፍና እግዚአብሔር የገባላቸውን ቃል ኪዳን የማግኘት መንፈስ አላቸው።

እግዚአብሔር ለጻድቁ ኢዮብ የሰጠውን ምስክርነት አስተውል። “በምድር ላይ እንደ እርሱ ፍጹምና ቅን እግዚአብሔርን የሚፈራ ከክፋትም የራቀ ሰው የለም . . . እስከ አሁን ፍጹምነቱን ይዟል።” ኢዮብ 2፡3። ዲያብሎስ ታዲያ እንዲህ ያለውን ሰው በማጥቃት ያሸንፈው ዘንድ ይችላልን? እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ይዋጋልና አይችልም። በውጊያ ሰዓት ምንጊዜም ማሸነፍን እንጂ መሸነፍን ከፊትህ አታስቀድም። “እግዚአብሔርን እስከተጠለልኩና እርሱ እስከተዋጋልኝ ድረስ መውደቅን አላስበውም። ዲያብሎስንም አልፈራውም።”ይልቁንም “በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም።” (መዝ 22፡4) በል። በእግዚአብሔር እቅፍ ውስጥ ነኝ። የእጆቼም መዳፍ ቀርጸውኛል ብለህ ማሰብንም አትዘንጋ። ኢሳ 49፡16። መድኃኒታችንም ስለ በጎቹ እንዲህ ብሏል። “እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፤ለዘላለም አይጠፉም፤ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም። . . . ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም።” ዮሐ 10፡28-29። በእምነት እንደምናሸንፍ ሁሉ በትሕትናም እናሸንፋለን።

ለ. በትህትና።

ቅዱስ እንጦንስ ርኩሳን መናፍስትን በትሕትና ያሸንፋቸው ነበር። ዙሪያውን በከበቡት ጊዜ ሁሉ “እናንተ ኃያላን ናችሁ፤ከእኔ ከደካማው ምን ትፈልጋላችሁ?” በማለት ከጠየቃቸው በኋላ “ከእነርሱ በጣም ታናሽ ከሚባለው ጋር እንኳ መዋጋት የማልችለውን ባሪያህን አድነኝ” በማለት ወደ አምላኩ ይጸልይ ነበር። እነዚያ ርኩሳን መናፍስትም እንዲህ ባሉ የትሕትና ቃላት የተመላ ጸሎቱን ሲሰሙ ሊሸከሙት ስለማይቻላቸው እንደ ጢስ በነው ይጠፋሉ። ታላቁ ቅዱስ መቃርስም እንዲሁ ዲያብሎስን በትሕትና አሸንፎታል። በአንድ ወቅት ዲያብሎስ ለዚሁ አባት ተገልጠ “መቃርስ ሆይ! አንተ ትጾማለህ፤እኛም አንበላም፤ሌሊት አታንቀላፋም፤ እኛም አንተኛም። በምድረ በዳ ትኖራለህ፤እኛም በዚያ እንኖራለን። የምታደርገውን ሁሉ እናደርጋለን ግን በአንድ ነገር ትበልጠናለህ” ይለዋል። መቃርስም ይህ አንድ ነገር ምን እንደሆነ ሲጠይቀው “የምትበልጠንና የምታሸንፈን በትሕትናህ ነው።” በማለት መልሶለታል። ስለተለያዩ ምክንያቶች ትሕትና ዲያብሎስን ያሸንፈዋል።





* ዲያብሎስ ትሑት አይደለም። እንዲያውም ትሕትና ለውድቀቱ ምክንያት የሆነውን ትዕቢቱን ያስታውሰዋልና ሊያየውም ሆነ ሊሰማው አይፈልግም።

* አሁንም ትሕትና የሰው ልጆችን ያድን ዘንድ በባሪያው መልክ ራሱን ባዶ አድርጎ የመጣውን ኢየሱስ ክርስቶስን ስለሚያስታውሰውና ለዚህ መነሻ ምክንያት የምትሆነው ጥቂት ትሕትና ስለምታናውጠው ትቶ ይጠፋል እንጂ አይዋጋም።

* በመጨረሻም ትሑት ሰው ድካሙን ስለሚያውቅ ዲያብሎስ ውጊያ በሚከፍትበት ጊዜ ሁሉ የእግዚአብሔርን እርዳታ በመሻት ስለሚጮህ ከሁሉ የበለጠ ይህ ዲያብሎስን ያስፈራዋል። በአንድ ወቅት በማስታወሻዬ ላይ እንደዚህ የሚሉ ቃላትን ጽፌ ነበር። “ዲያብሎስ በአንድ ወቅት ለእግዚአብሔር ‘ጠንካሮቹን ለእኔ ተውልኝ። ስለ እነርሱ ኃላፊነት እወስዳለሁ። ደካሞቹን ግን ላሸንፋቸው አልችልም። ምክንያቱም ኃይል እንደ ሌላቸው ሲያውቁ በአንተ ኃይል ስለሚዋጉኝ ነው።” ብሏል።”

የቅዱስ ሳራባሞን ታሪክ አጋንንት በትሕትና እንደሚወጡ ይነግረናል። በአንድ ወቅት ዘሀራ የሚባል ንጉሥ ሴት ልጅ በአጋንንት በተያዘች ጊዜ ፓትርያርኩ እነዚህን አጋንንት ያወጡላት ዘንድ ወደዚያው ይዘዋት ይመጣሉ። ፓትርያርኩም በትሕትና “እኔ እንደዚህ ዓይነት ስጦታ የለኝም፤ወደ ሳራባሞን ውሰዷት” ይላሉ። ወደ እርሱ ይዘዋት በመጡ ጊዜም እርሱም በትሕትና “የእኔ ብቻ ጸሎት በቂ አይደለም” ካለ በኋላ የፓትርያርኩን መስቀል ጠይቆ በማማተብ “በዚህ በተቀደሰ መስቀል ኃይል ትድናለች” በማለት ይናገራል። ይህን በማድረጉም የልጅቱ መፈወስ በእርሱ ሳይሆን በፓትርያርኩ ምክንያትነት መሆኑን ያሳያል። ዲያብሎስ እንዲህ ያለውን ትሕትና መሸከም ስላልቻለም ልጅቱ ልትፈወስ በቃች። የቅዱሳን አባቶች ትሕትና እንዴት ርኩሳን መናፍስትን ማስወጣት እንደቻለ ይህን በምሳሌነት ካየን አንድ ዐቢይ ጥያቄ እንጠይቅ።

የዲያብሎስን ውጊያዎች ለማሸነፍ የትሕትና ውጤቱ ምንድርን ነው?

* ትሑት ሰው ምንጊዜም ቢሆን የእርሱን ድካም ስለሚያውቅና የእግዚአብሔርን እርዳታ ስለሚሻ የእግዚአብሔር ኃይል በእርሱ ላይ ያድራል። በክንዱ ሳይመካ በእግዚአብሔር እርዳታ ስለተመካም ያሸንፋል።

* ትሑት ሰው ከጥቃቅኗ ኃጢአት ሳይቀር ራሱን ይጠብቃል። እንዳይወድቅ ስለሚፈራም ከሚፈታተኑት ነገሮች ሁሉ ይሸሻል። ማንኛውንም ነገር እንደ ቀላል ስለማይቆጥርም ራሱን ወጥመድ ላይ አይጥልም። በዚህ ትህትናው ባጎናጸፈው ጥንቃቄ ዲያብሎስን ያሸንፋል።

* ትሑት ሰው የገጠሙትን ውጊያዎችም ይሁን ድካሙን ስለማይደብቅና መፍትሄ ስለሚያገኝላቸው ያሸንፋል።

* ትሑት ሰው ለትንሿ ኃጢአት ሳይቀር ዘወትር ይጸልያል። በዚህም ለሚገጥመው ውጊያ ሁሉ እግዚአብሔርን ስለሚጠራና ስለሚይዝ ያሸንፋል።

* ትሕትና በራሱ ርኩሳን መናፍስት ሊሸከሙት የማይችሉት መልካም ምግባር በመሆኑ ይሸሻሉ።

ሐ. በጥበብና በማስተዋል።

አንድ ዓይነት አሳብ በአእምሮህ ደጋግሞ ሲመላለስ በሚገባ ትመረምረው ዘንድ ይገባሃል። የዲያብሎስ ውጊያ ይሆን? ምን ደግ ወይስ ምን ክፉ ጎን አለው? እነዚህን ጥያቄዎች ራዕይ ወይም ህልም ባየህ ጊዜም ሆነ የሌሎችን ምክር በሰማህ ጊዜ ለህሊናህ አቅርብ። ዲያብሎስ ሊያታልልህ ሲሞክርም ይህንኑ አድርግ። ሐዋርያው ነገሮችን በማስተዋል መመርመር እንደሚገባን አስመልክቶ " . . . መንፈስን ሁሉ አትመኑ፤ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ መርምሩ።" (1ኛ ዮሐ 4፡1) ብሎናል።

ታዲያ እንዲህ ያለው ጥበብ እውቀትና ማስተዋል መገኛው የት ነው? የመጀመሪያውን ሰው እግዚአብሔር ጠቢብ አዋቂና አስተዋይ አድርጎ ፈጥሮታልና ሰው በተፈጥሮው ብልህ ይሆናል። ስለሆነም የዲያብሎስን ውጊያ ከመንፈሳዊ አሳብ ለይቶ የማወቅ ችሎታ ይኖረዋል። ሁለተኛው ሰው ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን ገድላትንና የቅዱሳንን ታሪክ በማንበብ ጥበብን ያገኛል። ሦስተኛው ሰው ደግሞ ጥበብን ከልምድ ያገኛታል። እያንዳንዷ ውድቀቱ የዲያብሎስን የውጊያ ዘዴ ስለምትገልጥለትና ትምህርት ሰጥታው ስለምታልፍ ዳግመኛ አይወድቅም። ይህን አስመልክቶ አንድ ጻድቅ አባት ሲናገር "ዲያብሎስ በተመሳሳይ ኃጢአት ሁለቴ የጣለኝን ጊዜ አላስታውስም።" ብሏል። ሰው ጥበብን በምክር በመመሪያና በትምህርት ሊያገኛት ይችላል። በዚህም የዲያብሎስን ውጊያ ለይቶ በማወቅ ስለሚገልጠው ከዚያ ይርቃል ጠላቱም አያታልለውም።

ጥበብ የዲያብሎስን ደባ መግለጥ ብቻ አይደለም ምን እርምጃ መውሰድ እንደሚገባንም ትጠቁማለች። ስለሆነም ጠቢብና አስተዋይ ሰው የዲያብሎስን ደባ እንዴት ማምለጥ እንደሚችል፣ከወጥመዶቹም እንዴት መሸሽ እንደሚገባው፣ከወደቀም በኋላ እንዴት እንደሚነሳና ወደ ኃጢአት ከሚያደርሱ መንገዶች ሁሉ እንዴት መውጣት እንዳለበት ያውቃል። ይህን የማያውቅ ቢሆን እንኳ ጥበብ ሌሎችን ያማክር ዘንድ ትመራዋለች።

መ. በምክርና በንስሐ።

መንፈሳዊ ምክር የዲያብሎስን ደባዎች ከመግለጡ ባሻገር እንዴት ከእነዚህ ደባዎች ማምለጥ እንደሚቻልም ያመላክታል። መካሪው አሳቧን





የገለጠችለት ነፍስ ትድን ዘንድ ቅዱስ ጳውሎስ እንደጠቀሰው ይጸልይላታል። "ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ ፤ እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጡ አድረገው ይህንኑ በደስታ እንጂ በኃዘን እንዳያደርጉት ይህ የማይጠቅማችሁ ነበርና ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ።" ዕብ 13፡17። ስለዚህ "መሪ የሌላቸው ሁሉ እንደ ዛፍ ቅጠሎች ረግፈው ይቀራሉ።" እንደተባለው በመንፈሳዊ ጉዞ የራሱን ፈቃድ የሚከተል ሁሉ በዲያብሎስ ወጥመድ ላይ ይወድቃል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የንስሐ አባት አስፈላጊነት ጥቅሙ ለዚህ ነው። ራስህን ለማሳፈርና ለማዋረድ ልብህን በእርሱ ፊት ለእግዚአብሔር ትገልጣለህ። ከዚያም ምን ማድረግ እንደሚገባህ ይመክርሃል። ንስሐ ጀማሪ ክርስቲያኖች ያላስተዋሉት ውጊያ ካለ ይገልጣል። ንስሐ የሚገባ ሰው በንስሐ መልካም ምግባርነት ብዙ ኃጢአቶችን ያስወግዳል። እነዚህን የበዙ ኃጢአቶች ያሠሩት ርኩሳን መናፍስት የሰውየውን መዋረድና ንስሐ መግባት መሸከም ስለማይቻላቸው በነው ይጠፋሉ።

ርኩሳን መናፍስት በጨለማ መሥራትን ይወዳሉ። ንስሐ ግን ይገልጣቸዋል። ምክር ወጥመዳቸውን ይሰባብረዋል። በምሥጢረ ንስሐ የሚሰጠው ቀኖናም ኃይላቸውን ያጠፋዋል። ስለሆነም ኃጢአቶቹን የሚናዘዝና ምክር የሚቀበል ሰው የንስሐን ሕይወት ስለሚመራ ከዲያብሎስ ውጊያዎች ይድናል። ኃጢአት ሙሉ ለሙሉ ሊተወው ባይችልም እንኳ ሊያጠቃው የሚሞክረው በጣም በተዳከመ ኃይል ይሆናል። ይህ በመሆኑም ዲያብሎስ ንስሐን ለማደናቀፍ ሲል ተናዛዢው ናዛዢውን (የንስሐ አባቱን) እንዲጠራጠር ያደርገዋል። እዚህ ጋ ዓይናፋር የሚያደርገው ዲያብሎስ ንስሐን ለማደናቀፍ ይገባል። ከዚያም የዝሙት ዲያብሎስ ይመጣና "ተመልሼ ስለማሳስትህ ንስሐ ለምን ይጠቅመሃል?" ይለዋል። ከዚያም የአሳብና የክርክር ዲያብሎስ በአጠቃላይ ንስሐን በተመለከተ ጉዳይ ላይ ውይይቱን ይከፍታል። በመጨረሻም ንስሐንና የንስሐ አባትን አስመልክቶ ጥርጥርን ለመዝራት የጥርጥር ዲያብሎስ ይመጣል።

አንተ ግን ንቃ! ይህን ሁሉ ደባውን ተናዘዝ! ይህን ካደረግህ ዲያብሎስ መግቢያ ቀዳዳ ስለሚያጣ አንተን እንደ ችግር ፈጣሪ ባላጋራ በመቁጠር ትቶህ ይሄዳል።

ሠ. በንቁነትና በጥንቃቄ።

ምክር ለማግኘት መናዘዝህና አንተነትህን በካህኑ ፊት መግለጥህ ብቻ በቂ አይደለም። ሐዋርያው እንደተናገረው ለድነትህም ንቁ መሆን አለብህ። "በመጠን ኑሩ ንቁም ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን . . ." 1ኛ ጴጥ 5፡8። ምንም እንኳ ባላጋራህ ባልጠበቅኸው ሰዓት፣በተዘናጋህ ጊዜ፣ቸልተኛ ስትሆን፣ስትዳከም፣ስትጨነቅና መንፈሳዊ ተግባራትህን ማከናወን ስትረሳ ጠብቆ ቢያጠቃህም ጠንካራና ንቁ ስለሆነ አንተም ንቁ ልትሆን ይገባሃል። ቅድስት ቤተክርስቲያን በተለያዩ በዛ ባሉ አጋጣሚዎች ንቁ እንድንሆን ትጠራናለች። በጾም ወቅት "ንቁ ተዘጋጁ" ትላለች። በቅዳሴ

ክርስቲያን ግን ውጊያ ከመክፈቱ አስቀድሞ ጠብቀን ማለትን ታስተምራለች። ከ'አድነን' ጸሎት 'ጠብቀን' ጸሎት ይቀድማልና። ዲያብሎስ በእኛ ላይ ያጠመዳቸው ወጥመዶች ላይ ከመውደቅ እንዲጠብቀን አስቀድመን እግዚአብሔርን እንጠይቀዋለን። በወጥመዶቹ ላይ ከወደቅን በኋላ ግን አድነን ብለን እንጮኻለን። ለዚህም ነው በምስጋና ጸሎታችን ውስጥ "ፈተናን ፤ የዲያብሎስን ሽክም፤የጠላትንም መነሳት የተሰወረውንና የተገለጸውን ከእኛ አርቅልን" የምንለው። እነዚህ ሁሉ በእኛ ላይ ከመምጣታቸው በፊት ነው እንዲያርቅልን የምንጠይቀው። "ወደ ፈተናም አታግባን" የምንለውም ለዚሁ ነው። ዲያብሎስ ጦርነቶቹን ከመክፈቱ አስቀድሞ የእግዚአብሔርን እርዳታ እንጠይቃለን እንጂ ግራ እንጋባም፤እንደነጋገርምም።

"ይህን ለሰባት ሺህ ዓመታት ሰዎችን በመዋጋት ልምድ ያካበተ ዲያብሎስን እኔ ብቻዬን አልችለውም። አንተ እግዚአብሔር ግን ሕያውና ከዲያብሎስ በፊት የነበርህ ነህ። ከመውደቁ አስቀድሞ እርሱም የእጅህ ሥራ ነበር። አንተ ደባዎቹን ሁሉ ስለምታውቅ ልታስረው፤ልትገድበው ፤አልፎ ተርፎም ሙሉ ለሙሉ ልታጠፋው ትችላለህ። ስለዚህ ከእርሱ ውጊያዎች ሁሉ አንተ አድነኝ።" እያልክ በጸሎት ጥላ ሥር ሆነህ ፈጣሪህን ትለምናለህ፤ያለ ጸሎት አትድንምና። ከጠላት ጋር ተዋግተህ ከወደቅህ ግን ጸሎትህ ተቀባይነት አለማግኘቱን አስተውል! ጸሎትህ ጠንካራ ከሆነ ግን ያለ ምንም ጥርጥር ታሸንፈዋለህ። እግዚአብሔር የድሀውን ጩኸት ሰምቶ እንደሚመልስም እርግጠኛ ሁን። ምክንያቱም "ስለ ድሆች መከራ ስለ ችግረኞች ጩኸት፤እግዚአብሔር አሁን እነሳለሁ ይላል።" የሚል ቃል አለና። ስለዚህ "አቤቱ ተነሣ፤ጠላቶችህም ይበተኑ የሚጠሉህም ከፊትህ ይሽሹ።" ዘኍ 10፡35 "አቤቱ አድነኝ ደግ ሰው አልቋልና፤ከሰው ልጆችም መተማመን ጎድሏልና።" መዝ 11፡1። በል። አሁንም በግልጽ እንዲህ በል። "ኃያል ሆይ በቁንጅናህና በውበትህ ሰይፍህን በወገብህ ታጠቅ።" መዝ 44፡3።

አቤቱ ርኩሳን መናፍስት ለእኔ ጠላቶች ከመሆናቸው በፊት ለአንተ ነበሩ። አሁንም በእኔና በሌሎችም አድረው መንግሥትህን እየተቃወሙ ነውና ስለ እኔና ስለ ሌሎች ብለህ ተዋጋቸው። ያለ አንተ ምንም ማድረግ አይቻለንምና ለአጋንንት ውጊያ ብቻችንን አትተወን። ዮሐ 15፡5። በጦርነቶች ሁሉ የእግዚአብሔርን ድል ማድረግ የቀመሰው ንጉሥ ዳዊት እንዲህ ነበር ያለው "የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች ፤የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገችኝ።" መዝ 118፡15፤16። በሕይወትህ ዘመን የእግዚአብሔር ቀኝ ዳስሳሃለችን? እግዚአብሔር ለሙሴ የተናገረውን የማዳን ቃል አጣጥመሃልን? እንዲህ ነው የሚለው። "የእግዚአብሔርን ማዳን እዩ፤እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል፤ እናንተም ዝም ትላላችሁ።" ዘጸ 14፡13-14። ይህን ካጣጣምክ ከመዝሙረኛው ጋር እንዲህ በል። "በአጠገብህ ሺህ በቀኝህም አሥር ሺህ ይወድቃሉ፤ወደ አንተ ግን አይቀርቡም።" መዝ 90፡7። አንተ በራስህና በሌሎች ፈቃድ፤ምክንያት ማስተዋልና ተግባር መደገፍን ተለማምደሃል። የእግዚአብሔርንስ? የጠንካራ ጸሎት ውጤትንስ ቀምሰሃልን? እግዚአብሔርን "ልሞክረውና ከወደቅሁ መነሳትም ካቃተኝ





እፈልግሃለሁ" የሚለውን ሰው ግን አትምሰለው። ወድቀህ መነሳት እስኪያቅትህ ድረስ ለምን ትጠብቃለህ? አሁኑኑ ፈልገው! ኃይሉ እንዳትወድቅ ይደግፍሃልና። በእርግጥ እግዚአብሔር ከወደቅህ በኋላም ያነሣሃል። ግን ስተነሳ ተጎድተህ ነው የምትነሳው። በኃያሉ እግዚአብሔር ክንዶች ሥር ተጠልለህ "አቤቱ ጌታ ሆይ ከባላጋራችን ደባ አድነን ፤ ካጠመደብንም ወጥመዶች ሁሉ . . ." በለው። በዚህ ጊዜ መዝሙረኛው እንደተናገረ መጥቶ ነጻ ያወጣሃል፤ ያድንሃማል። "ወጥመድ ተሰበረ እኛም አመለጥን። ረድኤታችን ሰማይንና ምድርን በሠራ በእግዚአብሔር ስም ነው።" መዝ 123፡7-8።

እንዲህ ከሆነ ከአንተ አስቀድመው ለታገሉት አባቶች ድልን ያጎናጸፈ እግዚአብሔር ለአንተም እንዲያጎናጽፍህ ጠይቀው። ለእነርሱ የሰጠውን ኃይል ለአንተም እንዲሰጥህ ጠይቀው። የመንፈስ ቅዱስን ጸጋም እንዲያድልህ ጠይቀው። አስቀድሞ ዲያብሎስን "ሂድ አንተ ሰይጣን!" ብሎ እንደገሰጸው እንዲገስጽልህም ጠይቀው። ማቴ 4፡10።

ሰ. ሂድ አንተ ሰይጣን!

"ሂድ አንተ ሰይጣን" የሚለው የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የተግሳጽ ቃል ለእርሱ ላቀረበበት ፈተና ብቻ ሳይሆን ዲያብሎስ በሰው ልጆች ላይ ለሚከፍታቸው ጦርነቶች ሁሉ የተነገረ የተግሳጽ ቃል ነው።

ዲያብሎስ በአንተ ላይ የሚከፍተው ጦርነት እጅግ እንዳይከብድና ጌታ መጥቶ እንዲያባርርልህ የእነዚህን ቃላት ኃይል በሕይወትህ ተለማመዳቸው። አሊያም ለጊዜው ብቻ እንዳይለይህም (ሉቃ 4፡13) ለማድረግ ተጠቀምባቸው። ውጊያው ከፊትህ ገለል ሲልልህ፤ምኞቱና ፍትወቱ እንደቀድሞው ሳያስቸግርህ ሲቀር፤ድካሙ ሲጠፋልህና በምትኩ አዲስ ብርሃን ሲፈነጥቅልህ ያን ጊዜ ጌታ ዲያብሎስን ከአንተ ለማራቅ ገስጾ እንዳባረረው ታውቃለህ። ዲያብሎስ ያለ ልክ እንዲፈትነን እግዚአብሔር አይፈቅድለትም። እግዚአብሔር ዲያብሎስ በእጁ ውስጥ እንዲያስገባንም አይፈቅድለትም። እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ በዲያብሎስ ስንፈተን ዝም የሚለው ከእነዚህ ውጊያዎች መንፈሳዊ ጥቅሞችን እናገኝ ዘንድ ዕድሉን ሲሰጠን ነው። ሆኖም ግን ዲያብሎስ ተስፋ ማስቆረጥና ግራ መጋባትን ሲያጸናብን እግዚአብሔር "ሂድ አንተ ሰይጣን!" በማለት ይገስጽልናል።

አንዳንዴ ሰው ከዲያብሎስ ውጊያዎች እፎይ የሚልባቸው ጊዜያት ይኖራሉ። ፍጹም ከእግዚአብሔር ጋር መሆኑና ህብረት መፍጠሩ ይሰማዋል። አልፎ ተርፎም እንዴት ኃጢአት እንደሠራና እንደወደቀ ሲያስብም ይገረማል። በዚህ መንፈሳዊ መደላደል መካከልም የዲያብሎስን ፈተና ያሸነፈው ኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጋና ይግባውና "እኔ የፈቀድኩልህ እንድትፈትነውና እንድትፈትሸው እንጂ ይህን ያህል እንድታስጨንቀው አይደለም። ስለዚህ ሂድ አንተ ሰይጣን!" በማለት እንደገሰጸለት በሚገባ

ጽድቅ አይሠራምና።" (ያዕ 1፡20።) በል። በዓይንህ (በማየት) የሚዋጋህ ከሆነ ደግሞ "ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል።" (ማቴ 5፡28) የሚለውን ጥቅስ ከፊትህ አስቀድም። በዝሙት የሚዋጋህ ከሆነ ደግሞ የሐዋርያውን ቃል አስታውስ። "ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን?" (1ኛ ቆሮ 6፡19)። "ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደሆነ አታውቁምን? እንግዲህ የክርስቶስን ብልቶች ወስጄ የጋለሞታ ብልቶች ላድርጋቸውን? አይገባም።" 1ኛ ቆሮ 6፡15። አሁንም ዲያብሎስ በአንደበት ኃጢአት የሚፈታተንህ ከሆነ "በቃል ብዛት ውስጥ ኃጢአት ሳይኖር አይቀርም፤ ከንፈሩን የሚገታ ግን አስተዋይ ነው።" (ምሳ 10፡19) " . . . ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ይሁን።" (ያዕ 1፡19።) በል። ወይም ደግሞ እንዲህ በል። "አቤቱ ለአፌ ጠባቂ አኑር፤የከንፈሮቼንም መዝጊያ ጠብቅ።" መዝ 140፡3። በዚህ ዓለምና በፈተናዎቹ ሊዋጋህ ከመጣ ደግሞ በእነዚህ የእግዚአብሔር ቃላት መልሰው። "የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኗል።" (ያዕ 4፡4) "ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ . . . ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም።" (1ኛ ዮሐ 2፡15-16)። "ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ።" 1ኛ ዮሐ 2፡17። ከዚህ አኳያ በመጽሐፈ መክብብ የተጻፈውን በተለይም እንዲህ የሚለውን "ከንቱ ከንቱ የከንቱ ከንቱ ሁሉ ከንቱ ነው . . . እነሆ ሁሉ ከንቱ ነፋስንም እንደመከተል ነበር፤ከፀሐይ በታች ትርፍ አልነበረም።" መክ 1፡2፤14። 2፡11። በትዕቢት ከተዋጋህም "ትዕቢት ጥፋትን፤ኩሩ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል።" (ምሳ 16፡18) "እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል።" ያዕ 4፡6፤1ኛ ጴጥ 5፡5።

እነዚህንና እነዚህን የመሰሉ በውጊያዎችህ ላይ የምትጠቀምባቸው ሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በብዛት ስላሉ በአእምሮህ ያዛቸው በልቦናህም ጠብቃቸው። ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ "የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፤የሚሠራም ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው።" (ዕብ 4፡12) የሚል ቃል አለና። የእግዚአብሔርን ቃል ባስታወስክ ቁጥር ከውስጥህ በእውነት ሥራን ሠርቶ እንደሚሄድ እርግጠኛ ሁን። "ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል፤የምሻውን ያደርጋል የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም።" ኢሳ 55፡11። እንግዲህ ዲያብሎስ በሚከፍትብህ ውጊያዎች ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቃል ኃይል እንዳለው ሞክርና ተመልከት።





# ምዕራፍ አምስት

## የዲያብሎስ ውጊያዎች ጥቅም

ዲያብሎስ እኛን እንዳይዋጋን እግዚአብሔር አይከለክለውም። በሚከፍትብን ውጊያዎች ሁሉ ግን ከጎናችን በመሆን ውጊያዎቹን መንፈሳዊ ጥቅሞች እንድናገኝባቸው አድርጎ መለወጥ ይችላል። በአንድ ወቅት በአንድ ታላቅ አባት ጸሎት ጥላ ሥር እየተጠበቀ የኖረ ሌላ አባት ጊዜው ሲደርስ ካሁን በኋላ ብቻውን በበዐት በመወሰን ከዲያብሎስ ውጊያዎች መንፈሳዊ ጥቅም እንዲያገኝ ያ ታላቅ አባት እንዳሰናበተው እናስታውሳለን።

ብቻቸውን በበዐት በመወሰን በምድረ በዳና በዋሻ ቆይተው ከዲያብሎስ ጋር ለረዥም ጊዜ እየተዋጉ ራሳቸውን ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር ፍቅር አሳልፈው የሰጡ መናንያን በእነዚህ የዲያብሎስ ውጊያዎች የረዥም ጊዜ ልምድ አላቸው። ይህ ከሆነ ከዲያብሎስ ውጊያዎች የምናገኛቸው መንፈሳዊ ጥቅሞች ምንድር ናቸው? ምንስ ያስተምሩናል?

### 1. ትሑት መሆንን።

ዲያብሎስ አንድን ሰው ከፉኛ ደጋግሞ ከተዋጋው ድካሙ እየተሰማው ስለሚሄድ ቀድሞ የነበረበትን የትዕቢት መንፈስ ፍጹም በማስወገድ ትህትናና ተነሳሒነት ይሰማዋል። ሊወድቅ እንደሚችል ፈቃዱም ከንቱ መሆኑን በመረዳት ኃጢአት ምን ያህል ብዙዎችን እንደጣለችም ይገነዘባል። "ወግታ የጣለቻቸው ብዙ ናቸውና፤እርስዋም የገደለቻቸው እጅግ ብዙ ናቸው።" ምሳ 7፡26

### 2. የእግዚአብሔርን እርዳታ ለማግኘት ጸሎትና ጾም መያዝን።

ሰው በእረፍት ከኖረ የእግዚአብሔርን እርዳታም ሆነ ያ እርዳታ በአፋጣኝ እንደሚያስፈልገው ላይጠይቅ ወይም ላይረዳ ይችላል። ውጊያው እየበረታበት ሲመጣ ግን እግዚአብሔር በዚህ በጨካኝ ጠላቱ ላይ ድል እንዲያቀዳጀው መጮህ ይጀምራል። በመሆኑም ደካማነቱን ሲረዳ ጾም በመያዝና አዘውትሮ በመጸለይ ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት ይጀምራል። "በመከራ ቀን ጥራኝ ፤ አድንሃለሁ አንተም ታከብረኛለህ።" መዝ 49፡15።

### 3. ለኃጥአን ርኅራኄ ማድረግን።

በዲያብሎስ ውጊያዎች ያልተፈተነ ሰው በኃጥአን ላይ ጨካኝና ስለመውደቃቸውም የሚኮንናቸው ይሆናል። በዲያብሎስ የተፈተነውና ጭካኔውን የሚያውቀው ግን ለኃጢአተኞች ይራራል ይጸልይላቸውማል።

ይህን አስመልክቶም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል። "ከእነርሱ ጋር እንደ ታሰረ ሆናችሁ እስሮችን አስቡ፤የተጨነቁትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ ሆናችሁ አስቡ።" ዕብ 13፡3። ስለ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እንዲህ ብሏል። "እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለ ተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና።" ዕብ 2፡18።

4. የውጊያ ልምድን ያዳብራሉ።

ዲያብሎስ የሚዋጋው ሰው ውጊያንና እንዴት መዋጋት እንደሚገባው ከመማሩም በላይ የዲያብሎስን ደባዎችና የጠላትን ጥበብ ያውቃል። በመውደቁና በመነሳቱ መካከል ልምዱን ያዳብራል። እያንዳንዷ የእድገት ደረጃ ከፈተና በኋላ የምትገኝ ናት። ፈተናውን የሚያልፍ ደግሞ ልክ እንደ ተማሪ ከአንዱ ወደ ሌላው ይዘዋወራል። ስለሆነም በዲያብሎስ ውጊያዎች ውስጥ ያለፈ ሁሉ ጥሩ የውጊያ ልምድ ይኖረዋል። እነዚህ መንፈሳዊ ልምምዶች መንፈሳዊ መመሪያ የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ናቸው። ሌሎችን የመርዳት የማበረታታትና የጠላትን ተንኮል የማጋለጥ ልምድ ያላቸው ሰዎችን የሚያፈሩ ትምህርት ቤቶች ማለት ነው።

5. የድል አክሊልን ያቀዳጃሉ።

ከቅዱሳን ወገን የሆነ አንድ አባት "ያልተጋደለ አያሸንፍም፤ ያላሸነፈም የድል አክሊል አያገኝም።" በማለት የተናገረው ትክክል ነው። የዲያብሎስን ውጊያዎች በጽናት መከላከላችን፣መታገላችንና መቋቋማችን ሁሉ ለጌታችን ያለንን ፍቅር የሚያሳይ በመሆኑ የድል አክሊል ያሰጠናል። ይህን አስመልክተው አንድ አባት ሲናገሩም "አክሊሎቹ የሚሰጡት ድል ለተቀዳጁት ወታደሮች ብቻ አይደለም። እጃቸውን ለጠላት ሳይሰጡ በጽናት ተዋግተው ለተጎዱትና ለቆሰሉትም ጭምር እንጂ።" ብለዋል።

6. መንፈሳዊ ንቃትና ዝግጁነትን ያጎለምሳሉ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ወገባችሁ የታጠቀ መብራታችሁም የበራ ይሁን።" (ሉቃ 12፡35) በማለት ተናግሯል። በውጊያ ውስጥ ያለ ሰው በጾም፣በጸሎት፣በትህትናና በመንፈሳዊ ምክር በመታገዝ ዲያብሎስን ድል ለማድረግ ምንጊዜም ንቁና ዝግጁ ይሆናል። ውጊያዎቹ ጥቂት ከሆኑ ግን በመንፈሳዊ ተግባራቱ ይደከማል። ውጊያዎቹ ግን በማንኛውም ጊዜ ዝግጁ ንቁና ራሱን የሚጠብቅ እንዲሆን ያደርጉታል። መውደቅን ስለሚፈራም ለማሸነፍ በቂ ዝግጅት ያደርጋል።

7. ጠንካራና የማንፈራ ያደርጋሉ።

ውጊያን የሚፈራ ሰው ውጊያን መጋፈጥ የማይፈልግ አሊያም የማይዋጋ ሰው ነው። በውጊያዎች ውስጥ ያለፈ ሰው ግን ድፍረትና





ጥንካሬን ገንዘቡ አድርጓል። የሚቀዳጃቸው የድል አክሊሎች ወደ ሌሎች ውጊያዎች እንዲገባ ስለሚያበረታቱት መውደቅን አይፈራም። አንድ ተማሪ "እወድቃለሁ ብዬ ስለምፈራ ፈተና አልፈተንም ወይም አላጠናም ወይም ደግሞ ትምህርት ቤት አልሄድም" ማለት ይችላልን? አይችልም። ፈተናዎቹን ይፈተናል። እንዲያውም "ለመማርና ለመፈተን የሚያዳግቱኝን ችግሮች ሁሉ እወጣቸዋለሁ!" በማለት በድፍረት ይናገራል።

8. የእምነት ት/ቤቶች ናቸው።

በእነዚህ ውጊያዎች ውስጥ እንዴት እግዚአብሔር እንደሚታደግ ፣እንዴት እንደሚረዳና ድል እንደምናደርግ፣እንዴት ጠላትን እንደሚገስጽ፣እንዴት ብላቴናው ዳዊት ግዙፉን ጎልያድን ለማሸነፍ ኃይል ማግኘቱን እንመለከታለን። ይህም በእግዚአብሔር ፍቅር፣እንክብካቤና ለእኛ በሚያደርጋቸው ሥራዎች ላይ ጽኑ እምነት እንዲኖረን ያደርገናል። በዚህም እነዚህ የዲያብሎስ ውጊያዎች ለእኛ የእምነት ት/ቤቶች ናቸው እንላለን።

9. የዲያብሎስን እኩል ተሳትፎ ያሳያሉ።

ምንም እንኳ ዲያብሎስ "እግዚአብሔር ለምን ይረዳቸዋል? እኔ አጋጣሚውን ባገኝ እጥላቸው ነበር።" በማለት በቁጭት ቢቃወምም እንኳ ባለው ኃይል ሁሉ የእግዚአብሔርን ልጆች የመዋጋት ዕድል ተሰጥቶታል። ይህን ዕድል ማግኘቱን በኢዮብ ታሪክ ውስጥ ብንመለከትም ኢዮብ እስከ መጨረሻው ጽናቱን እንደያዘ ቆይቷል። (ኢዮ 2) ምንም እንኳ እግዚአብሔር ዲያብሎስ እኛ ልጆቹን እንዲዋጋ ቢፈቅድለትም አሸንፈው የምናዋርድበትንም ኃይል አብሮ ሰጥቶናል።

10. የመንግሥተ ሰማይ በሮችን ይከፍታሉ፤ደረጃችንንም ይወስናሉ።

እያንዳንዱ እንደ ሥራውና እንደ ተጋድሎው የዘራውን ያጭዳል። አማኞችም ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር በሚቻላቸው ሁሉ መግለጽ አለባቸው። ይህ ፍቅራቸው ደግሞ በሚያደርጓቸው መንፈሳዊ ውጊያዎች ካልሆነ በምን ሊገለጽ ይችላል? ያለ እነዚህ መንፈሳዊ ውጊያዎችስ በሰማያዊው መንግሥት እንዴት ማዕረግ ሊያገኙ ይችላሉ? እግዚአብሔር አምላካችን በመንፈሳዊ ውጊያዎቻችን ሁሉ ከእኛ ጋር በመሆን በእርሱ እንድናሸንፍ ይምራን!!

በነውን ሁሉ ያደረገና የሚያደርግ እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን
አሜን!!